እነዚህ ስድስት መመሪያዎች የተራራውን ስብከት እንዴት መረዳት ወይም ተግባራዊ ማድረግ እንዳለብን ለሚነሡ ጥያቄዎች በሙሉ መልስ እንደማይሆኑ እንረዳለን፤ ሆኖም ለትምህርቱ በምንሰጠው አተረጓጐም ዙሪያ እንደ መለኪያ ወይም መመዘኛ ሊያገለግሉ ይችላሉ::

## የማቴዎስን አቀራረብ ከሉቃስ አቀራረብ የምናነጻጽረው እንዴት ነው?

ሉቃስ አብዛኛውን የተራራውን ስብከት ክፍል የወሰደው ከማቴዎስ ቢሆንም የአቀማመጥ ለውጥ አድርጓል::[47] ለምሳሌ ያህል ሉቃስ እንደሚለው ኢየሱስ ስብከቱን ያቀረበው በደልዳላ ቦታ ላይ ቆሞ እንደ ነበር ማየት ይቻላል (ሉቃ 6÷17-49):: ዲኤ ካርሶን እንደሚያመለክተው፣ እንደ ማቴዎስ 5-7 ሁሉ ሉቃስም፣ (1) የሚጀምረው ስለ «ብፁዓን» በመናገር ነው፤ (2) የሚጨርሰው በአስተዋዩና ሞኙ ቤት ሠሪ ታሪክ ነው፤ (3) ወርቃማውን ሕግ፣ ሌላውን ጉንጭ የመስጠትን፣ ጠላቶቻችንን የመውደድንና በሌሎች ያለ መፍረድን ትእዛዞች አካቷል፤ የዐይን ጉድፍና ምሰሶውን ምሳሌ ሲያቀርብ ስለ ዛፍና ፍሬው የተነገረውን ምሳሌም አቅርቧል፤ (4) ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም መሄዱን ያመለክታል::[48]

ያም ሆኖ ግን በጉልህ የሚታዩ ልዩነቶችም ይኖራሉ:: (1) ሁለቱም ስብከቶች ሌላው ዘንድ የማይገኙ መረጃዎችን ይዘዋል:: (2) ማቴዎስ በመቶ ሰባት ቁጥሮች ሲያቀርብ፣ ሉቃስ ግን በሠላሳ ቁጥሮች ብቻ አቅርቧል:: (3) ብፁዓንን በተመለከተ ሉቃስ ያቀረበው በዋናነት ደረጃ ቁሳዊ ሲሆን፣ ማቴዎስ ያቀረበው ግን መንፈሳዊ ነው:: (4) ማቴዎስ ላይ የምናገኘው ተራራ ላይ የተሰጠ ሲሆን የሉቃስ ግን ደልዳላ ሜዳ ላይ ነው::

[47] ሉቃስና ማርቆስ ማቴ 5-7 በእንዴት ዐይነት ሁኔታ እንደ ተጠቀሙበት የተሟላ ሰንጠረዥ ለማግኘት J.A. Brooks, "The Unity and structure of the Sermon on the Mount," *CTR* 6/1 (1992) : 15-28 ይመ::

[48] D.A. Carson, *The Sermon on the Mount* (Grand Rapids: Baker 1978), pp. 139-140



በሁለቱ መካከል ስላለው ተመሳሳይነትና ልዩነት ምን እንላለን? አንደኛው መፍትሔ ማቴዎስም ሆነ ሉቃስ ያደረጉት የኢየሱስን አባባሎች በማሰባሰብ በስብከት መልክ ማቅረብ ብቻ ነበር ማለት ነው::[49] አንዳንዶች ይህን አንድ እርምጃ ወደ ፊት በመውሰድ እነዚህ ትምህርቶች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን በመመሪያ መልክ ትጠቀምባቸው የነበሩ እንጂ ጨርሶ ኢየሱስ ያስተማራቸው አይደሉም ብለዋል::[50]

ይሁን እንጂ ሁለቱም ወንጌላውያን ታሪካዊ እውነታ እንዳለው እንደ አንድ ወጥ ስብከት ነበር ያቀረቡት:: ለምሳሌ ያህል ሁለቱም ከተወሰነ ስፍራ ጋር (ተራራ/ደልዳላ ሜዳ) አያይዘውታል፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም መሄዱን አመልክተዋል (ማቴ 8÷5፤ ሉቃ 7÷1):: ሌላው ቀርቶ ማቴዎስ ሕዝቡ ያደረበትን መገረም እንኳ አመልክቷል (7÷28-29):: ስለሆነም ኢየሱስ ይህን ስብከት ያቀረበው በሁለት የተለያዩ ወቅቶች ነበር የሚል መደምደሚያ ላይ እንደርሳለን:: ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ለሚያስተምር ሰባኪ ይህ ያልተለመደ አይደለም::

እንዲህ ሲባል ግን ስብከቱ በሙሉ ቃል በቃል ቀርቧል ማለት አይደለም:: የማቴዎስ አቀራረብ እንኳ ዐሥራ አምስት ደቂቃዎች ብቻ የሚወሰድ ነው ይልቁንም እንደ ማንኛውም አዲስ ኪዳን የሚያቀርበው ንግግር ሁሉ፣ እጥር ምጥን ባለ ሁኔታ ዋና ዋና ይዘቱ ብቻ በጽሑፍ ተላላፎልናል:: በዚያ ዘመን እንደ ተለመደው ኢየሱስ ያስተማረው

[49] ማቴዎስ ይህን ያቀረበው ምዕ 10 ላይ ካለው ደቀ መዛሙርትን ከላከበት ሁኔታ ጋር በተያያዘ ስለ መሆኑ ጥቂት ማስረጃዎች አሉ ቁጥር 5 ወደ አሕዛብ እንዳይሄዱ ያዝዛል:: ቁጥር 18 ግን ለአሕዛብ እንኳ እንደሚመሰክሩ ይናገራል:: እንግዲህ የኢየሱስ አነጋገር እርስ በርሱ ይጋጫል ካልተባለ ደቀ መዛሙርትን ስለ መላክ የቀረበውን ንግግር ማቴዎስ ያሰባሰበው ከዚያ በኋላ ኢየሱስ ካቀረበው ትምህርት ነበር ማለት ነው:: በሉቃስ መካከል ያለውን ልዩነት በተመለከተ እጥር ምጥን ያለ ሐተታ አቅርቧል::

[50] Carson contains an excellent synopsis of the issues involved in the differences between Matthew and Luke in *The Sermon on the Mount*, pp. 139-149.

ለተወሰኑ ሰዓታት ያህል ከነበረ ከተካተተው ይልቅ ሳይካተት የቀረው ይበዛል ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ኢየሱስ ያስተማረው አራማይክ ከሆነ (እንደዚያ እንደሚሆን ይታሰቦል) በማቴዎስና በሉቃስ መካከል ላለው መጠነኛ ልዩነት ተጠያቂው ወደ ግሪክ የተረጐመው ሰው ነው ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም በመካከላቸው ላለው ልዩነት እንደ ምክንያት ሊቀርብ የሚችለው ሁሌም ቢሆን ወንጌላውያኑ የሚያቀርቡት ቅደም ተከተላዊ የሕይወት ታሪክን ሳይሆን ሁኔታዎችንና አባባሎችን አጉልቶ ማሳየት የሚያስችላቸውን ነገር መለኮታዊ እውነትን በመተረክ ነው፡፡ በመጀመሪያው መቶ ዓመት ይህ አሠራር ያልተለመደ አልነበረም፡፡ ታማኝነትን እንደማጉደል ወይም ታሪካዊ ሐቅን እንደ ማፋለስ አይታይም ነበር፡፡

በመጨረሻም፣ ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን የነበረው የመማሪያ መንገድ የሚሰጠውን ትምህርት በቃል ማጥናት ነበር፡፡ ለምሳሌ ያህል የአይሁድ መምህራን አምስቱንም የሙሴ መጻሕፍትና ቃል በቃል ይተላለፉ የነበሩ ትውፊቶችን በቃላቸው ይይዙ ነበር፡፡ ስለሆነም የሁለት የተለያዩ ስብከቶችን ዋና ዋና ነጥቦች፣ በተለይም ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሲታከልበት ጨርሶ የማይታሰብ ሊሆን አይችልም ማለት ነው (ዮሐ 14÷16)፡፡

**§ 54ሀ**
**የስብከቱ መቼት**
**(ማቴ 5÷1-2፤ ሉቃ 6÷17-19)**

ይህ ስብከት ሦስት ነገሮችን ይመለከታል፤ እነርሱም ሕግ (5÷17-48)፣ ሃይማኖተኝነት (6÷1-18) እና ማኅበረሰብ፣ (6÷19-7÷12)፡፡ ዴቪስና ኤሊሰን እንደሚያመለክቱት፣ «ይህ ዓለም በሦስት ነገሮች ላይ ጸንቶ ቆሟል፤ እነርሱም የሕጉ መጻሕፍት (ቶራ)፣ የመቅደሱ አገልግሎትና «መልካም ምግባር»[51] ናቸው» በማለት ስምዖን የተባለው ሰው ከተናገረው ዝነኛ አባባል ጋር በሚያስደንቅ ሁኔታ

[51] D.C. Allison, “The Structures of the Sermon on the Mount,” *JBL 106/3 (1987): 423-445.*



ይስማማል፡፡ በተራራው ስብከት ውስጥ የተካተቱት እነዚህ ሦስት የአይሁዳዊነት ዐምዶች የመንግሥቱ መሠረትም ሆነዋል፡፡

ማቴዎስ የኢየሱስን ስብከት፣ «ንስሐ ግቡ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና» በሚል አጭር ዐረፍተ ነገር በማጠቃለል አቅርቧል (4÷17፣23)፡፡ የተራራው ስብከት ደግሞ ያንን በአጭሩ ቀርቦ የነበረውን ስብከት ይበልጥ ያብራራል፡፡ የተለወጠ ሕይወት ይኖረን ዘንድ የቀረበ ጥሪ ነው፡፡ ስቶት እንደሚለው አቻ ክርስቲያናዊ ባሕል ነው፡፡[52] እንዲያውም ስቶት እንደሚለው ማቴዎስ 6÷8 (ዘሌ 18÷3 ጋር ያነ) ይህን ስብከት ለመረዳት የሚያስችል ቁልፍ ነው፤ «እነርሱን አትምሰሏቸው» የመንግሥቱ ዜጎች ትክክለኛ መመሪያን ችላ በሚል ዓለማዊ መንግሥት መካከል ሲኖሩ ምግባርና ዝንባሌያቸው ምን መምሰል እንዳለበት ተገቢ ግንዛቤ ያስጨብጣል፡፡

| | |
|---|---|
| **ማቴ 5÷1-2**<br>**ሉቃ 6÷17 ጋር** | [1]ብዙ ሕዝብ እንደ ተሰበሰበ ባየ ጊዜ፣ ወደ ተራራ ወጣና ተቀመጠ፤ ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ መጡ፡፡ [2]እንዲህም እያለ ያስተምራቸው ጀመር፤ |

ኢየሱስ ወደ ተራራው መሄድ ነበረበት፡፡[53] ሕዝቡ በጣም በዝቶ ስለ ነበር ሰፈር ውስጥ መቆየት አልቻለም፡፡ ኢየሱስ «የምሥራቹን ቃል» መስበክ ብቻ ሳይሆን ደዌያቸውንም እየፈወሰ ነበር (ማቴ 4÷23)፡፡ ከዚህም የተነሣ ዝናው በጣም ተስፋፍቶ ስለ ነበር ከሶሪያ፣ ከገሊላ፣ ከዐሥሩ ከተሞች፣ ከኢየሩሳሌም፣ ከይሁዳና ከዮርዳኖስ ማዶ ካሉ አገሮች

[52] John Stott *Christian Counter-Culture* (Downers Grove, IL: InterVarsity, 1978).

[53] በማቴዎስ ወንጌል፣ «ተራራ» ብዙውን ጊዜ አዲስ መገለጥ ከተገኘበት ቦታ ጋር ተያይዞ ነው የቀረበው (ማቴ 4÷8 የኢየሱስን መፈተን፣ 17÷1 መለወጡ፣ 21÷1 በድል መግባቱ፣ 24÷3 የደብረ ዘይት ትምህርት፣ 28÷16 ታላቁ ተልዕኮ)፡፡ Cf. A.A. Trites, "The Blessings and Warnings of the Kingdom," *Rev & Expos* 89/2 (1992): 179-196.

ሁሉ ሰዎች ወደ እርሱ ይመጡ ነበር (ማቴ 4÷24-25፤ ሉቃ 6÷17-19):: ቃሬዛና ምርኩዞች፣ አጋንንት ያደሩባቸውና ሽባዎች፣ ሰውነታቸው የተጥመለመለና በጣም የተጐዱ ሰዎች በዚያ ቦታ ነበሩ፤ ወደ ጌታ ለመቅረብ በሚያደርጉት ሙከራ አንዳንዶች እስኪደሙ ድረስ ይቆስሉ ነበር፤ ውሎ ያደረ ቁስላቸው ይላጥ ነበር:: ሉቃስ (6÷19) ኢየሱስን በመንካት ፈውስን ለማግኘት ምን ያህል ይጋፋ እንደ ነበር ይነግረናል::

በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ከሙሴ ጋር በሚገርም ሁኔታ ተመሳስሏል (ዘዳ 18÷15)::[54] ሙሴ ወደ ተራራ የወጣው ሕግ ለመቀበል ሲሆን፣ ኢየሱስም ወደ ተራራ ወጥቶ ሰብኳል:: እንደ ሙሴ ሁሉ ኢየሱስ የአዲሱ እስራኤል ታዳጊ ነበር፤ ይህ ስብከት ደግሞ የክርስቲያኖች የውል ሰነድ ነው::

ኢየሱስ ተራራው ላይ በተቀመጠ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ መጡ:: ኢየሱስ የተጠቀመው የአይሁድ መምህራን ከሚያስተምሩበት መንገድ አንዱን ነበር::[55] አንድ የአይሁድ መምህር ሲቀመጥ፣ መደበኛው ትምህርት ሊጀመር መሆኑን ለተማሪዎች

[54] D.C. Allison, “Jesus and Moses (|MT 5:1-2),” *ExpT* 97/7 (1987): 203-205 ላይ በዚህ ምንባብ ኢየሱስን ሙሴን በአራት መንገዶች እንዳንጸባረቀ አመልክቷል:: (1) ኢየሱስ መቀመጡ፣ ሙሴ በሲና ተራራ (ዘዳ 9÷9) መኖሩን [*yashab*] ያንጸባርቃል:: (2) ኢየሱስ ወደ ተራራ መሄዱ፣ ሕግን ለመቀበል ሙሴ ወደ ተራራው ስለ መውጣቱ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ዘፀ 34: 29 ከሚገልጽበት ሁኔታ ጋር ይስማማል:: (4) በማቴ 1-4 ያቀረበው የኢየሱስ ሕይወት፣ ሙሴና እስራኤል የየሩቅ ሕይወት ተጓዳኝ መሆኑን አመልክቷል:: በማቴዎስ ውስጥ ከሙሴ ጋር ተያያዥ ስለሆኑ ነገሮች ሁሉ፣ W.S. Baxter, "Mosaic Imagery In the Gospel of Matthew," *TrinJ* 20ns (1999): 69-83 ይመ::

[55] G.L. Stevens, "Understanding the Sermon on the Mount: Its Rabbinic and New Testament Context," *TheolEd* 46 (Fall 1992): 83-95 በተራራው ስብከቱ ኢየሱስ የተከተላቸው የአይሁድ መምህራን ማስተማሪያ ዘዴዎችን አቅርቧል፤ ምሳሌዎች (7÷24-27)፣ ዘይቤያዊ አነጋገር (5÷13-16፤ 7÷16-20)፣ ተቃርኖ (5÷17-44)፣ ሥነ አመክንዮ በተለይም ከትንሹ ወደ ትልቁ መሻገርን በተመለከተ (6÷28-30 የአነጋገር ለዛ (7÷4) ቅዱሳት መጻሕፍት (5÷27)፣ ትውፊት (6÷1-18)::



የሚያመለክትበት መንገድ ነበር:: ይህ ከድካም ማረፍን ሳይሆን፣ ትምህርት ሊጀመር እንደ ሆነ የሚያውጅ የደወል ድምፅ ነው::

**§ 54ለ**
**ብፁዓን**
**(ማቴ 5÷3-12፤**
**ሉቃ 6÷20-26)**

3(ወደ ደቀ መዛሙርቱም በመመልከት እንዲህ አለ፤[ሉቃ])
«በመንፈስ ድኾች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፤ መንግሥተ
ሰማይ (የእግዚአብሔር መንግሥት[ሉቃ]) የእነርሱ ናትና፤
4የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፤
መጽናናትን (ይሥቃሉና[ሉቃ]) ያገኛሉና::
5የዋሆች ብፁዓን ናቸው፤
ምድርን ይወርሳሉና::
6ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፤
ይጠግባሉና::
7ምሕረት የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው፤
ምሕረትን ያገኛሉና::
8ልባቸው ንጹሕ የሆነ ብፁዓን ናቸው፤
እግዚአብሔርን ያዩታልና::
9ሰላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤
የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉና::
10ስለ ጽድቅ ብለው የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፤
መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና
11«ሰዎች በእኔ ምክንያት ቢሰድቧችሁ፣ (ሲጠሏችሁ፣ ከመካከላቸው ሲለዩአችሁ[ሉቃ])
ቢያሳድዷችሁና ክፉን ሁሉ በሐሰት ቢያስወሩባችሁ፤ ብፁዓን ናችሁ:: 12በሰማያት
የምትቀበሉት ዋጋ ታላቅ ስለሆነ ደስ ይበላችሁ፤ (በዚያን ቀን ደስ ይበላችሁ፤
ፈንድቁም[ሉቃ]) ሐሤት አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን (የቀድሞ አባቶቻቸው[ሉቃ])
ነቢያት እንደዚሁ አሳደዋቸዋልና::

[24]ነገር ግን እናንተ ሀብታሞች ወዮላችሁ፤ መጽናናታችሁ አሁኑኑ ተቀብላችኋልና።

[25]እናንተ አሁን የጠገባችሁ ወዮላችሁ፤ ኋላ ትራባላችሁና። እናንተ አሁን የምትስቁ ወዮላችሁ፤ ኋላ ታዝናላችሁ፤ ታለቅሳላችሁም።

[26]ሰዎች ሁሉ ስለ እናንተ መልካም ሲናገሩላችሁ ወዮላችሁ፤ የቀድሞ አባቶቻቸው ለሐሰተኞች ነቢያት ያደረጉላቸው ይህንኑ ነበርና።

ሉቃ 6÷24-26

ስለ ብፁዓን የሚያወሳው ክፍል በዕንቁ የታጨቀ ከረጢት ያህል ነው፡፡ እያንዳንዱን ከመመልከታችን በፊት እንደ መንደርደሪያ እንዲሆን ጥቂት ግንዛቤዎችን መጨበጥ ይኖርብናል፡፡

## በማቴዎስና ሉቃስ ወንጌል
## ስለ ብፅዕና የቀረበው ንጽጽር

በመጀመሪያ ማቴዎስ ስለ ብፁዓን የሚዘረዝረውን ክፍል ያቀረበበት ስልት ከሉቃስ የተለየ ነው፡፡ ማቴዎስ ስምንት ቡራኬዎች አስፍሮአል፡፡ በአንጻሩ ግን ሉቃስ አራት ቡራኬዎችን ሲያቀርብ (ማቴ 5÷3፤ 6፣ 4 እና 11ን የመሳሰሉ) በተጨማሪም ማቴዎስ ውስጥ የማናገኛቸውን አራት ወዮታዎችን አስፍሯል፡፡ አራቱ ዋይታዎች የአራቱ በረከቶች ተቃራኒ ናቸው፡፡ በዚህ መንገድ ሉቃስ አጽንዖት የሚሰጠው የተጨቆኑቱ በሚመጣው መንግሥት የሚባረኩ ስለ መሆናቸው ነው፡፡ በአንጻሩ የዚህ ዓለም ዜጐች ጊዜያዊ በረከቶችን ተቀብለዋል፡፡ ወደ ፊት ከሚመጣው በረከት ይልቅ (መንፈሳዊ) ርካሽ በሆነው ነገር ረክተዋልና ወዮላቸው፡፡

ከፍ ያለ ግምት የሚሰጠው ልዩነት ግን ሉቃስ ብፅዕናን የሚያቀርበው በመንፈሳዊ ሳይሆን በቁሳዊ መልኩ መሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ማቴዎስ፣ «በመንፈስ ድኾች የሆኑ ብፁዓን ናቸው» ሲል፣ ሉቃስ



ግን «ድኾች ብፁዓን ናቸው»[56] ብቻ ነው የሚለው፡፡ «አሁን የሚራቡትን» እና «የሚያለቅሱትን»፣ «አሁን የጠገቡት» እና «የሚሥቁትን» በተመለከተም ተመሳሳይ ነው፡፡ ሉቃስ ሆን ብሎ ለድኾችና ለተጨቆኑት አጽንዖት መስጠቱ ሊያስገርመን አይገባም፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንዶች ማኅበረ ሰባዊ ወንጌልን [የሰውን መሻት ብቻ የሚያገለግል] ለማቅረብ ሉቃስን እንደ መድረክ ሊጠቀሙበት ይሞክራሉ፡፡ ረጋ ብለን ስንመረምር ግን ሐቁ ከዚህ የተለየ መሆኑን ነው የምንመለከተው፡፡ ድኾች ኤኮኖሚያዊ ዋስትና እንደሚኖራቸው ኢየሱስ ቃል መግባቱን አይደለም ሉቃስ የሚነግረን፡፡ ይልቁንም ቃል የተገባላቸው የእግዚአብሔር መንግሥት ነበር፡፡[57] እንዲህ ሲባል ግን ኢየሱስ ለድሆች ደንታ ቢስ ነበር ማለት አይደለም፡፡ እንዲያውም የመጣው ለድሆች ወንጌልን ለመስበክ ነበር (ሉቃ 4÷18)፡፡ ይሁን እንጂ ዋናው ትኩረቱ ይበልጥ የሚያስፈልጋቸው ነገር ላይ ያም የመንግሥቱ ዜጐች መሆን ላይ ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ ግን ሀብት ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዳይመጡ እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል ከማሰብ ይልቅ የመጨረሻው በረከት እንደ ሆነ ያስባሉ (ማቴ 19÷16-24)፡፡

[56] ይሁን እንጂ ሉቃስ፣ «ድሆች» ሲል መዝ 37 እና ኢሳ 61 ካለው ተቃራኒ በሆነ መልኩ፤ «ሃይማኖተኞች» ማለቱ ነው፡፡ ስለሆነም ማቴዎስም ሆነ ሉቃስ ያቀረቡት የብፁዓን ዝርዝር ይዘት መንፈሳዊ ነው ማለት ይቻላል በማለት ተመልክቷል፤ G.T. Meadors "The 'Poor' in the Beatitudes of Matthew and Luke," *GTJ* 6/2 (1985): 305-314).

[57] ይህ ኢየሱስ በወንጌል ካደረገው ጋር ይስማማል፤ (1) ድንጋዩን እንጀራ ማድረግ አለመፈለጉ (ሉቃ 4÷4)፣ (2) 5,000 ሰዎችን ከመገበ በኋላ ንጉሥ እንዲሆን አለመፈለጉ (ዮሐ 6÷15)፣ (3) ጲላጦስ ኢየሱስን ስለ መንግሥቱ በጠየቀው ጊዜ፣ «መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለም» በማለት መመለሱ (ዮሐ 18÷36)፡፡

## ስለ ብፅዕና የሚያወሳው ክፍል አቀማመጥ

በሁለተኛ ደረጃ ስለ ብፅዕና የሚያወሳው ክፍል አቀራረብ የምሳሌዎች ዐይነት ነው:: ያም ማለት አጭርና መልእክተ አዘል ሲሆኑ፣ የጋራ የሆነ ዐቢይ ሐሳብም አላቸው ማለት ነው:: እያንዳንዳቸው ሦስት ክፍሎች አሏቸው፤ (1) «ብፁዓን» የሚል ቃል ይዘዋል፤ (2) አንድ መለያ ነገርን ያቀርባሉ፤ (3) ለዚያ የሚገባውን በረከት ያቀርባሉ::

ሌላው ማቴዎስ የተጠቀመበት ስልት ደግሞ፣ ከመጀመሪያውና መጨረሻው ብፅዕና ጋር በማያያዝ (ቁ 3፣10) «መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና» የሚለውን በረከት ድጋሚ ማቅረቡ ነው:: ይህም ሁለት ነገሮችን ያመለክታል:: ቁጥር 11-12 ለስምንተኛውና ለመጨረሻው ብፅዕና የተሰጠ ማብራሪያ መሆኑን ያሳያል:: ከዚህ በላይ ግን ክፍሉን በሙሉ በአንድ የጋራ በሆነ ርዕሰ ጉዳይ፣ ያው በእግዚአብሔር መንግሥት ማጠቃለሉ ነው::

ይህን የጋራ ርዕሰ ጉዳይ፣ «የእግዚአብሔር መንግሥት አሠራር» በሚል ዐረፍተ ነገር መግለጽ ይቻል ይሆናል:: በዚህ ዓለም መንገድ መሠረት ድሆች የሚሰደዱ የሚያለቅሱ፣ የዋሆችና እንደ ዕድለ ቢሶች እንጂ እንደ ተባረኩ ሰዎች የሚቈጠሩ አይደሉም:: የመጨረሻ የሚባሉ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ሀብታሞች፣ ተደማጭና ባለ ሞገስ ሊሆኑ ይችላሉ (ማቴ 19÷30፤ 20÷16፤ ያዕ 4÷6፤ 1ጴጥ 5÷6፤ ምሳ 3÷34):: ከዚህም በላይ ከእኛ ውጪ የሆኑ ነገሮችን የሚያመለክቱ እነዚህ ተደራጊ ግሦች፣ በመለኮት አሠራር መሠረት፣ ከእኛ ቍጥጥር ውጪ እንዲሆኑ የተደረጉ ነገሮች እንደ ሆኑ መገንዘብ አለብን:: በሌላ አነጋገር በረከት መስጠት የሚችል እግዚአብሔር ነው፤ ስለሆነም፣ «ይጽናናሉ» የሚለውን፣ «እግዚአብሔር ያጽናናቸዋልና» በማለት ማንበብ እንችላለን::

እዚህ ላይ ግን አንድ ማሳሰቢያ እናቀርባለን:: እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች እውነት የሚሆኑት ከእግዚአብሔር መንግሥት እንጂ የግድ



ከማኅበረ ሰቡ አንጻር ላይሆን ይችላል:: ከዚህም በላይ ምሳሌዎቹ አጠቃላይ እውነት እንጂ፣ ፍጹምና ያላቸው ተስፋዎች አይደሉም:: ለምሳሌ ያህል የሚያለቅሱ ሁሉ በመንግሥቱ ይጽናናሉ:: እንዲህ ሲባል ግን ባለቀስን ቍጥር ወዲያውኑ የተሟላ መጽናናት ይኖረናል፤ ወይም ሁሌም እግዚአብሔርን እናየዋለን፤ ወይም ሁሌም ምሕረት እናገኛለን ማለት አይደለም:: እነዚህ ስምንት ተስፋዎች በተሟላ መልኩ ፍጻሜ የሚያገኙት በዘላለም እንጂ፣ የግድ በዚህ ዘመን ይሆናል ብለን መጠበቅ አይኖርብንም::

## ብፅዕናን በተግባር መተርጐም

በሦስተኛ ደረጃ ብፅዕናን አስመልክቶ የቀረበው ዝርዝር ስለ ስምንት የተለያዩ ዐይነት ሰዎች እያመለከተ አይደለም:: በሐሳብ ደረጃ ቢሆንም ስለ እያንዳንዱ የመንግሥቱ ዜጐች ነው የሚናገረው::[58] ሔንክሊ እንዲህ በማለት በሚገባ ገልጾታል፤ «ብፅዕናዎቹ በተናጠል ያሉ ምግባሮች አይደሉም፤ ይልቁንም ይበልጥ ወደ እግዚአብሔር በሚያቀርበን የንስሐ መንገድ የምናገኛቸው መንገድ ጠቋሚ ምልክቶች ናቸው::[59] ይህም ከስብከቱ ዐቢይ ሐሳብ ጋር በሚገባ ከመጣጣሙ ባሻገር ከመንግሥቱ ጋር በተያያዘ መልኩ ኢየሱስ ስለ ንስሐ ያቀረበውን መልእክት በሚገባ ይገልጸዋል::

በመጨረሻም፣ «ብፁዓን» («ማካሪየስ» (*Makarios*) የሚለው ቃል)፣ «የታደሉ» ወይም፣ «የተባረኩ» ወይም፣ «ደስተኞች» ተብሎ ሊወሰድ ይችላል:: እነዚህ ሰዎች እንኳን ደስ ያላችሁ መባል ያለባቸው ናቸው:: ይሁን እንጂ፣ ትክክለኛ ትርጉሙን ተለዋዋጭ ደስታን

---

[58] የመንግሥቱ ዜጋ በዚህ ዘመን ክርስቲያን ከማለት ጋር አንድ ነው:: ከተራራው ስብከት ጋር በተያያዘ ክርስቲያን የሚል ቃል መጠቀም ግን ያለ ቦታው ያለ ነገር ሊሆንብን ይችላል:: እንግዲህ ይህን ግንዛቤ ከጨበጥን ከዚህ በኋላ ሁለቱንም በማፈራረቅ እንጠቀምባቸዋልን::

[59] K. Hinckley, "The Journey to Freedom: A Fresh Look at the Beatitudes" *DJ* 9 (Jan 1989): 45-48.

ወደሚያመለክት ደረጃ ዝቅ እንዳናደርገው መጠንቀቅ ይኖርብናል:: ይህ ዐይነቱ ብፅዕና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን በማግኘት የምንለማመደው የከበረ መንፈሳዊ ይዞታ ነው:: ዓለም በሚያውቀው መልኩ በየጊዜው የሚለዋወጥ ደስታ ወይም በቁሳዊ ወይም ውጫዊ ሁኔታዎች የሚደገፍም አይደለም::

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ መልስ ማግኘት ይኖርበታል፤ ይህ ዐይነቱ ብፅዕና አሁን ወይስ ወደ ፊት የምንደርስበት ነው? እነዚህን ባሕርያት በሙላት የምንለማመደው በዘላለም ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት፣ «በሰዎች መካከል» (ከራእ 2÷13 ጋር ያነ) በምትኖርበት ጊዜ መሆኑ ጥርጥር የሌለበት ጉዳይ ነው:: ቁጥር 12 ይህንኑ ሐቅ ያመለክታል:: እንዲህ ሲባል ግን ከእነዚህ በረከቶች ምንም አንቀበልም ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግሥት አሁንም ቢሆን እውን በመሆኗ ነው:: ከዚህም በተረፈ ቁጥር 3 እና 10 የሚያመለክቱት የአሁን ጊዜ ግሥን እንጂ ገና ወደፊት የሚሆነውን አይደለም:: በየመካከሉ የምናገኛቸው የወደፊቱን የሚያመለክቱ ግሦች እንኳ የወደፊቱን ማመልከታቸውን ያህል ለአሁኑ ጊዜም ቢሆን አጽንዖት በመስጠት ያመለክታሉ:: ስለዚህም፣ «እነዚህ በረከቶች አሁን የምንለማመዳቸው ናቸው ወይስ ወደፊት የምንደርስባቸው?» በማለት ላነሣነው ጥያቄ መልሱ፣ «ሁለቱም» የሚል ይሆናል ማለት ነው::

ማቴዎስ ወዳቀረባቸው ብፅዕናዎች ስንመለስ የመጀመሪያዎቹ አራት በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ ከማለታችን ጋር የተያያዙ መሆናቸውን እንገነዘባለን:: የተቀሩት አራቱ ግን ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ግንኙነት የተነሣ ለሌሎች የምናሳያቸው የምሕረት ተግባሮችን ይመለከታሉ:: ስለዚህም የመጀመሪያዎቹ አራት ብፅዕናዎች አጽንዖት የሚሰጡት ከፍ ብሎ ላለው ሲሆን፣ የመጨረሻዎቹ አራት ግን እኵናችን ላሉት አጽንዖት ይሰጣሉ:: በዐሥሩ ትእዛዞችም ውስጥ ይህ ዐይነት ሁኔታ ይታያል::



## በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ ማለት

ማቴ 5÷3 [3]በመንፈስ ድኾች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፤ መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና::

በሁለት ምክንያቶች ይህ የተራራው ስብከት ተገቢ ማስተዋወቂያ ነው:: በመጀመሪያ የኢየሱስን ዐቢይ ጭብጥ፣ ያም የእግዚአብሔርን መንግሥት ያስተዋውቃል:: አድማጮቹ ብዙም ሳይቆዩ በነበራቸው የእግዚአብሔር መንግሥት ግንዛቤና ኢየሱስ በሚያቀርብበት መንገድ መካከል ስላለው ሰፊ ልዩነት ሊረዱ ነው:: ሁለተኛ፣ ይህ የመጀመሪያው ብፅዕና የኢየሱስን አድማጮች በሁለት ምድብ ይከፍላቸዋል:: ጥቂቶቹ መንግሥቱን የሚቀበሉት ቀድሞ ይጠብቁት የነበረውን የሚያሟላ ሆኖ እስካገኙት ድረስ ነው:: ይሁን እንጂ፣ ለዚህ ዜግነት ብቁ የሚሆኑት መንፈሳዊ ባዶነታቸውን የሚገነዘቡ ብቻ ናቸው:: ስለሆነም ይህ የመጀመሪያ ብፅዕና ጠቅላላውን ስብከት አሟልቶ ይዟል ማለት ይቻላል::

«በመንፈስ ድኻ» የመሆን ነገረ መለኮታዊ ግንዛቤ ብሉይ ኪዳንን መሠረት ያደረገ ሲሆን፣ አዲስ ኪዳንም በዚሁ ግንዛቤ የታጨቀ ነው:: አይሁዳውያን በተከታታይ የደረሰባቸው ጭቆና ከቁሳዊ ንብረት አንጻር ድኾች አድርጓቸው ነበር፤ ይህም ረድዔትና ጽናት ይሰጣቸው ዘንድ ተስፋቸውን ሁሉ እግዚአብሔር ላይ እንዲያደርጉ ምክንያት ሆኗል:: ስለሆነም ድኽነታቸው ይበልጥ ሃይማኖታቸውን እንዲያጠብቁ፣ በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ እንዲሉ፣ ልባቸው የተሰበረ እንዲሆኑና በእርሱም እንዲደገፉ ያደርጋቸው ነበር:: ለምሳሌ መዝመር 34÷6፣ «ይህ ችግረኛ ጮኸ፤ እግዚአብሔርም ሰማው፤ ከመከራውም ሁሉ አዳነው» ይላል:: ምሳሌ 16÷19፣ «በተዋረደ መንፈስ ከተጨቆኑት ጋር መሆን፣ ከትዕቢተኞች ጋር ብዝበዛን ከመካፈል ይሻላል» ይላል:: ምናልባትም ለዚህ ብፅዕና መሠረት ሊሆን እንደሚችል የሚታሰበው

ኢሳይያስ 61÷1-2 ደግሞ፣ የመሲሑ አገልግሎት በተለይ ድኾችና ችግረኞችን የሚነካ እንደሚሆን ያመለክታል::[60] ባደገበት ከተማ በነበረው ምኩራብ ኢየሱስ ይህ ክፍል እርሱን የሚመለከት መሆኑን ተናግሮአል (ሉቃ 4÷18)

[4]የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው መጽናናትን ያገኛሉና:: ማቴ 5÷4

እዚህ ላይ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ወዳጆቻችን በሞት ሲለዩን ስለሚደርስብን ሐዘን ሳይሆን፣ ከንስሐ ጋር ስለተያያዘ ሐዘን ነው:: ኢየሱስ መጽናኛ መሆኑ እውነት ነው (ኢሳ 40÷1)፤ ልባቸው የተሰበረውን ይጠግናል (ኢሳ 61÷1)፤ ሆኖም፣ የዚህ ክፍል ሐሳብ ግን ይህ አይደለም:: በቁጥር 3 መሠረት ድኽነታችንን መገንዘባችንን ተከትሎ ቁጥር 4 መጀመሪያውኑ ለዚያ ድኽነት ምክንያት ከሆነ ነገር ንስሐ ማድረግ እንደሚገባ ያመለክታል:: እንዲህ ያለ የንስሐ ሐዘን ታላቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል (2ቆሮ 7÷8-13)::

ታዲያ፣ ሐዘናችን የታል? በኀጢአታቸው የሚያለቅሱ ስንቶች ናቸው? ስለ ሕዝባቸው ኀጢአት ስላለቀሱ ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ምሳሌዎች ማቅረብ ይቻላል፤ (መዝ 119÷136፤ ሕዝ 9÷4፤ ማቴ 23÷37፤ ፊልጵ 3÷18):: ብዙዎችም ስለ ራሳቸው ኀጢአት አልቅሰዋል (ሉቃ 5÷8፤ 7÷36-38፤ ሮሜ 7÷24፤ 1ቆሮ 5÷2፤ 2ቆሮ 12÷21):: ብዙ ጊዜ ግን የወንጌል አማኞች ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡት ለጸጋ በመሆኑ በኃጢአታቸው ሲያዝኑ የሚታየው በጣም በጥቂቱ ነው::

[5]የዋሆች ብፁዓን ናቸው፤ ምድርን ይወርሳሉና ማቴ 5÷5

[60] Cf. W.R. Domeris, “Biblical Perspectives on the Poor,” *JTSA* 57 (Dec. 1986): 57-61.



የዋህ ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል «ፕራየስ» (*Praus*) ሲሆን «ጨዋ፣ ደግ፣ አስተዋይ» የሚል ሐሳብም ይዟል:: ቃሉ ኢየሱስን የሚገልጽ ነው (ማቴ 11÷29፤ 2ቆሮ 10÷1):: ይህ ቃል በጌቶቻቸው ቁጥጥር ሥር እንዲሆኑ በልጓም የተሸበቡ የጦር ሜዳ ፈረሶችን ለማመልከት ጥቅም ላይ ቢውልም፣ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ብርቱ ስለሆኑ፣ ሆኖም ይህን ብርታታቸውን በጨዋነት መግለጽ ስላልቻሉ ሰዎች እንደ ሆነ ማሰብ የለብንም:: ቃሉ የሚያመለክተው የጦር ሜዳ ፈረስን ሳይሆን ልጓምን፣ ያም መገዛትን ነው:: የዋሆች በሌሎች ቁጥጥር ሥር ያሉ ናቸው:: በመንፈስ ድኾች የሚለው የሚያመለክተው ባዶነታችንን መገንዘባችንን ሲሆን፣ «የዋህ» የሚለው የሚያመለክተው ግን ከዚያ ትሕትና ወይም ባዶነት አንጻር ማንነታችን ስለሚገለጥበት ሁኔታ ወይም ማኅበረሰቡ ውስጥ ስላለን ስፍራ ነው:: አዲስ ኪዳን ስለዚህ ባሕርይ ብዙ የሚለው አለው (2ቆሮ 10÷1፤ ገላ 5÷22፤ ቈላ 3÷12፤ 1ጴጥ 3÷15፤ ያዕ 1÷19-21)::

ስለሆነም የዋሃን ምድርን ይወርሳሉ ማለት በዚህ ቁሳዊና የራሱን ጥቅም በሚያሳድድ ማኅበረሰብ ውስጥ መሳቂያ መሆን ነው:: ታዲያ፣ ይህ እውን ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች እንደ መሆናችን መጠን የኋላ ኋላ ክርስቲያኖች ሁሉን መውረሳቸው እውነት ነው (ሮሜ 8÷17):: አዲሲቱን ምድርን እንወርሳለን:: እውነቱን ለመናገር ከዚህ ዐውድ አንጻር ይህ በጣም «የተጋነነ» ይመስላል:: ምድርን እንወርሳለን ሲል አሁን ያለችውን ምድር ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ይቻላል:: ሁለተኛ ቆሮንቶስ 6÷10 በክርስቶስ ሁሉን እንደምንወርስ ይናገራል:: እርግጥ ነው ሰይጣን ይህን ዓለም እየገዛ ነው (ኤፌ 6÷12)፤ ይሁን እንጂ የሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑ ግልጽ ነው:: ልጆቹ እንደ መሆናችን መጠን በመንፈሳዊ መልኩ እኛም የዚህ ዓለም ባለቤቶች ነን:: ምናልባትም

ከዚያም አልፎ ቃል በቃል መወሰድ በሚችል መልኩ መናገሩም ሊሆን ይችላል። ይህ ክፍል ከመዝሙር 37÷11 የተጠቀሰ መሆኑ ግልጽ ነው። ምንም እንኳ ፍጹም እውነት ባይሆንም፣ በአጠቃላይ መርሕ ደረጃ ክፉዎች መጥፋታቸውና የራሳቸውን ብቻ ፈላጊ ሰዎች የማይታመኑ መሆናቸው አሁንም ቢሆን የሚካድ አይደለም። ስለ ሌሎች የሚያስቡ፣ ታማኞችና ራሳቸውን በመግዛት የሚኖሩ ግን ለኀላፊነት ይበቃሉ። በእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ ሳይሆን፣ በዚህ በአሁኑ ዓለምም ጭምር ቃል በቃል መወሰድ የሚችሉ እውነቶች በዚህ በረከት ውስጥ ተካትተዋል።

[6]ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው ይጠግባሉና። ማቴ 5÷6

ወደ ሐዋርያቱ መልእክቶች ስንመጣ፣ «ጽድቅ» የሚለው ቃል ኢየሱስ መስቀል ላይ ከፈጸመው የተነሣ ከእግዚአብሔር የምንቀበለውን የሚያመለክት ቃል መሆኑን እንመለከታለን። በሌላ አነጋገር ለኀጢአታችን የሚገባው ዋጋ በመከፈሉ እግዚአብሔር እንደ ጽድቅ ይቆጥርልናል ማለት ነው። ይሁን እንጂ በዚያ ገለጻ የምንጠቀምበት ጊዜ ገና ነው። እዚህ ላይ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ጽድቅ፣ ግብረ ገባዊ ንጽሕናንና (ቁ 10-20) ትክክለኛ ዝንባሌን የሚመለከት ነው (ቁ21-40)። ምናልባትም ይህ ኢሳይያስ 55÷1 እና መዝሙር 42÷1-2 ላይ ያለውን የሚያንጸባርቅ ሊሆን ይችላል። ጽድቅን የሚራቡ የሚበለጽጉት ከራሱ ከእግዚአብሔር በሚቀበሉት ሽልማት ነው። ስለሆነም መሠረታዊ ሐሳቡ፣ ከምንም ነገር ይልቅ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ለመኖር እየናፈቃችሁ ነውን? እንደዚያ ከሆነ እግዚአብሔር የናፈቃችሁትን ይሰጣችኋል የሚል ነው።

ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ በጣም ጥቂት ክርስቲያኖች ብቻ መሆናቸው የሚያሳዝን ነው። ጥሩ ራት ቢዘጋጅላቸውም፣ በከረሜላና



ሌሎች ጣፋጭ ነገሮች የመብላት ፍላጐታቸውን ያጡ ሕፃናትን እንመስላለን። በታዋቂነታችን፣ በሥራ እንቅስቃሴያችን፣ በምናዘወትረው መዝናኛና ስሜቶቻችንን በሚያነቃቁ ነገሮች ረክተን ተቀምጠናል። በእንዲህ ዐይነት ነገሮች በመሞላታችን ከዚህ ጥልቅ ረሃብና መሻት ተዘናግተናል። ከዚህም የተነሣ በማኅበረሰባችን ለውጥ ማምጣት አልቻልንም። ጨው አልሆንንም፤ ብርሃንም አልሆንም (ቁ 13-16)፤ ይልቁንም ይህን የሚተካልን እየመሰለን በሌሎች ማኅበራዊ ጉዳዮች ተጠምደናል።

በእውነት ጽድቅን መራብና መጠማት ማለት የማያቋርጥ መሻት ወይም ፍላጐት ማለት ነው። ምግብ ስንበላ የምንጠግበው ለጊዜው ነው፤ ከጥቂት ሰዓት በኋላ እንደ ገና እንራባለን። ጽድቅን መሻት ወይም መናፈቅም እንዲህ ነው። እግዚአብሔርን ወደ መምሰል በምናደርገው ግሥጋሤ እርካታ ቢኖረንም፣ ይበልጥ ወደፊት እንድንራመድ መንፈስ ቅዱስ ልባችን ውስጥ መሻት ያኖራል። ጽድቅን መራብና መጠማት በመንፈስ ድኾች መሆንን፣ ከኀጢአት ማዘንና በእግዚአብሔርም ሆነ በሰዎች ፊት የዋሃን ሆኖ መገኘትን መሠረት ያደረገ ነው።

## ለሰዎች ምሕረት ማድረግ

[7]ምሕረትን የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው ምሕረትን ያገኛሉና። ማቴ 5÷7

ኢየሱስ ይቅር ለማለት ፈቃደኛ ባልነበረው አገልጋይ ምሳሌ (ማቴ 18÷21-35) እና በሐዋርያት ጸሎት ይህን ብፅዕና በሚገባ አብራርቶታል። ያስቀመጠው መርሕ ማንም በቀላሉ የሚረዳው ሲሆን፣ ይኸውም እግዚአብሔር እኛን የሚያስተናግደን ሌሎችን ባስተናገድንበት ሁኔታ ነው የሚል ነው (ማቴ 10 ÷ 32-33፤ 25÷40 ጋር ያነ)። እነዚህ ጉዳዮች ጸጋን ብቻ እንጂ የእኛን ልፋት ውጤት አያመለክቱም።

ክርስቲያን ለሌሎች ምሕረት የሚያደርገው፣ እርሱ ራሱ ምን ያህል ምሕረት እንደ ተቀበለ በመረዳቱ ነው:: እኛ ራሳችን ስለ ተወደድን ሌሎችን እንወዳለን፤ እኛ ራሳችን ይቅር ስለ ተባልን ሌሎችን ይቅር እንላለን:: ለሌሎች ምሕረት ለማድረግ አለመፈለጋችን የሚያሳየው እግዚአብሔር ለእኛ ያሳየውን ምሕረት በሚገባ አለማጣጣማችን ወይም የተደረገልንን ምሕረት አድናቂ አለመሆናችንን ነው:: ይህን አስመልክቶ ነበር ጳውሎስ፣ «እንግዲህ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሆን ዘንድ ክርስቶስ እንደ ተቀበላችሁ፣ እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ» ያለው (ሮሜ 15÷7)::

8 ልባቸው ንጹሕ የሆነ ብፁዓን ናቸው፤ **ማቴ 5÷8**
እግዚአብሔርን ያዩታልና::

«ልበ ንጹሐን» የሚለው ቢያንስ ሁለት ተጨማሪ ትርጉሞች አሉት፤ እነዚያም ንጽሕናና ቅንነት ናቸው:: የፈሪሳውያን ትኩረት ውጫዊ ንጽሕና ላይ ብቻ ነበር (ማቴ 23÷23-27 ጋር ያነ):: በውጭ በኩል ሲታዩ መልካም ይመስላሉ፤ ውስጣቸው ግን መጥፎ ሽታ ነበር:: ኢየሱስ እንዲህ ያለውን ጠባብ ሃይማኖተኝነት በጣም ነበር ያወገዘው:: ንጽሕናችን ልቦናችንን ጠልቆ እንዲዘልቅ ይፈልጋል:: ይህ ደግሞ ከብሉይ ኪዳን የተላለፈ ሐሳብ ነበር፤ «ወደ እግዚአብሔር ተራራ ማን ሊወጣ ይችላል? በተቀደሰ ስፍራውስ ማን ይቆማል? ንጹሕ እጅና ቅን ልብ ያለው፣ ነፍሱን ለሐሰት የማያስገዛ» ሲል ብሉይ ኪዳን እንኳ ይህን እንደሚገነዘብ ማየት ይቻላል (መዝ 24÷3-4)::

ሁለተኛው ተጨማሪ ትርጉም ቅንነት ነው:: ኢየሱስ፣ «ያልተሸቃቀጠ» ልብ ይፈልጋል:: ለምሳሌ ያህል በማቴዎስ 6÷22-24 ላይ ኢየሱስ፣ «ዐይን የሰውነት መብራት ነው፤ ስለዚህ ዐይንህ ጤናማ ከሆነ መላው ሰውነትህ በብርሃን የተሞላ ይሆናል ... አንድ ሰው ሁለት ጌቶችን ማገልገል አይችልም» ብሏል:: እግዚአብሔር ባልተከፋፈለ ሁኔታ



ለእርሱ እንድንገዛ ይጠብቀብናል:: ስለዚህም እግዚአብሔርን እንድናይ ከተፈለገ ንጹሕ ልብ፣ ያም የጸዳና ቅን ልብ ሊኖረን ይገባል ማለት ነው:: እንዲህ ሲባል ግን እግዚአብሔርን ማየት የሚያስችለንን ይለፍ አግኝተናል ማለት ሳይሆን፣ የመንፈሳዊ ዐይኖቻችንን ጉድፍ እንድናጠራ የቀረበ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን መገንዘብ አለብን:: እግዚአብሔር ከእኛ የተደበቀ አይደለም:: ዐይኖቻችን ተጋርደዋል፤ ልባችንን በማንጻት ይህ ግርዶሽ የፈጠረብን ነገር መወገድ አለበት::

9 ሰላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤
**ማቴ 5÷9** የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉና::

«የእግዚአብሔር ልጆች»፣ መሆን ብቻ ሳይሆን ባሕርይንም ይመለከታል:: ኢየሱስ በዚህ ምድር ባስተማረበት ዘመን አንድን ሰው የውሻ ልጅ ብሎ መጥራት ባሕርዩ እንደ ውሻ መሆኑን ያመለክት ነበር:: የዲያብሎስ ልጅ ነው ማለትም እንዲሁ፣ ተግባሩ እንደ ዲያብሎስ ነው ማለት ነበር:: በተመሳሳይ መልኩ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ሲባል ተግባሩ እንደ እግዚአብሔር ነው ማለት ነበር::

እግዚአብሔር ሰላምን የሚያወርድ ነው:: ይህ ደግሞ ነገረ መለኮታዊ ፋይዳ ያለው ነው (ከኤፌ 2÷11-22 ጋር ያነ):: የሰው ልጅን ከራሱ ጋር፣ አይሁድን ከአሕዛብ ጋር፣ ወንዶችን ከሴቶች ጋር፣ ወዘተ አስታረቀ:: የእግዚአብሔር አርአያ በመከተል እኛም ሰላም አድራጊዎች መሆን አለብን:: ተቀዳሚ አገልግሎታችን ይኸው መሆን አለበት (2ቆሮ 5÷18-20):: ይህም ሰላምን ከመፈለግ፣ ወይም የሰላም ሰው ከመሆን አልፎ ሰላም ወዳድ ሕዝብ መሆንን ይጠይቃል:: በዚህ በተመሰቃቀለ ዓለም የሰላም መሣሪያዎች መሆን አለብን::

ችግሩ የሚነሣው በጥላቻ ከተሞላው ዓለም ጋር ፊት ለፊት ስንጋፈጥ ነው (ቁ 10-12፣39-45):: በግልጽ ለማስቀመጥ ይህ ዓለም

ክርስቲያኖችን መቀበል አይፈልግም። በሌሎች መካከል በተፈጠረ አለመግባባት ሰላም ማድረግ ደስ ቢለንም ሰላምን ለማምጣት ሲባል ሌላውን ጉንጫችንን ማዞር ግን አንፈልገውም። ነገሩን የከፋ የሚያደርገው ደግሞ ኢየሱስ የጥላቻ ዒላማ ስለ ነበር፣ እርሱ ባለበት ሁሉ ተቃውሞ መነሣቱ ነው። ሌላው ቀርቶ በእርሱ ምክንያት የሰይፍን ያህል በሚቆርጥ ጉዳይ ቤተ ሰቦች እንኳ ሊከፋፈሉ ይችላሉ (ማቴ 10÷34-37)። ይህ ማለት ግን የኢየሱስ የመሆናችንን አቋም ማወላወል አለብን ማለት ሳይሆን፣ በሚቻለን ሁሉ በጥንቃቄ ማድመጥን፣ ለስለስ ባለ ሁኔታ መናገርን፣ የግል ጥቅምን ገሸሽ ማድረግን፣ ብንበደል እንኳ አለመቀበልን፣ ከበደልናቸው ይቅርታ መጠየቅን፣ ነገሮች ቢካረሩ እንኳ ፈገግተኛ መሆንን፣ ሌሎችን ማስቀደምንና ሌሎችን ይጨምራል። ሰላም አድራጊዎች ስንሆን ሰዎች የእግዚአብሔርን ባሕርይ እያንጸባረቅን መሆኑን ይገነዘባሉ።

[10]ስለ ጽድቅ ብለው የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፤ መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና። [11]ሰዎች በእኔ ምክንያት ቢሰድቧችሁ፣ ቢያሳድዷችሁና ክፉን ሁሉ በሐሰት ቢያስወሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። [12]በሰማይ የምትቀበሉት ዋጋ ታላቅ ስለሆነ ደስ ይበላችሁ፤ ሐሤት አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያት እንደዚሁ አሳደዋቸዋልና።

**ማቴ 5÷10-12**

ሰላም አድራጊዎች ስደት ሊደርስባቸው ይችላል። ለምን? ምክንያቱም መንገዳችን ከዚህ ዓለም ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ነው። አንጉል ቀልዶች አያስቁንም፣ ክፉ ነገርን አንደግፍም፣ ግብር አናጭበረብርም፣ ከውሸት ጋር አንስማማም፤ ይህ ሁሉ ግን በዙሪያችን ያሉትን ሊያበሳጫቸው ይችላል። በዓለማዊ ሰዎች ውስጥ ፍርሃትና



የበደለኝነት ስሜት እንዲፈጠር ስለሚያደርግ ክርስቲያኖችን ለማሳደድ ያነሳሣቸዋል።

እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ክርስቲያን ብፁዕ የሚሆነው በራሱ ጥፋት ወይም ዝርክርክነት በሚነሣበት ስደት ሁሉ ሳይሆን በጽድቅ ምክንያት በሚነሣበት ስደት መሆኑን ነው። የዋህነት፣ ንጽሕናና ሰላም አድራጊነት የክርስቲያን ምልክቶች እንደ ሆኑ ሁሉ ስደትም እንዲሁ የክርስቲያን ምልክት ነው። በሌላ አነጋገር ክርስቶስን እስከ ተከተልን ድረስ ስደትንም መጠበቅ አለብን ማለት ነው (ዮሐ 15÷18-21፤ 1ጴጥ 4÷13-14፤ ሐሥ 14÷22፤ 2ጢሞ 3÷12)። ያ ካልሆነ ግን በእውነት በጽድቅ እየኖርን መሆናችንን መጠየቅ ይኖርብናል። እንዲያውም ሉቃስ፣ «ሰዎች ሁሉ ስለ እናንተ መልካም ሲናገሩላችሁ ወዮላችሁ» ሲል እየተናገረ ያለው የዚህን ተቃራኒ እንደ ነበር መረዳት ይቻላል።

ቁጥር 11-12 ይህን የመጨረሻ ብፅዕና በተለያዩ መንገዶች ይበልጥ ያብራራዋል። በመጀመሪያ ኢየሱስ፣ «ብፁዓን ናችሁ ...» ሲል ነገሩን ወደ ግለሰብ ደረጃ አጥብቦታል። ሁለተኛ ኢየሱስ የተናገረው ያለው ስለ አካላዊ ስደት ብቻ ሳይሆን፣ ስለ ስድብና ስም ማጥፋት ጭምር መሆኑን ግልጽ አድርጓል። ሦስተኛ ምላሻችን ምን መሆን እንዳለበት ተናግሯል፣ «በሰማይ የምትቀበሉት ዋጋ ታላቅ ስለ ሆነ ደስ ይበላችሁ፤ ሐሤት አድርጉ» («ፈንድቁም» ሉቃ 6÷23)። መሰደድ የሚያስገኘውን በረከት አሁን ማየት ባንችልም የኋላ ኋላ ግን እናያለን። ጳውሎስ እንደሚለው፣ «ቀላልና ጊዜያዊ የሆነው መከራችን ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊ ክብር ያስገኝልናል» (2ቆሮ 4÷17)። አራተኛ፣ «ስለ ጽድቅ» የሚለውን፣ «በእኔ ምክንያት» በሚል በመተካቱ ኢየሱስ አብራርቶታል። የሚጠቅም ውጤት ያለው ስደት ሊነሣብን የሚገባው አቋማችን ከኢየሱስ ጋር በመሆኑ እንጂ በማኅበረሰባዊ ሃይማኖት ተሳትፎአችን ምክንያት መሆን የለበትም።

ለሚነሳብን ስደት የምንሰጠው ምላሽ እንደ ውሻ ቁስላችንን በመላስ መሆን የለበትም:: በሌላ በኩል ደግሞ ከጉዳታችን ወይም ከመቁሰላችን አንድ ዐይነት ደስታ እንደምናገኝ በማሰብ መሆን የለበትም:: ሕመምን ወይም ጉዳትን ጨክነን እንቀበላለን እንጂ ጉዳት መኖሩን በመካድ መሆን የለበትም:: ስደት በሚያመጣው በረከት ደስ ይለኛል:: ይህ በረከት ምንድነው? (1) ወደፊት ስለሚጠብቀን ሽልማት ቀደም ሲል ተመልክተናል (ቁ 12፤ 2ቆሮ 4÷17)፤ (2) እምነትና ምግባርን ያንጻል (1ጴጥ 1÷6):: (3) የእምነታችንን እውነተኛነት ያረጋግጣል (ቁ 12ለ፤ ሐሥ 5÷41)::

ይህ የኢየሱስ ስብከት መገለጫ ነው:: ግለኝነትን፣ በራሳችን ብርቱ መሆንን፣ ዕብሪትንና በራሳችን ስኬታማ የመሆንን ፍላጐት በነበረበት ዘመንም ሆነ በዚህ ባለንበት ዘመን ፊት ለፊት ተቃውሞታል:: የእግዚአብሔር መንግሥት የምትስፋፋው፣ ይህን ዓለም በመቋቋም ነው:: በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የአድማጮቹን ትኩረት ሙሉ በሙሉ ሳይስብ እንዳልቀረ ማሰብ ይቻላል::

§ 54ሐ
ጨውና ብርሃን
(ማቴ 5÷13-16
ሉቃ 14÷35)

[13]እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው የጨውነት ጣዕሙን ቢያጣ ጣዕሙን መልሶ፣ ሊያገኝ ይችላልን? ወደ ውጪ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ጥቅም አይኖረውም (ለመሬትም ሆነ ለማዳበሪያነት የማይጠቅም በመሆኑ ወደ ውጭ ይጣላል[ሉቃ])::

[14]እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፤ በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትደበቅ አትችልም፣ ሰዎችም መብራት አብርተው ከዕንቅብ ሥር አያስቀምጡትም፤ በቤት ውስጥ ላሉት ሁሉ እንዲያበራ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጡታል እንጂ:: [16]እንደዚሁም ሰዎች ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰዎች ፊት ይብራ::



ብፅዕናዎቹ ክርስቲያን ምን መሆን እንዳለበት ይናገራሉ:: ምናልባትም የመንግሥቱ ዜጐች ገዳም ውስጥ ያሉና፣ በጸጥታና በገለልተኝነት የሚኖሩ ጥቂት ሰላም ወዳድ ሰዎች ብቻ ሊሆኑ እንደሚችሉ እናስብ ይሆናል:: ትሑት ከሆነውና ለሌሎች መገዛት ከሚችለው ባሕርያቸው የተነሣ ምናልባት በማኅበረሰቡ ላይ ያላቸው ተፅዕኖ እዚህ ግን የማይባል እንደሆነ ሊታሰብ ይችላል:: ኢየሱስ ግን እንዲህ ያለውን አስተሳሰብ አይቀበልም፤ መቀበል ቢከብደንም እንኳ እነዚህ ብፁዓን ዜጐች በዓለም ላይ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ::

ክርስቲያኖች ማምጣት የሚችሉትን ለውጥ ለማሳየት ኢየሱስ በማንኛውም አይሁድ ቤት በቀላሉ የሚገኙ ሁለት ነገሮችን እንደ ምሳሌ ተጠቅሟል፤ ጨውና መብራት:: ሁለቱም ምሳሌዎች በመንግሥቱ ዜጐችና በዚህ ዓለም ሰዎች መካከል ያለውን ንጽጽር ወይም ልዩነት ያመለክታሉ:: ይህ ልዩነት ሊሸቃቀጥ ወይም ሊድበሰበስ እንደሚችል ሁለቱም ምሳሌዎች ያሳያሉ:: እንዲህ ሲሆን ደግሞ ክርስቲያን በዚህ ዓለም ለውጥ ማምጣትም ሆነ ለዚህ ዓለም ጣዕም መሆን አይችልም::

ከዚህም በላይ ምንም እንኳ ጨውም ሆነ ብርሃን በጣም ጠቃሚ ቢሆኑም፣ ተቃራኒ ውጤት ሊያመጡ መቻላቸውንም ማመን ይኖርብናል:: በዚህ ስብከት መሠረት መኖር የሚፈልጉ ክርስቲያኖች ለስደት ዒላማ መሆናቸው ሊያስገርመን አይገባም::

***ጨው***

ጨው የተለያዩ ጥቅሞች አሉት፤[61] አራቱ ግን በጣም ወሳኝ ናቸው፣ (1) ምግብ እንዳይበላሽ ይረዳል፤ (2) መሥዋዕቱን ያጠራል (ዘሌ 2÷13)፤ (3) ያጣፍጣል፤ (4) ውሃ እንዲጠማን ያደርጋል:: ምንም

[61] W.D. Davies & D.C. Allison *Matthew*, The International Critical Commentary, Vol 1 (Edinburgh: T& T Clark 1988) ገጽ 472-473 ላይ ዐሥራ አንድ የጨው ጥቅሞችን ጠቁሟል:: ሰፋ ያለ መረጃ ለማግኘት፣ M. Kurlansky, *Salt: A World History* (New York: Wacker & Co, 2002) ይመ::

እንኳ የመጨረሻዎቹ ሁለቱ ከንግግር ማጣፈጫነት ያለፈ ነገር ባይኖራቸውም፣ ኢየሱስ አጽንዖት የሰጠው ለመጀመሪያው ወይም ለሁለተኛው ጠቀሜታ ሊሆን ይችላል፡፡ ምግብን ለረጅም ጊዜ ማቆየት የሚችሉ ማቀዝቀዣዎች በሌሉባቸው አገሮች ምግብ እንዳይበላሽ በማድረግ ረገድ ጨው ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው (በጨው የታሹ ምግቦች ድጋሚ ጨው አያስፈልጋቸውም)፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ክርስቲያኖች ግብረ ገባዊ ብልሽት እንዳይኖርና በማኅበረሰቡ ፍትሕ እንዲሰፍን የማኅበረሰቡ ሕሊና የመሆን ኀላፊነት አለባቸው፡፡ እግዚአብሔር መንግሥትንና ቤተሰብን የመሠረተው ለዚሁ ዓላማ ነበር፤ ይሁን እንጂ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ እነዚህ ነገሮች እንኳ ጨውና መብራት የመሆናቸውን እውነት ሊያጡ ይችላሉ፡፡ ከታሪክ እንደምንመለከተው ቤተ ክርስቲያን በሳይንስ፣ በሕክምና፣ የእስረኞችን አያያዝ በማሻሻል፣ ወላጅ አልባ ሕፃናትን በመንከባከብ፣ የባሪያ አሳዳሪ ሥርዐትን በማስወገድ፣ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛንና ማይምነትን በማስወገድ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ነበራት፡፡ በእርግጥም፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ይህን ዓለም በማጣፈጥ ረገድ በቻልታ የማይታለፍ አስተዋፅዖ ስታደርግ ኖራለች፡፡

ችግሩ የሚመጣው ጨው ጨውነቱን ሲያጣ ነው፡፡ በመሠረቱ ጨው (ሶዲየም ክሎራይድ) ጨውነቱን ማጣት ባይችልም፣ ከሌሎች ነገሮች ጋር ሊቀያየጥ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ያህል የሙት ባሕር አካባቢን የወሰድን እንደ ሆነ ውሃ ውስጥ ያለው ጨው ደርቆ ከሌሎች ንጥረ ነገሮችና ነጭ አፈር ጋር ተቀያይጧል፡፡ ምንም እንኳ ጨውነት ቢኖረውም፣ ምግብ እንዳይበላሽ የሚያደረግ ችሎታውን ግን አጥቷል፡፡ አንድ ጆንያ ሙሉ «ጨው» ብትገዙ አውጥታችሁ ከማፍሰስ ውጪ ለሌላ ለምንም አይጠቅማችሁም፡፡ ክርስቲያንን ለመግለጽ የተጠቀመበት ዘይቤ ግልጽ ነው፡፡ አንድ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ከተቀያየጠ ማኅበረሰቡ ውስጥ ለውጥ ማምጣት አይችልም፡፡



*ብርሃን*

ጨለማ ውስጥ ደብዛዛ መብራት እንኳ በቀላሉ ይለያል፡፡ ሊደብቀው የሚፈልግ ምን ዓይነት ሞኝ ነው? ብዙ ክርስቲያኖች ማንነታቸው እንዳይታወቅ ጥረት ሲያደርጉ ይታያል፡፡ ጨለማው ብርሃንን እንዳይውጠው ይሰጋሉ፡፡ ይህ ግን የማይቻል ነው፡፡ ኢየሱስ ብርሃን በመሆኑ፣ (ዮሐ 8÷12፤ 9÷5) እኛም በእርሱ በመሆናችን፣ እንደ ከዋክብት እናበራለን (ፊልጵ 2÷15)፡፡ እርሱ የዓለም ብርሃን እንደ ነበር ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም የእርሱን ብርሃን በማንጸባረቅ ትዘልቃለች (ኢሳ 9÷2፤ 49÷6፤ ሉቃ 2÷32፤ ሐሥ 13÷47፤ 26÷23)፡፡

«ብርሃን»፣ ነገረ መለኮታዊ የእምነት መግለጫ ወይም ሃይማኖታዊ ተቋም አይደለም፡፡ ብርሃን የእያንዳንዱን ክርስቲያን መልካም ተግባር ይወክላል፡፡ ያለብንን ኀላፊነት ቤተ ክርስቲያን ወይም ሃይማኖታዊ ተቋም ውስጥ በመደበቅ ከተጠያቂነት ማምለጥ አንችልም፡፡ ድነትን ያላገኙ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማንነት ማየት ይችሉ ዘንድ እያንዳንዱ ክርስቲያን በዚህ ዓለም ብርሃን እንዲሆን ተጠርቷል፡፡

ይህን ስናደርግ እግዚአብሔር ይመሰገናል፡፡ ይህ ዓለም ተገቢውን አገልግሎት ማግኘት እንደሚችል ከምንባቡ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለ ብፅዕና ከሚያወሳው ክፍል እያንዳንዱ ክርስቲያን ስለሚያገኘው በረከት እናያለን፡፡ የተራራውን ስብከት በሕይወታችን ተግባራዊ ስናደርግ ውጤቱ ይህን ይመስላል፡፡ እንግዲህ ኢየሱስ በመግቢያው አማካይነት መሠረት ካኖረ በኋላ ወደ መልእክቱ ዋነኛ ሐሳብ ይሸጋገራል፡፡

**§ 54መ**
**ሕጉ በተግባር ይፈጸማል እንጂ አይሻርም**
**(ማቴ 5÷17-20)**

ስለ ብፅዕናዎቹ የሚያወሳው ክፍል፣ «በመንግሥተ ሰማይ» ማዕቀፍ የሚታይ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ይህም ስብከት መታየት ያለበት «ከሕግና ከነቢያት» አንጻር ነው (ማቴ 5÷17፣19-20፤ 7÷12)፡፡ ስለሆነም የስብከቱን

ጭብጥ ሐሳብ መረዳት የሚቻለው የእግዚአብሔርን ቃል (ብሉይ ኪዳን) አሁን ላለው የእግዚአብሔር መንግሥት ተግባራዊ ስናደርግ ነው:: ኢየሱስ ስብከቱን የጀመረው ሦስተኛ መደብ በመጠቀም ነበር (ቁ 3-10 ስለ ብፁዓን)፤ ቀጥሎ በሁለተኛው መደብ መናገር ጀመረ (ቁ 11-16 ክርስቲያናዊ ተፅዕኖ)፤ አሁን ደግሞ እርሱ ራሱ ከብሉይ ኪዳን ጋር ያለውን ግንኙነት ለማሳየት በመጀመሪያ መደብ ይጠቀማል (ቁ 17-20)::

ኢየሱስ ብሉይ ኪዳንን መፈጸሙን የሃይማኖት መምህራኑ ከሚሰጡት ትርጉም ጋር በማነጻጸር እየተናገረ ነበር (ቁ 21-48):: አነጋገሩ ብሉይ ኪዳንን የሚጻረር አስመስሎታል:: እያስተማረ የነበረው በራሱ ሥልጣን እንጂ የአይሁድ መምህራን በሚያስተምሩበት መንገድ አልነበረም (ማቴ 7÷28-29):: ስለ ሰንበት የነበራቸውን ባሕላዊ አመለካከት በመጻረሩም አንዳንዶቹን አስቆጥቶ ነበር (ማር 2÷23-3÷6):: ኢየሱስ በጣም የተለየ ከመሆኑ የተነሣ አንዳንዶች ትምህርቱን፣ «አዲስ ትምህርት» ብለውት ነበር (ማር 1÷27):: ይሁን እንጂ ኢየሱስ አንዱንም የብሉይ ኪዳንን ክፍል እንደማይቃወም በአጽንዖት አስረዳ (ቁ 17-20):: እንዲያውም ያደረገው ትርጉሙን ጥልቅ በሆነ መልኩ ማቅረብ ነበር፤ የተቃወመው በቃል ሲተላለፍ የኖረውን የጸሐፍት አመለካከት ነበር::

> [17]«ሕግንና የነቢያትን ቃል ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ:: ለመፈጸም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም:: [18]እውነት እላችኋለሁ፤ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ሕግ ሁሉ ይፈጸማል እንጂ ከሕግ አንዲት ፊደል ወይም አንዲት ነጥብ እንኳ አትሻርም::
>
> ማቴ 5÷17-18

ይህ አስቸጋሪ ክፍል ነው:: በአንድ በኩል ኢየሱስ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ሕጉ እንደሚኖር ይናገራል:: በሌላ በኩል



ደግሞ ጳውሎስ የሙሴ ሕግ መፈጸሙን ያመለክታል (ሮሜ 10÷4፤ ገላ 3÷23-25፤ ኤፌ 2÷15፤ ቈላ 2÷14):: ይህን አለመጣጣም የሚመስል ጉዳይ እንዴት ነው የምናስማማው? አንደኛው መልስ አያሌ ዓመታት ወደ ኋላው ቶማስ አኲይናስ ዘመን የሚመልሰን ሲሆን (1225-1274 ዓ.ም.) በግብረ ገባዊ፣ ፍትሐ ብሔርና ሥርዐታዊ ሕግ መካከል ልዩነት ያደርጋል::

ይህ አመለካከት የሚያስቀምጠው ንድፈ ሐሳብ ከሞላ ጐደል እንዲህ ይላል፤ ሥርዐታዊው ሕግ ኢየሱስ መስቀል ላይ በነበረ ጊዜ ተፈጽሞአል፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ የመንፈሳዊው እንጂ የቁሳዊው ዓለም ዜጐች ባለመሆናቸው የፍትሐ ብሔሩ ሕግ ከእንግዲህ ጥቅም የለውም:: እንዲህ ከሆነ ዛሬም ቢሆን ክርስቲያኖች ማክበር ያለባቸው የብሉይ ኪዳኑን ግብረ ገባዊውን ሕግ ብቻ ይሆናል ማለት ነው::

ችግሩ የሚመጣው ሥርዐታዊ፣ የፍትሐ ብሔርና ግብረ ገባዊ የብሉይ ኪዳን ሕጐችን መወሰን የሚቻለው እንዴት እንደ ሆነ ጥያቄ ሲነሣ ነው:: ቅዱሳት መጻሕፍት በእነዚህ መካከል ምንም ልዩነት አላኖሩም:: ስለሆነም ይህን በመወሰን ረገድ መጽሐፍ ቅዱስ ሊረዳን አይችልም ማለት ነው:: ነገሩን ይበልጥ ውስብስብ የሚያደርገው ደግሞ አንዳንድ ግበረ ገባዊ፣ የፍትሐ ብሔርና ሥርዐታዊ ሕጐች ተወራራሽ መሆናቸው ነው:: ለምሳሌ ያህል የሰንበት ሕግ ሥርዐታዊም ሃይማኖታዊም ይመስላል:: መፋታትን በተመለከተ ሕጉ የፍትሐ ብሔርም ግብረ ገባዊም ነው:: ስለ መሥዋዕት አቀራረብ የተሰጠው ሕግ ደግሞ ሥርዐታዊና ግብረ ገባዊም ነው:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ እየጠበቅን ያለነው የትኛውን ሕግ እንደሆነ እንኳ በእርግጠኝነት ማወቅ አንችልም ማለት ነው:: ከዚህም በላይ ቁጥር 18 ከቀረበው ንድፈ ሐሳብ ጋር አይስማማም:: ኢየሱስ የብሉይ ኪዳንን ሕጐች በሙሉ መፈጸም እንዳለብን ነው የተናገረው::

እንግዲህ፣ ኢየሱስ ሕጉን የፈጸመው እንዴት ነበር? ይህን አስመልክቶ ጥቂት መልሶች ቀርበዋል፤ (1) ወደ እርሱ የሚያመለክቱ ትንቢቶች - ብሉይ ኪዳን ሁሉ ወደ እርሱ ያመለክታል፤ ስለሆነም ከኢየሱስ በተለየ ሁኔታ ልንረዳው አንችልም (ሉቃ 24÷27፣44፤ ዮሐ 5÷39 ጋር ያነ):: ይህም በምሳሌና ዘይቤ የተነገሩትን ይጨምራል:: (2) መታዘዙ - ሕጉ የሚጠይቀውን ሥነ ምግባራዊ መስፈርት ሁሉ የፈጸመ ኢየሱስ ብቻ ነው (2ቆሮ 5÷21፤ ዕብ 4÷15):: (3) ቤዛነት - ኢየሱስ የኀጢአታችንን ዋጋ ሁሉ ከፈለ (ሮሜ 6÷23፤ ዕብ 10÷11-18):: ይሁን እንጂ እነዚህ መልሶችን በተመለከተ ችግር የሚኖረው ቁጥር 19 ላይ ነው:: ኢየሱስ ሕጉን መፈጸሙን ብቻ ሳይሆን እኛም መፈጸም እንዳለብን ጭምር ነበር የተናገረው::

ታዲያ፣ ኢየሱስ ሕግን ፈጽሞአል ሲባል ምን ማለት ነው? ምንም ማለት ይሁን ምን ክርስቲያኖች ከሙሴ ሕግ በታች አለመሆናቸው ግን ግልጽ ነው:: ይህም ማለት በሙሴ ሕግ መሠረት አይፈረድብንም ወይም አንኰነንም:: ሕጉ የሚጠይቀው ቅጣት ተሟልቷል (ሮሜ 7÷4፤ ቈላ 2÷14፤ ዕብ 8÷13፤ 10÷8-10):: የምንመራው በመንፈስ ቅዱስ በኩል በልባችን በተጻፈ አዲስ ሕግ ነው (ሮሜ 8÷2-4፤ ገላ 5÷4-5፣18፤ ዕብ 8÷10-11፤ ኤር 24÷7፤ 31÷33):: አዲሱ ጌታችን፣ ክርስቶስ እንጂ ሕግ አይደለም (ሮሜ 10÷4፤ ገላ 4÷23-25)፤ ሌላው ቀርቶ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንኳ ሲያመለክቱ የኖሩት ወደ ክርስቶስ ነበር (ሮሜ 3÷21፤ ገላ 3÷24):: ኢየሱስ የብሉይ ኪዳንን አመጋገብ ደንብ ለውጧል (ማር 7÷19 ጋር ያነ):: ነገሮች ተለውጠዋል!

ይሁን እንጂ፣ ከብሉይ ኪዳን ሕግ ቁጥጥር ሥር አለመሆናችን ወይም የሚፈረድብን በዚህ ሕግ መሠረት አለመሆኑ ትእዛዞቹን ችላ እንድንል ምክንያት ሊሆነን አይገባም:: ኢየሱስ ሕጉ መከበር እንዳለበት



ነው የተናገረው:: ሌላው ቀርቶ አንዲት ፊደል ወይም ነጥብ እንኳ መሻር እንደሌለበት አመልክቷል::

እንዲህ ከሆነ ክርስቲያን ለብሉይ ኪዳን ሕግ የሚኖረው አመለካከት ምን መሆን አለበት? መሠረታዊው ጉዳይ ያለው እዚህ ላይ ነው፤ ክርስቶስ ሕጉን የፈጸመው በድርጊት ሳይሆን ሆኖ በመገኘቱ ነበር::[62] ኢየሱስ መቅደሳችን፣ ሰንበታችን፣ ንጉሥ ዳዊትና ሙሴ ሆኖልናል፤ እርሱ ሊቀ ካህናችን፣ የመሥዋዕቱ በግ፣ የተስፋው ምድር እንደ መሆኑ መጠን በአካል የተገለጠ የሙሴ ሕግ ነበር ማለት ይቻላል:: ብሉይ ኪዳን ሁሉ ተጣርቶ የሚያልፈው በኢየሱስ ውስጥ ነው:: ማንኛ ውም የሕጉ ዐረፍተ ነገር፣ ቃል፣ ሌላው ቀርቶ እያንዳንዱ ፊደል እንኳ በእርሱ ውስጥ ተካትቷል:: እዚህ ላይ ግን ምንም የጠፋ ነገር የለም ሲባል ምንም የተለወጠ ነገር የለም ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል:: የሙሴ ሕግ ደንብ በክርስቶስ ተፈጽሞአል፤ ዓላማው ግን ያው እንደ ቀድሞው ይኖራል::

በብሉይ ኪዳንም ቢሆን ሕጉ የድነት ምንጭ እንዳልነበር መገንዘብ አለብን::[63] አይሁድ ይድኑ የነበረው እግዚአብሔር ስለ መረጣቸው ብቻ እንጂ፣ እንደሚገባ ለሕጉ በመታዘዛቸው አልነበረም:: ስለሆነም የሕጉ ዓላማ ሁለት ነበር ማለት ነው:: የእግዚአብሔር ቅድስና ማወጅና በማኅበረሰቡ ውስጥ እንዴት መኖር እንደሚገባ መመሪያ መስጠት:: ከዓለም በመለየት የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያመለክታል::[64] ስለዚህ ብሉይ ኪዳን ለድነትና ለፍርድ ባይሆንም፣ መመሪያና ትምህርት በመስጠት ረገድ ጠቃሚ ነው ማለት ነው (2ጢሞ

[62] F. Zaspel, "Devine Law: A New Covenant Perspective," R&R 6/3 (1997): 145-169.

[63] J.D. Charles, "The Greatest or the Least in the Kingdom? The Disciple's Relationship to the Law (Mt 5:17-20)" *TrinJ* 13ns (1992): 139-162.

[64] W.C. Kaiser, "The Place of Law and Good Works in Evangelical Christianity," in *A Time to Speak: The Evangelical-Jewish Encounter*, ed. by A. James Rudin and Martin R. Wilson (Grand Rapids: Eerdmans, 1987).

3÷16):: የማቴዎስን መጽሐፍ ልብ ስንል ሕጉ በተግባር መዋል ያለበት ፍቅርና ምሕረትን መሠረት በማድረግ እንደ ሆነ እንገነዘባለን (ማቴ 5÷43-48፤ 7÷12፤ 19÷19፤ 22 ÷34-40፤ 24÷12፤ 25÷31-46)::[65] በተጨማሪም አዲስ ኪዳን አንዳንድ የቀድሞ ደንቦችን ተግባራዊ የምናደርግበትን መንገድ እንደሚለውጥ ግልጽ ነው:: ባሙሴ በኩል በተሰጠው ኪዳን መሠረት በመንግሥተ ሰማይ ተግባር ላይ የሚውሉት ሁሉም አይደሉም:: ስለዚህም በትክክል ሕጉን መረዳት የሚቻለው በኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት በኩል ነው (ሉቃ 24÷25-27):: እንደ ጥንት እስራኤል ሁሉ የተለየን መሆናችንን ለማሳየት የክርስቶስን ሕግ እንፈጽማለን፤ ለድነታችን በክርስቶስ መሥዋዕትነት እንታመናለን::

ማቴ 5÷19-20

19ስለዚህ ማንም ከእነዚህ ትእዛዛት ለነስተኛይቱን
እንኳ ቢተላለፍ፣ ሲሎችንም እንዲተላለፉ ቢያስተምር
በመንግሥተ ሰማይ ታናሽ ተብሎ ይጠራል፤ ነገር ግን
እነዚህን ትእዛዛት እየፈጸመ ሌሎችም እንዲፈጽሙ የሚያስተምር በመንግሥተ ሰማይ
ታላቅ ይባላል:: 20ጽድቃችሁ ከፈሪሳውያንና ከኦሪት ሕግ መምህራን ጽድቅ ልቆ
ካልተገኘ መንግሥተ ሰማይ መግባት አትችሉም::

ፈሪሳውያን ተግባር ላይ መዋል የማይችል የመሰላቸውን፣ ወይም ምቾት የማይሰጣቸውን ክፍል በቸልታ የማለፍ መጥፎ ልማድ ነበራቸው:: ኢየሱስ ግን እነዚህን ክፍሎች አጥብቆ ይመረምር ነበር «መሻር» [*katalysai*] (ቁ 17) እና «መተላለፍ» [*lyse*] (ቁ 19) ሲል ምን ማለቱ እንደ ነበር በትክክል ይረዱታል:: ፈሪሳውያን አስቸጋሪ ክፍሎችን በቸልታ ማለፍ ብቻ ሳይሆን፣ በትክክል ቢያስተምሩ እንኳ የሚያስተምሩትን አይኖሩበትም ነበር (ማቴ 23÷2-4):: ለእግዚአብሔር ቃል ከበሬታ እንዳላቸው ቢናገሩም ቃሉ ለሚጠይቀው አይታዘዙም ነበር (ዮሐ 5÷39-40)::

[65] K.R. Snodgrass "Matthew's Understanding of the Law," *Int* 46(Oct 1992): 368-378.



ፈሪሳውያን ጥቃቅኑን ሃይማኖታዊ ሥርዓት በመፈጸም ይታወቁ ነበር (ማቴ 23÷23-24):: ምንም እንኳ አስተሳሰባቸው ትክክል ባይሆንም፣ አንድን ሰው ከጸሐፍትና ከፈሪሳውያን የበለጠ የጽድቅ ሕይወት መኖር ይቻላል ወይ በማለት እንዲጠይቅ ሊያደርገው ይችላል:: ኢየሱስ ግን የመታዘዝ ስፋቱን ሳይሆን ጥልቀቱን ነበር የሚፈልገው:: ለሕግና ሥርዐት ዝርዝሮች ከመታዘዝ ይልቅ እግዚአብሔር ለሚፈልጋቸው ነገሮች ቅድሚያ የሚሰጥን ልብ ነበር የሚመለከተው «እነዚያን ሳትተዉ እነዚህን ማድረግ በተገባችሁ ነበር» (ማቴ 23÷23)::

**§ 54ሰ**
**«እንዲህ እንደተባለ ተሰምታችኋል ... እኔ ግን እላችኋለሁ» ስድስት ንጽጽሮች (ማቴ 21-48፤ ሉቃ 6÷27-30፣32-36)**

ከዚህ ክፍል እንደምንመለከተው፣ ኢየሱስ «እኔ ግን እላችኋለሁ» የሚለውን ዐረፍተ ነገር እንደ መዝሙር አዝማች ሁሉ በመሐል እያስገባ ሲጠቀምበት እናያለን (5÷22፣28፣34፣39፣44):: ይህም በኢየሱስ ትምህርትና ቀደም ሲል በነበረው ትምህርት መካከል የነበረውን ተቃርኖ ያመለክታል:: እዚህ ላይ፣ «የቀደመው ትምህርት ምን ነበር?» የሚል ጥያቄ ይነሣል፤ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ማለቱ ከሆነ በመጠኑ እያሰፋው አንዳንዱንም እየተቃረነው እንደ ነበር መመልከት ይቻላል:: ይሁን እንጂ ጆን ስቶት ኢየሱስ እየተቃረነ የነበረው የፈሪሳውያንን የብሉይ ኪዳን አተረጓጎም እንጂ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዳልነበር ጠንካራ መከራከሪያ አቅርቧል::[66]

ስቶት አቋሙን ለመደገፍ አራት ማስረጃዎች አቅርቧል፤ (1) እነዚህ ስድስት ጥቅሶች እያንዳንዳቸው ከሕጉ ውስጥ የተወሰዱ ይመስላሉ:: ይሁን እንጂ «ወዳጅህን ውደድ፤ ጠላትህን ጥላ» ወደሚለው

[66] J.R. Stott, *Christian Counter-Culture* (Downers Grove, IL: InterVarsity, 1978) pp. 76-79.

ወደ ስድስተኛው ስንመጣ ግን የመጀመሪያውን ክፍል ዘሌዋውያን 19÷18 ላይ ብናገኘውም፣ በተጨማሪም ቁ 31 የዘዳግም 24÷1፣3ን ማብራሪያ ይመስላል:: (2) «ለቀደሙት ሰዎች» (ቁ 21፣33) «እንዲህ እንደ ተባለ ሰምታችኋል «(ቁ 27፣38፣43) በማለት ኢየሱስ የተጠቀመበት መግቢያ «እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል» ከሚለው በጽሑፍ ከሰፈረው ይልቅ በቅብብሎሽ ሲተላለፍ ከኖረው ትምህርት ጋር ይበልጥ ይስማማል:: (3) ከዐውዱ መመልከት እንደሚቻለው (ቁ 17-20) ምንም እንኳ ፈሪሳውያን ችላ በማለት ማለፋቸውን ቢቃወምም የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ኢየሱስ በማስረግጥ አመልክቷል:: ስለሆነም ቀጣዩ ገለጻ የፈሪሳውያንን የተሳሳተ አተረጓጎም የተመለከተ ነበር ማለት ነው:: (4) በሌላ ስፍራ ኢየሱስ በጽሑፍ ለሰፈረው ቃል መገዛቱን አሳይቷል (ለምሳሌ፣ በተፈተነ ጊዜ ምዕ 4):: እዚህም ላይ ያንኑ እያደረገ እንደ ነበር ማሰብ ይቻላል::

የፈሪሳውያን አተረጓጎም እግዚአብሔር የከለከላቸውን ነገሮች በተመለከተ ቸልተኝነት ቢያሳይም፣ የፈቀዳቸውን ነገሮች ግን ከሚገባው በላይ አስፍቷቸዋል:: ስለሆነም የእግዚአብሔርን ሕግ፣ «ለአያያዝ እንዲመች» እያደረጉት ነበር ማለት ነው:: ኢየሱስ ግን ተቃራኒውን ነበር ያደረገው:: ይህንን ከታች ካለው ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል::

| ሕጉ | ዐይነቱ | ፈሪሳውያን | ኢየሱስ |
|---|---|---|---|
| መግደል (ቁ 21-26) | የተከለከለ | በድርጊት ብቻ የተወሰነ | ሐሳብንም ይጨምራል |
| ማመንዘር (ቁ27-30) | የተከለከለ | በድርጊት ብቻ የተወሰነ | ሐሳብንም ይጨምራል |
| መፋታት (ቁ 31-32) | የተፈቀደ | በማንኛውም ቦታ ተግባራዊ መሆን የሚችል | የሚፈቀደው በዝሙት ምክንያት ብቻ ነው |
| መሐላ (ቁ 33-37) | የተከለከለ | በአንዳንድ ተስፋዎች ብቻ | አዎን ወይም አይደለም ማለት ብቻ ይበቃል |
| መበቀል (ቁ 38-42) | የተፈቀደ | ተገቢ ከሆነ ይፈቀዳል | ጨርሶ የማይፈቀድ |
| መወደድ (ቁ 43-48) | ትእዛዝ ነው | በወዳጆች ብቻ ይወሰናል | ጠላቶችን መወደድም ይጨምራል |



ድምር ውጤቱ ፈሪሳውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ እንዲቻል ሲያቀሉት ኢየሱስ ግን ይበልጠ ከባድ ማድረጉ ነው:: የሚገርመው ፈሪሳውያን አንዳንድ ተጨማሪ ሕጎችን ሲቀበሉ ኢየሱስ ግን እንዲህ ያሉትን ማስወገዱ ነው:: ታዲያ፣ ኢየሱስ ያቀረበው መመሪያ ይበልጥ ከባድ የሚሆነው እንዴት ነው? ሕጉን ውስጣዊ ነገርንም መመልከት በሚችል ሁኔታ አቅርቧል፤ እርሱ ወደ ዘልቆ ገብቷል::

## 1. መግደል/መቆጣት

ማቴ 5÷21-22

[21]ለቀደሙት ሰዎች፣ አትግደል፣ የገደለ ይፈረድበታል እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ [22]እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ወንድሙን ያለ አግባብ የሚቆጣ ይፈረድበታል፤ ማንም ወንድሙን «ጅል» የሚል በሸንጎ ፊት ይጠየቅበታል፤ «ደደብ» የሚለው ደግሞ የገሃነም እሳት ፍርድ ይጠብቀዋል::

«አትግደል»፣ የሚለው 6ኛው ትእዛዝ ነው::[67] ፈሪሳውያን ያተኮሩት በተግባር የሚፈጸም ግድያ ላይ ነበር:: በሌላ በኩል ደግሞ ኢየሱስ ቅጣቱ ከግድያው በስተጀርባ ያለውን ዐላማ የሚመለከት አድርጎታል:: በኋላ ላይ ዮሐንስ፣ «ወንድሙን የሚጠላ ነፍስ ገዳይ ነው» ሲል ይህንኑ ማንጸባረቁ ነበር (1ዮሐ 3÷15)::

እዚህ ላይ አንዳንድ ነጥቦችን ግልጽ ማድረግ ይኖርብናል:: በመጀመሪያ የቅጣቱ እያደገ መሄድ (ፍርድ /ሸንጎ/ገሃነም) ምናልባት ከአጻጻፍ ስልት የዘለለ ላይሆን ይችላል:: ብዙ ጊዜ አይሁዳውያን እንዲህ ያሉ ተጓዳኝ ነገሮች ይጠቀማሉ:: ሁለተኛው፣ «ጅል» (ራካ፣ የተሰኘው የአረማይክ ስድብ፣ «ባዶ ጭንቅላት» የማለት ያህል ነው) እና «አንተ

[67] «መግደል» ለሚለው የዕብራይስጡ ቃል ራስን ለመከላከል፣ በቅጣት መልክ የሚፈጸም መግደልን፣ በስሕተት ሰውን መግደልን ወይም ጦር ሜዳ መሞትን አይጨምርም:: እነዚህ ነገሮች በሌላ ቦታ የሚታዩ ይሆናሉ::

ሞኝ» የሚሉት ሁሌም ቢሆን ተገቢ እንዳልሆነ ንግግር የሚቆጠሩ አይደሉም:: ኢየሱስ ራሱ ፈሪሳውያንን ሞኞች በማለት ጠርቷቸዋል (ማቴ 23÷17-19፤ በተጨማሪም 1ቆሮ 15÷36፤ ገላ 3÷1፤ ያዕ2÷20 ይመ):: ይሁን እንጂ፣ «ገዳይ» ከሆነ ስሜት የሚፈልቁ ከሆነ ግን አደገኞች ናቸው:: አንዳንድ ቅጆች «ወንድሙን» ካሉ በኋላ፣ «ያለ ምክንያት» የሚል በመጨመራቸው በቅጆቹ መካከል ልዩነት መኖሩ አሳማኝ ማስረጃ አለ:: ምንም እንኳ እነዚህ ቃሎች በጥንቱ ቅጂ ባይገኝም ኢየሱስ መናገር የፈለገውን በሚገባ መግለጽ የቻሉ ይመስላል:: የኢየሱስን አነጋገር ላላ ያደረጉ ቢመስልም ወደ ስድብና ንቀት አነጋገር በሚመራ ሁኔታ በትንሹ በትልቁ መቆጣታችንን ግን አይደግፉልንም::

[23]ስለዚህ መባህን በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር በምታቀርብበት ጊዜ ወንድምህን የተቀየመበትህ ነገር መኖሩ ትዝ ቢልህ፣ [24]መባህን በዚያው በመሠዊያው ፊት ተወው፤ በመጀመሪያ ሄደህ ከወንድምህ ጋር ተስማማ፤ ከዚያም ተመልሰህ መባህን ለእግዚአብሔር አቅርብ::

ማቴ 5÷23-24

«ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጌታን እያመለክህ እያለ ከሰው ጋር ስላለህ ጥላቻ ልብ ካልክ ማምለክህን ትተህ መጀመሪያ ሄደህ ከወንድምህ ጋር ታረቅ» በማለት ብዙዎች ይህን ክፍል ለዘመናችን በሚሆን መልኩ ሲያብራሩት ይሰማል:: ኢየሱስ ያቀረበውን መርሕ በአጭሩ ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት መስተካከሉ ከትክክለኛ ሃይማኖታዊ ሥርዐት የበለጠ አስፈላጊ ነው ወደሚል ድምዳሜ ያደርሰናል:: ይህ አባባል ከምንም በፊት እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ቦታ መያዝ አለበት የሚሉ ሃይማኖተኞችን ሊያስቆጣ ይችላል:: እነዚህ ሰዎች ትክክል ናቸው:: ሆኖም ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት በተሻለ መልኩ የሚመዘነው ከሃይማኖታዊ ሥርዐት ይልቅ ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት መሆኑን



መዘንጋት የለብንም:: ምንም እንኳ የተበደለው ወንድም እንደሚቀበለን እርግጠኞች ባንሆንም፣ «የምንችለውን ሁሉ» ማንኛውንም ጥረት ማድረግ አለብን (ሮሜ 12÷18)::

ማቴ 5÷25-26

[25]«የከሰሰህ ባላጋራህ እንዳያስፈርድብህ፣ ዳኛውም ለአሳሪ አሳልፎ እንዳይሰጥህ፣ በወህኒም እንዳትጣል፣ በመንገድ ላይ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ:: [26]እውነት እልሃለሁ ካስፈረደብህ ግን የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከዚህ አትወጣም»::

የመጀመሪያው ምሳሌ ወዳጅን የሚመለከት ነበር (ቁ 23):: ሁለተኛው ምሳሌ ግን ጠላትን ወይም ባለጋራን የሚመለከት ነበር (ቁ 25):: የመጀመሪያው መቅደስ ውስጥ ነበር:: ሁለተኛው ግን የፍርድ ቤት መንገድ ላይ ነበር:: ይሁን እንጂ ሁለቱም አንድ ዐይነት መልእክት ያስተላልፋሉ - ዕርቅ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን::

የኢየሱስ ንግግር ምሬታዊ ጥበብን ያዘለ ነው:: ከፍርድ ቤት ውጪ እልባት የሚያገኝ ነገር ምን ያህል ቀላል መሆኑን የትኛውም የሕግ ሰው ይገነዘባል:: ዳኛ ዘንድ ከደረሰ ግን ጉዳዩ ከእጃችን ወጥቷል ማለት ነው:: በኢየሱስ ዘመን እንደ ነበር በዚህ ዘመንም የመጨረሻው ሳንቲም[68] እስኪከፈል ድረስ ተከሳሹ ወህኒ ይቆያል::

ይሁን እንጂ ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር የሚመለከተው ምድራዊ ሙግትን አይደለም ከዐውዱ መረዳት እንደሚቻለው ስለ ዘላለማዊ ፍርድ ነው የሚናገረው:: በዚህ ምድር የሚኖረን ግንኙነት ከዚህ በኋላ[69] ያለውን ዕጣ ፈንታ ይወስዳል::

[68] ኳድራንቴ የሚባለው ሳንቲም መደበኛ የቀን ክፍያ አንድ ስድሳ አራተኛ ነበር::

[69] ከዐውዱ አንፃር ይህን ዘይቤአዊ አነጋገር መንጽሔን (purgatory) ሊያመለክት እንደሚችል ማሰብ በፍጹም የማይቻል ነው::

## 2. ማመንዘር

27«አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል፡፡28እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ሴትን በምኞት ዓይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል፡፡» ማቴ 5÷27-28

ኢየሱስ ከ6ኛው «አታመንዝር» ወደ 7ኛው ትእዛዝ ተሻግሯል፡፡ ይህን በተመለከተም ቢሆን ፈሪሳውያን ግምት የሚሰጡት በተግባር ለተፈጸመው ብቻ ሲሆን ኢየሱስ ግን ከድርጊቱ ባሻገር ያለውን፣ ያም ምኞትን ማካተት ወደሚችል ደረጃ አሳድጎታል፡፡ እዚህ ላይ እየተናገረ ያለው ስለ ድንገተኛ እይታ ወይም ሳንፈልገው ስለሚመጣ ሐሳብ አይደለም፡፡ «ተመልክቶ» (*blepon*) የሚለው ያሁን ጊዜን ቀጣይ ድርጊት ያመለክታል፤ እንዲህ ያለውን ሐሳብ ማውጣት ማውረድን ይመለክታል፡፡

ኢየሱስ የተቃወመው መመልከትን ሳይሆን በዚያ ሳቢያ የሚመጣ የኃጢአት ምኞትን ነው፡፡ ወሲብ ነክ ምስሎች በመገናኛ ብዙኃን በሚተላለፉበት በዚህ ዘመን ምኞት ወደ አእምሮአችን እንዳይዘልቅ ማድረግ በፍጹም የማይቻል ነው፡፡ እንዲህ በመሆኑ በደለኞች አንሆንም፡፡ እነዚህ ሐሳቦችን በአእምሮአችን ብናብሰለስላቸው ግን የማመንዘር ኃጢአት ፈጽመናል ማለት ነው፡፡ ከተለያየ አቅጣጫ ሰይጣን ቤተ ክርስቲያንን እያጠቃ እንደሆነ ያታወቃል፡፡ ብዙ ጊዜ ደግሞ ሲያመነዝሩ የተያዙ ሰዎች እንኳን በመገረም፣ «እንዴት ሊሆን እንደቻለ አናውቅም» ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ ችግሩ የኢየሱስን ቃል በሚገባ አለመስማታችን ነው፡፡ ዝሙት ተፈጸመ የሚባለው ሁለት ተቃራኒ ጾታዎች የግብረ ስጋ ግንኙነት ከማድረጋቸው በፊት ነው (ኢዮ 31÷1፣7፣9)፡፡



29ቀኝ ዓይንህ የኃጢአት ሰበብ ቢሆንብህ፣ ማቴ 5÷29-30
ዐውጥተህ ወዲያ ጣለው፤ ሰውነትህ በሙሉ ወደ ገሃነም
ከሚጣል ከሰውነትህ አንዱን ክፍል ብታጣ ይሻልሃል፡፡ 30ቀኝ እጅህ የኃጢአት ሰበብ ቢሆንብህ ቆርጠህ ወዲያ ጣለው፤ ሰውነትህ በሙሉ ወደ ገሃነም ከሚጣል ከሰውነትህ አንዱን ክፍል ብታጣ ይሻልሃል (ከማቴ 18÷8-9 ጋር ያነ)፡፡

ለኢየሱስ ታማኝ ለመሆንና ወደ ገሃነም እንዳንጣል ካለን ፍላጎት የተነሳ ከፊል እኛነታችን ይህን ክፍል ቃል በቃል መውሰድ ይፈልጋል፡፡ በተጨማሪም፣ ምን ያህል ኃጢአተኞች እንደምንሆን እንገነዘባለን፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የግነት ቃል ለመሆኑ መገንዘብ አያዳግተንም፡፡ የኢየሱስን አነጋገር ቃል በቃል ተግባር ላይ እናውለው ቢባል ውጤቱ ምን ያህል ዘግናኝ እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ዋናው የኃጢአት መሣሪያ አንጐላችን እንጂ ሌላው የአካል ክፍላችን ባለመሆኑ እንደዚያ ማድረግ ምንም ጥቅም አይኖረውም፡፡[70]

ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ግልጽ ስለሆኑት የአካል ብልቶቻችን አይደለም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ አንድ ዓይንን አውጥቶ መጣል ብቻ ምን ሊጠቅም ይችላል? አንድ ዓይናችን ቢወጣ እንኳ በሌላው ዐይናችን እናያለን፡፡ ስለዚህ እጃችን ቁርጦ የተጣለ ያህልና ዐይናችን ወጥቶ የተወገደ ያህል [illegible] ነው፡፡ ፈተና ሲገጥመን ማየት ማቆም አለብን፡፡ [illegible] ዘወር ማለት አለብን፤ ለኃጢአት ሰበብ ከሚሆኑ ጓደኞቻችን መራቅ አለብን፡፡ እንዲህ ማድረጋችን ራሱ አንዳንዴ የአካል ክፍሎቻችንን ቆርጠን የመጣልን ያህል ያመናል፤ የዚያን ያህል አስቸጋሪ ይሆንብናል፡፡ ለኃጢአት ብቸኛው መፍትሔ ሞት ነው (ማር 8÷34፤ ሮሜ 6÷5 -7፤ 8÷13፤ ገላ 5÷24፤ ቆላ 3÷5)፡፡

70 አንዳንዶች ይህን ቃል በቃል ተግባር ላይ በማዋላቸው የተጠቀሰው ዐይነት ችግር አጋጥሟቸዋል፡፡ ምናልባትም ለዚህ ታዋቂ ምሳሌ የሚሆነን ምንም እንኳ ራሱን ቢያኰላሽም ከምኞት ነጻ ሊሆን ያልቻለው አርጌንስ (195-254 ዓ.ም.) ነው፡፡

### 3. መፋታት

[31]ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ የፍቺ ወረቀት መስጠት አለበት እንደተባለ ሰምታችኋል [32]እኔ ግን እላችኋለሁ በላዩ ላይ ስታመነዝር ካላገኛት በስተቀር፣ ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ እንድታመነዝር ያደርጋታል፤ በዚህ ሁኔታ የተፈታችውን ሴት ያገባም እንዳመነዘረ ይቈጠራል:: ማቴ 5÷31- 32

*31 ዘዳ 24÷1*

ብዙውን ጊዜ ከማመንዘር ጋር በተያያዘ የሚነሳው መፋታትን የሚመለከተው ጉዳይ ቤተ ክርስቲያንን ከሚገጥሟት አዳጋችና ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቁ ነገሮች መካከል ዋነኛው ነው:: መፋታትን አስመልክቶ ኢየሱስ በሰፋት የተናገረው በማቴዎስ 19÷1-12 ነው:: ስለ ገሃነም ዘርዘር ባለ መልኩ የምንመለከተው ወደዚያ ስንደርስ ይሆናል:: አሁን ግን ይህ የመፋታት ጉዳይ ከተራው ስብከት መልእክት ጋር እንዴት ሊጣጣም እንደሚችል እናያለን::

በመጀመሪያ፣ መፋታት የተፈቀደው ከማመንዘር ጋር በተያያዘ ሁኔታ እንደሆነ ኢየሱስ መናገሩን ነው የምንረዳው:: ከኢየሱስ በፊት የነበሩ ሒላልና ሽማኤ የተባሉ ሁለት ታዋቂ የአይሁድ መምህራን በዚህ ጉዳይ ከፍተኛ ክርክር አድርገዋል:: ዘዳግም 24÷1-4ን መሠረት በማድረግ አንድ ሰው ማንኛውንም ዐይነት «ተገቢ ያልሆነ» ጉዳይ ፈጽማ ከተገኘች ሚስቱን መፍታት እንደሚችል ይታሰብ ነበር:: ያ፣«ተገቢ ያልሆነ» ጉዳይ ምን ሊሆን እንደሚችል ብዙ የሚያከራክር ነው:: ሽማኤ እንደሚለው ጉዳዩ የሚመለከተው ከግብረ ሥጋ ጋር ተያያዥ የሆኑ ነገሮችን ብቻ ነው:: ሒላል ግን በምግብ ዝግጅት የሚያጋጥም ስሕተትን ጨምሮ ማንኛውም አግባብ ያልሆነን ነገር ሁሉ እንደሚጨምር ያስባል:: በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው የሒላል



አስተሳሰብ ነበር:: እዚህም ላይ ኢየሱስ ተቀባይነት ከነበረው አስተሳሰብ ጋር መጋጨቱን እናያለን::

ለጋብቻ ታማኝ አለመሆንን ለማመልከት ኢየሱስ የተጠቀመበት «ፖርኔኢ» የተሰኘው ቃል [porneia] የግድ ከማመንዘር ጋር ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ሴሰኝነትን ጨምሮ (ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት) የተለያዩ ተገቢ ያልሆኑ የግብረ ሥጋ ግንኙነቶችን ሁሉ ያካትታል:: ይሁን እንጂ በዚያ ዘመን «ፖርኔኢ» የሚለውን ቃል በዋነኛ ነት ደረጃ የሚጠቀሙበት የሴቶች ማመንዘርን ለመግለጥ ነበር:: የወንዶች ማመንዘር «ሞይኬያ» [moicheia] በተሰኘ ቃል ነበር የሚገለጸው:: ስለሆነም ኢየሱስ እየተናገረ የነበረው ከጋብቻ በፊት ስለሚፈጸም ልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙት ሳይሆን በጋብቻ ውስጥ ታማኝ አለመሆንን አስመልክቶ እንደ ነበር ግልጽ ነው:: በአይሁድ ሕግ መሠረት (m. Yebam. 2:8 m. Sota 5:1) አንድ የትዳር ጓደኛ ታማኝ ያልሆነውን ወገን የመፍታት ግዴታ ነበረበት ለክርስቲያን ግን እንዲህ አይደለም:: ዮሐንስ አፈወርቅ እነዚህ ጥቅሶች ስለ ብፅዕና ከሚያወሳው ክፍል ተገንጥለው መታየት እንደሌለባቸው በማመልከቱ ትክክል ነበር:: ሌላው ቀርቶ ሚስቱ ብታመነዝር እንኳ የዋህ፣ ሰላም አድራጊና ይቅር ባይ የሆነ ባል ሚስቱን አስወጥቶ አይጥልም:: እግዚአብሔር በትዕግሥት ተቀብሎናል፤ እኛም ምሳሌነቱን መከተል ይኖርብናል (ኤር 2÷1-3÷1፤ 4÷1፤ ሆሴ 2÷1-23)::

ማርቆስም ሆነ ሉቃስ ይህን መግደፋቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት አንዳንዶች ሌላው ቀርቶ ማመንዘር እንኳ ለመፋታት በቂ ምክንያት ሊሆን መቻሉን ጥያቄ ውስጥ አስገብተዋል:: ኢየሱስ ያገለግል በነበረበት ዘመን ግን ማመንዘር ፍቺ ለማድረግ በቂ ምክንያት እንደሆነ ይታሰብ ነበር፤ ሒላልና ሽማኤ እንኳ በዚህ ይስማማሉ:: ማቴዎስ 19÷9 ይህን ጉዳይ በተመለከተ ግልጽ መመሪያ ያለው ይመስላል::

እዚህ ላይ ዋናው ጥያቄ፣ «መፋታት አንድን ወገን አመንዝራ የሚያደርገው እንዴት ነው?» የሚለው ነው። ኢየሱስ መፋታትን ከማመንዘር ጋር በማመሳሰል ምሳሌያዊ የሆነ ቃል እየተጠቀመ ነበር (ሆሴ 2÷4፤ ኤር 5÷7፤ ሕዝ 16÷32)። ያለ ምንም በደል ባልዋ የፈታት ሴት አመንዝራለች ማለት አይቻልም። በደል የለባትም። ከሌላ ወንድ ጋር ካልተኛች በአመንዝራነት ልትከሰስ አትችልም። ምናልባት በአይሁድ ልማድ መሠረት የተፈታች ሴት ልታገባ ወይም ሴተኛ አዳሪ ልትሆን እንደምትችል ይታሰብ ስለ ነበር ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ የግድ እንዲህ ሊሆን ይችላል ተብሎ መታሰብ የለበትም። ምናልባት ከቤተሰቧ ጋር ልትኖር ትችላለች። ኢየሱስ መፋታት የማመንዘርን ያህል ነው ማለቱ ሳይሆን፣ ሁለቱም አደገኛ ውጤት ሊኖራቸው ይችላል ማለቱ ነበር። በማቴዎስ 1÷91-12 ባለው ክፍል ኢየሱስ የጋብቻ መጀመርን በተመለከተ ከኦሪት ዘፍጥረት ሁለቱን አዕማድ አመልክቷል፤ (1) ሰው አባት እናቱን እንደሚተውና ከሚስቱ ጋር እንደሚጣበቅ፤ ይህም ማለት አንዳቸው ለሌላው ይሰጣሉ ማለት ነው፤ (2) ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤ አንዳቸው ለሌላው ታማኝ እንደሚሆኑ ቃል ይገባሉ ማለት ነው። ይህ ሁለተኛው ዐምድ ጠቅላይ ሐሳብ ሲሆን የግድ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ብቻ ግን የሚወሰን አይደለም።[71]

አንድ ወንድ ሚስቱን ከፈታ እርስ በርስ የመሰጣጣቱ ዐምድ ተፋልሷል፤ ጋብቻውም እንዳልነበር ሆኗል ማለት ነው። አንድ ሰው ካመነዘረ ታማኝነትን የሚወክለው ዐምድ ፈርሷል፤ ጋብቻውም መሠረት አጥቷል ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ መፋታትም ሆነ ማመንዘር የጋብቻ መፍረስ ምክንያት ሊሆኑ ስለሚችሉ ሁለቱም አንድ ናቸው ማለት ይቻላል። የተፈታውን የሚያገባ ሦስተኛ ወገንም እንዲሁ መሠረቱ በተናደው ጋብቻ ውስጥ ገብቷል፤ የመጀመሪያዎቹ ባልና ሚስት ዕርቅ

[71] C.L. Blomberg, "Marriage, Divorce, Remarriage and Celibacy: An Exegesis of Mt 19:3-12," *TrinJ* 11ns (1990):161-196.



ማድረግ እንዳይችሉ ምክንያት ሆኗል ማለት ነው። ስለሆነም በሁለተኛ ጋብቻ ውስጥ ተሳትፎ የማድረግ ተግባራዊ ውጤት የማመንዘር ያህል ነው፤ የመጀመሪያው ጋብቻ እንደገና እንዳይጠገን የራሱ አሉታዊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

ታዲያ ይህ እንደ ገና ማግባትን ኀጢአት ያደርገዋል? ማንኛውም ዕርቅ የማድረግ ሙከራ ካልተሳካ ምናልባት ኀጢአት አይሆንም። እንደ ቀጣይ የማመንዘር ኀጢአትም አይቈጠርም። ከዘዳግም 24÷1-4 እና ዮሐንስ 4÷17-18 ላይ ኢየሱስ ከተናገረው እንደምንመለከተው ከአንድ በላይ ጋብቻ ሊኖር የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ ልብ ይሏል።[72] ሆኖም፣ ምንም እንኳ ማመንዘር ባይሆንም እንደ ገና ማግባት የሚደገፍ ነው ማለት አይደለም። ምንጊዜም ቢሆን ሁለተኛ ጋብቻ የራሱ ስብራት ይኖረዋል።

ምናልባትም በፊታችን ሁለት የማይፈለጉ አማራጮች ይጋረጡ ይሆናል፤ እንደ ገና ማግባት ወይም ለብቻ መኖር። ልጆች ካሉ ምናልባት እንደገና ማግባት የተሻለ ምርጫ ሊሆን ይችላል። ያም ሆኖ ግን ሁለቱም ጥሩ ምርጫዎች አይደሉም። እንዲህ ሲባል ግን እንደ ገና ማግባት የተሳካ አይሆንም ማለት አይደለም። ሆኖም ያለፈውን ስብራት ትዝታ ይቀሰቅሳሉ፤ ከተግባራዊ ገጽታው በመነሣት የመጀመሪያው ጋብቻ ትቶት የሄደውን ስብራት ለመጠገን ሲባል ሁለተኛ ማግባቱ ከፍተኛ ስሕተት ነው።

ታዲያ፣ እንዲህ ከሆነ እንደገና የተጋቡ በማመንዘር ሕይወት እየኖሩ ነው ማለት ይቻላል? አይደለም። ምሳሌያዊ አነጋገር መሆኑን እናስታውስ። ኢየሱስ እንደ ገና ማግባት ተመሳሳይ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ እንደ ማመንዘር ይቆጠራል አለ እንጂ እንደገና ማግባት ኀጢአት ነው አላለም። ምንም እንኳ በማመንዘር ሕይወት

[72] በእግዚአብሔር ፊት ጋብቻ እንዳልነበር ሊሆን ይችላል። Cf. M.J. Down "The Sayings of Jesus about Marriage and Divorce," *ExpT* 95 (1984): 332-334.

ውስጥ መኖር ማለት ባይሆንም በስብራት ሕይወት ውስጥ ግን መኖር ማለት ነው:: እግዚአብሔር ያለፈ ኀጢአታችንን ቁስል መፈወስ ይችላል፤ ጠባሳው ግን አብሮ ይኖራል::

እግዚአብሔር መፋታትን እንደሚጠላ፣ (ሚል 2÷16) የፈቀደውም ከሰዎች ልብ ጠንካራነት የተነሣ እንደ ነበር እናውቃለን (ማቴ 19÷8፤ ማር 10÷5):: ጌታ አጽንዖት በመስጠት መናገር የፈለገው፣ «አትፋቱ» የሚለውን ነው:: አንድ ሰው ከተፋታ በኋላስ ምን ማድረግ ይቻላል? በጣም አስቸጋሪ ጥያቄ ነው:: መፋታትን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው፣ «አትፋቱ» የሚለውን ትክክለኛ መርሕ ለማመልከት ነበር:: ከዚህ ሐቅ በተጻረረ እንድንሄድ ምክንያት ሊሆኑን የሚችሉ ነጥቦች በጣም ጥቂቶች ናቸው:: መጽሐፍ ቅዱሳዊ መስፈርቶችንና በቅንነት ዕርቅ ማድረግን ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ ማስተናገድ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ከባድ ኀላፊነት ነው::

## 4. ስለ መሐላ

[33]ስቀደሙት ሰዎች፣ በሐሰት አትማል፤
በእግዚአብሔር ፊት የማልኸውንም ጠብቅ እንደ ተባለ — ማቴ 5÷33-37
ሰምታችኋል:: [34]እኔ ግን ፈጽሞ አትማሉ እላችኋለሁ፤
በሰማይም ቢሆን አትማሉ፤ የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤ [35]በምድርም ቢሆን አትማሉ፤
የእግዚአብሔር የእግሩ ማረፊያ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም አትማሉ፤ የታላቁ ንጉሥ ከተማ
ናትና፤ [36]በራሳችሁም ቢሆን አትማሉ፤ ካጠጉራችሁ መካከል አንዲቷን እንኳ ነጭ
ወይም ጥቁር ማድረግ አትችሉምና:: [37]ስለዚህ ስትነጋገሩ ቃላችሁ አዎን ከሆነ፣
አዎን፤ አይደለም ከሆነ አይደለም ይሁን፤ ከዚህ ውጭ የሆነ ሁሉ ከክፉው የሚመጣ
ነውና::

ኢየሱስ እየተናገረ ያለው በቀጥታ ከብሉይ ኪዳን በመጥቀስ አልነበረም:: ሐሰት ስለ መናገርና ስለ መሐላ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች የሚናገሩትን በአጭሩ ብቻ ነበር ያቀረበው (ዘፀ 20÷7፤ ዘሌ



19÷12፤ ዘኁ 30÷2፤ ዘዳ 23÷21-24):: ፈሪሳውያን መሐላን የሚጠቀሙበት የሌላውን እምነት ለማጽናት ሳይሆን እነርሱ ራሳቸው የገቡትን ቃል ለማድበስበስ ነበር:: ሃይማኖታዊው የአይሁዶ መጣጥፍ የትኛው መሐላ አሳሪ እንደ ሆነ የትኛው ደ'ሞ እንዳልሆነ ይዘረዝራል::

በፈሪሳውያን አስተሳሰብ መሠረት በሰማይ ወይም በምድር ወይም በእግዚአብሔር ዙፋንም ሆነ በኢየሩሳሌም መማል (ቁ 34-36፤ ማቴ 23÷16-22 ጋር ያነ) በራሱ በእግዚአብሔር መማልን ያህል አሳሪ አልነበረም:: ኢየሱስ ደግሞ እነዚህ አራት ነገሮች በተለየ ሁኔታ የእግዚአብሔር መሆናቸውን ይገልጻል:: የጠጉራችን ቀለም እንኳ አሁን ያለው ዐይነት እንዲሆን የተወሰነው በእግዚአብሔር ነው:: ስለሆነም የእነዚህ ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር ከሆነ መሐላዎች ሁሉ የእርሱን እውነት ገጽታ ማንጸባረቅ ይኖርባቸዋል ማለት ነው:: ይህን አመክንዮ በሰማይም ሆነ በምድር ያሉ ነገሮችን በሚመለከት ሁኔታ ማስፋት ይቻላል::

አንዳንዶች የኢየሱስን አነጋገር ከሚገባው በላይ ቃል በቃል ከመውሰዳቸው የተነሣ በማንኛውም ሁኔታ፣ ሌላው ቀርቶ በፍርድ ቤት እንኳ መሐላ ማድረግ አይፈልጉም:: ይሁን እንጂ በብሉይ ኪዳንም ሆነ (ዘዳ 10÷20) በአዲስ ኪዳን (ሮሜ 1÷9፤ 2ቆሮ 1÷18፣23፤ ገላ 1÷20፤ 1ተሰ 2÷5፣10) በአግባቡ መማል እንደሚቻል ምሳሌዎች ማቅረብ ይቻላል:: ኢየሱስ ራሱ ለፍርድ በቀረበ ጊዜ ለሊቀ ካህናቱ በመሐላ ነበር የመለሰለት (ማቴ 26÷63-64):: ኢየሱስ የተቃወመው፣ መሐላን ሌላውን ለማታለል በሚመች ሁኔታ መጠቀምን ነበር:: እንዲህ ከሆነ ልትል የምትፈልገውን ተናገር፣ የምትናገረውንም ሁነው (ያዕ 5÷12):: ዋናው ጉዳይ የተጠራነው ታማኞች እንድንሆን መሆኑን ማወቅ ነው:: እንደዚያ ካልሆነ ግን የሐሰት ሁሉ አባት ለሆነው ለክፉው ተፅዕኖ እየተገዛን ነው ማለት ነው (ዮሐ 8÷44)::

### 5. በቀል

[38]ዓይን ስለ ዓይን፣ ጥርስ ስለ ጥርስ እንደ
ተባለ ሰምታችኋል። [39]እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ክፉ ማቴ 5÷38-42
አድራጊውን ሰው አትቃወሙት፤ ነገር ግን ቀኝ ጉንጭህን
ለሚመታህ ሌላውን ጉንጭህን ደግሞ አዙርለት። [40]አንድ ሰው እጀ ጠባብህን ሊወስድ
ቢከስህ ካባህን ጨምረህ ስጠው። [41]አንድ ሰው አንድ ኪሎ ሜትር ተኩል የሚያህል
ርቀት እንድትሄድ ቢያስገድድህ ዕጥፉን መንገድ አብረኸው ሂድ። [42]ለሚለምንህ ስጥ
ከአንተም ሊበደር የሚሻውን ፊት አትንሣው።

ብሉይ ኪዳን ዐይነትን በዐይነት መመለስን ይደግፋል (*Lex Talionis*፣ ዘፀ 21÷24፤ ዘዳ 19÷21)። አንዳንዴ ሰዎች የሚበቀሉት የበደላቸውን ሰው በመክሰስ[73] ሲሆን፣ የብቀላው መጠን ከተፈጸመው በደል የበለጠ ሊሆን ይችላል። ኢየሱስ ግን፣ እንደ ፈጸመው ሁሉ፣ ከመበቀል ይልቅ ራስን መሥዋዕት ማድረግን መርጧል። ይህን ከብቀላ የጠራ መንገድ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ሦስት መርሖዎች አስቀምጧል። እነዚህን ሦስት መርሖዎች በሚገባ መረዳት የሚቻለው ከአይሁድ ባሕል አንጻር ያየናቸው እንደሆነ ነው።

(1) በጥፊ መምታት የተለመደ የስድብ ዐይነት ሲሆን፣ ለእንዲህ ዐይነቱ ጉዳይ በዐይነት መመለስ የሚጠበቅ ነበር። ይህ ዐይነትን በዐይነት የመመለሱ ሂደት ከፍ እያለ ይሄድና ወደ ለየለት ትንንቅ ሊያመራ ይችላል። (2) በፍርድ ቤት በመያዣነት እንዲያገለግል እጀ ጠባብ ይጠየቅ ነበር (ዘፀ 22÷26-27)። ኢየሱስ፣ «አንድ ሰው እጀ

[73] S.D. Currie, "Mt 5:39a – Resistance or Protest" *HTR* 57 (1964): 140-145 ላይ ይህን በተመለከተ ከሕግ ጋር የተያያዙ ብዙ ጉዳዮች መኖራቸውን ያመለክታል። በተጨማሪም፣ «መቃወም» [*anistemi*] የሚለው የፍርድ ቤት ቃል ሲሆን «በሌላው ላይ መመስከር» ማለት ነው። ስለዚህም ኢየሱስ «ጠላቶቻችሁን በተመለከተ አላዋቂ አትሁኑ፤ ይልቁንም ለመብታችሁ ተከራከሩ»፣ ወይም፣ «ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት አትውሰዱ። ጉዳት አትፈለጉ» ማለቱ ሊሆን እንደሚችል አመልክቷል።



ጠባብህን ሊወስድ ቢከስህ ካባህን ጨምረህ ስጠው» አለ። (3) የሮም ወታደሮች ማንኛውንም ተራ ዜጋ ወታደራዊ ዕቃዎቻቸውን የማሸከም መብት ነበራቸው። ይህን በተመለከተ ነበር ኢየሱስ አንድ ኪሎ ሜትር እንድትሄድ ቢያስገድድህ ሁለት አድርግለት ያለው።

እነዚህ ሦስት ምሳሌዎች (ደንቦች አይደሉም) አንድን መርሕ፣ ያም በቀል አስፈላጊ አለመሆኑን ነው የሚያመለክቱት። ምናልባትም እነዚህ ሦስት ምሳሌዎችን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ የማይሞከርበት ወይም ጨርሶ የማይቻልባት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ከዚህም በላይ እነዚህን ነገሮች ተግባር ላይ የምናውልበት መንፈስ ወሳኝ ነው፤ ምክንያቱም ነገሮችን ግምት ውስጥ ሳናስገባ አለመበቀልን ተግባር ላይ ለማዋል የምናደርገው ሙከራ ኢየሱስንም ላያስከብር ይችላልና ነው፤ ከዐውዱ ሐሳብም ጋር የተጣጣመ አይደለም።

ኢየሱስ እነዚህን ቃላት ሲናገር፣ (1) ክርስቲያን ማንኛውንም ስቃይ በቸልታ መቀበል አለበት ማለቱ አልነበረም፤ (2) አጉል ሰላም ወዳድነትን ወይም ተገቢ ጦርነትን በመደገፍ መናገሩ አልነበረም፤[74] (3) ሌላ ሦስተኛ ወገን ያለ አግባብ ሲጠቃ ክርስቲያን ቆሞ ማየት አለበት ማለቱ አልነበረም፤ (4) ራስን ለመከላከል የሚደረግ ሙከራን እየተቃወመ አልነበረም፤ (5) መንግሥት ወንጀለኛን መቅጣት የለበትም ማለቱም አልነበረም። ብሉምበርግ የኢየሰሱ ዐላማ ምን እንደ ነበር በአጭሩ ሲያመለክት፣ «ደቀ መዛሙርት በቀልን መሠረት ያደረገ ተነሳሽነትን አለመፈለግ ብቻ ሳይሆን፣ ለማይመቿቸው ሰዎች እንኳ መልካም ለማድረግ ዝግጁ መሆን አለባቸው» ብሏል (ገጽ 113)።

ቁጥር 42 ላይ ኢየሱስ እውነተኛ ችግር ስላለባቸው ሰዎች ይናገራል። ለምሳሌ አንድ ሰው አጉል ሱሱን እንዲያረካ ወይም በአጉል መንገድ መበልጸግ ለሚፈልግ ሰው ብር እንድናበድር አልተጠየቅንም።

[74] Cf. J. Rausch, "The Principle of Nonresistance and Love of Enemy in Mt 5:38-48," *CBQ* 28 (1966): 31-41.

አውጉስጢኖስ ይህን የኢየሱስን አነጋገር ሲያብራራው፣ «ለሚጠይቅህ ሁሉ ስጥ» እንጂ፣ «ለሚጠይቅህ ሁሉ ማንኛውንም ነገር ስጥ አልተባለም» ብሏል (*De Sermone Domine en Monte,* 67)፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን በአጭበርባሪዎች መታለል የለብንም፡፡ እውነተኛ ችግርን አይተን እንዳላየን ከማለፍ ይልቅ ግን በሌሎች መታለል ይሻላል፡፡

### 6. ፍቅር (በተጨማሪ ሉቃ 6÷27-30፤32-36)

**ማቴ 5÷43-47**

43«ወዳጅህን ውደድ፤ ጠላትህን ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል፡፡ 44እኔ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ እላችኋለሁ፡፡ 45እንደዚህም በማድረጋችሁ በሰማይ ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆናላችሁ፤ እርሱ ፀሓዩን ለክፉዎችና ለደጎች ያወጣል፤ ዝናቡንም ለኃጢአተኞችና ለጻድቃን ያዘንባል፡፡46የሚወዷችሁን ብቻ የምትወዱ ከሆነ ምን ዋጋ ታገኛላችሁ? ቀራጮችስ ይህንኑ ያደርጉ የለምን? 47ወንድሞቻችሁን ብቻ እጅ የምትነሡ ከሆነ ከሌሎች በምን ትሻላላችሁ? አሕዛብስ ይህንኑ ያደርጉ የለምን?

**ሉቃ 6÷34-35**

34ብድር ይመልሳሉ ለምትሉት ብታበድሩ ምን የተለየ ዋጋ ታገኛላችሁ? ኃጢአተኞችም እንኳ ያበደሩትን ያህል መልሰው ለመቀበል ለኃጢአተኞች ያበድራሉ፡፡ 35ነገር ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ መልካም አድርጉ፤ መልሳችሁ ለመቀበል ተስፋ ሳታደርጉም አበድሩ፤ በዚህም ወሮታችሁ ታላቅ ይሆናል፤ የልዑልም ልጆች ትሆናላችሁ፤ እርሱ ለማያመሰግኑና ለክፉዎች ቸር ነውና፡፡

**ማቴ 5÷48 ከሉቃ 6÷36 ጋር**

48ስለዚህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም (ርኅሩኅ[ሉቃ]) እንደሆነ እናንተም ፍጹማን (ርኅሩኆች) ሁኑ»፡፡

ከዘሌዋውያን 19÷18፣ «ባልንጀራህን ውደድ» የሚል እናነባለን፡፡ «ጠላትህን ጥላ» የሚል ግን ከየትኛውም የብሉይ ኪዳን ክፍል



እናነብም፡፡ ምናልባት ከዘዳግም 23÷36፣ 25÷17-19 ወይም ከመዝሙር 139÷21 የተወሰደ ነው ቢባል እንኳ ጨርሶ የሚያስኬድ አይሆንም፡፡ ምናልባትም፣ «ባልንጀራህን ብቻ ውደድ» በሚል መልኩ አንብበውት ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ፀሐዩን በማውጣትና ዝናቡን በማዝነብ ለኀጢአተኞችም ሳይቀር ለሰዎች ሁሉ ፍቅሩን ገልጿል (ዮሐ 3÷16፤ ሮሜ 5÷8 ጋር ያነ)፡፡ እንግዲህ በእርግጥ ልጆቹ ከሆንን፣ ያም ማለት የእርሱ ባሕርይ ካለን በሰዎች መካከል ልዩነት ሳናደርግ ሁሉንም መውደድ ይኖርብናል ማለት ነው፡፡ በአንድ በኩል ይህ ያለ መበቀል ሌላው ገጽታ መሆኑ ነው በአንድ በኩል ጠላቶቻችንን መበቀል የለብንም ማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በፍቅር መልካም ልናደርግላቸው ይገባል ማለት ነው፡፡

በአይሁዳውያን አስተሳሰብ የቀረጥ ሰብሳቢን ያህል የሚጠላ ሰው አልነበረም (ቁ 46)፤ ምክንያቱም ሐሰተኞች አማልክትን ያመልኩ ለነበሩ ሮማውያን ሕዝባቸውን እያስበዘበዙ ነበር (ቁ 47)፡፡ በእርግጥም እነዚያ መልካም መስለው የሚታዩ ሃይማኖተኞች ከሚንቋቸው አረማውያን የተሻሉ ሊሆኑ ይችሉ ነበር፡፡ ሆኖም የሃይማኖት ባለ ሥልጣኖችም ቢሆኑ ተግባራቸው እንደ ኀጢአተኞች ነበር፡፡ እነርሱ የሚወዱት እንደ እነርሱ የሆኑትን ብቻ ነበር፤ በዐይነት ሊከፍሉዋቸው የሚችሉትን ብቻ ነበር፡፡ ሉቃስ 6÷34-35 ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ሁኔታ አቅርቦታል፡፡ እንዲመለስላችሁ ተስፋ በማድረግ ብታበድሩ መሥዋዕት ያደረጋችሁት ነገር የለም ማለት ነው፡፡ እንዲመለስላችሁ ተስፋ ሳታደርጉ ብታበድሩ ግን አረማውያን ከሚያደርጉት የበለጠ ነገር አድርጋችኋል ማለት ነው፡፡

ጽድቃችን ከፈሪሳውያን ጽድቅ ይልቅ ጥልቀት ያለው ሊሆን እንደሚገባ እስከ አሁን ድረስ ስድስት የተለያዩ ምሳሌዎችን ስንመለከት ነበር (ቁ 21-47)፡፡ ምንም እንኳ የመንግሥቱ ዜጋ እንዴት ዐይነት እንደሆነ አጠቃላይ ምስል ቢሰጥም የተሟላ ዝርዝር ነበር ማለት ግን

አይቻልም:: እነዚህን ነገሮች ተግባር ላይ ካዋልን የሰማይ አባታችንን ባሕርይ እናሳያለን:: ስለሆነም እግዚአብሔር ፍጹም እንደሆነ ሁሉ እኛም፣ «ፍጹማን» ሆነናል (ቁ 48):: ይህ ግን ከፍተኛ ሥራና ሁለንተናን የሚጠይቅ ነው፤ እንዴት አድርጌ እንደ እግዚአብሔር መሆን እችላለሁ?

«ፍጹም» የሚለው የግሪክ ቃል [*teleios*] «እንከን የለሽ» ማለት ሳይሆን፣ «በሳል፣ የተሟላ፣ አስተዋይ» ማለት ነው:: ይህን ቃል ወንጌሎች ውስጥ ሌላ ቦታ የምናገኘው አንዴ ብቻ ነው (ማቴ 19÷21):: ኢየሱስ ለዚያ ወጣት ባለጠጋ፣ «ፍጹም ለመሆን ከፈለግህ፣ ሄደህ ንብረትህን ሁሉ ሸጠህ ገንዘቡን ለድኾች ስጥ» ብሎት ነበር:: ይህም እስካሁን ስንመለከት ከነበረው ሥር ነቀልና ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ከማያስገባ ፍቅር ጋር ይስማማል (ቁ 43-48):: ስለሆነም ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ሁሉ ምንም በደል የሌለብን ንጹሐን እንድንሆን እየተናገረ አልነበረም:: ይልቁንም እርሱ እየተናገረ ያለው እግዚአብሔር ሰዎችን በሚወድበት ዐይነት ፍቅር በሳል፣ የተሟላና አስተዋይ ዐይነት ፍቅር ሊኖረን ይገባል ማለት ነው:: ይህም ማለት ክፉዎችንም ደጎችንም፣ ጠላቶቻችንንም ወዳጆቻችንንም ጭምር መውደድ እንዳለብን ያስገነዝባል:: ሉቃስ (6÷36) ለመውደድ የሚያስቸግሩ ሰዎችን ስለ መውደድ ሲናገር፣ «አባታችሁ ርኅሩኅ እንደ ሆነ እናንተም ርኅሩኆች ሁኑ» ይላል:: ይህን ማድረግ ከባድ ቢሆንም ጨርሶ የማይቻል ግን አይደለም::

ምናልባትም ይህ አባባል፣ «እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» የሚለውን ዘሌዋውያን 19÷2 ላይ ያለውን የሚያሳስብ ሊሆን ይችላል::[75] የሰማያዊ መንግሥት ዜጎችም፣ «እግዚአብሔር ፍቅር እንደ ሆነ፣ እናንተም ሌሎችን ውደዱ» በተባለው መሠረት የንጉሡን ማንነት ማንጸባረቅ ይኖርባቸዋል::

[75] B.B. Thurston, "Mt 5:43-48," *Int* 41(1987): 170-173.



**§ 54ሸ**
**የሌሎችን ትኩረት ለመሳብ የሚደረግ ምጽዋት፣ ጸሎትና ጾም የተከለከለ መሆኑ (ማቴ 6÷1-18)**

ምዕራፍ አምስት ከሰዎች ጋር ሊኖረን ስለሚገባው ምግባር ስድስት ምሳሌዎች ያቀርባል (ቁ 21-48):: ስድስቱንም ጊዜ ኢየሱስ፣ «የልባችሁን ዝንባሌ መርምሩ» ብሏል:: ምዕራፍ ስድስት ሦስት ሃይማኖታዊ ምግባርን የሚመለከቱ ምሳሌዎች ይሰጣል፤ ስለ ምጽዋት (2-4)፣ ስለ ጸሎት (5-13) እና ጾም (14-18):: ሦስቱንም ጊዜ ኢየሱስ፣ «የልባችሁን ዝንባሌ መርምሩ» ይላል:: ማኅበራዊ ግብረ ገብም ሆነ ሃይማኖታዊ ሥርዐት በእግዚአብሔር ያለንን እምነት የምንገልጽባቸው ተገቢ ምግባሮች ናቸው:: ይሁን እንጂ ሁለቱንም ለተሳሳተ ዓላማ ልንጠቀምባቸው እንችላለን:: ኢየሱስ፣ «የልባችሁን ዝንባሌ መርምሩ» በማለት የሚያስጠነቅቀንም በዚህ ምክንያት ነበር::

በምዕራፍ አምስትና ስድስት መካከል ያለው ሌላ ተጓዳኝ ሐሳብ ደግሞ፣ «እነርሱን አትምሰሏቸው» የሚለው የኢየሱስ ምክር ነው:: «እነርሱ» ሲል ግብዞቹ፣ ፈሪሳውያንና (ማቴ 5÷20፤ 6÷5) አሕዛብን ይጨምራል (ማቴ 5÷46-47፤ 6÷7):: የተራራው ስብከት ሕይወታችን የተለየ መሆን እንዳለበት ጠንከር ያለ ጥሪ ማቅረቡን ቀጥሏል፤ ከሃይማኖታዊ ግብዞችና ከአሕዛብ መለየት አለብን::

> እውነተኛ ፍጽምና እንዲኖረን የቀረበው ጥሪ ውጫዊ ሃይማኖተኝነትን ወደ ሙሰስ ዝቅተኛ ግብ ሲወርድ ይችላል፤ እግዚአብሔርን ደስ የማሰኘት ግብ፣ ሰዎችን ደስ ወደ ማሰኘት ዝቅ ሲል ይችላል:: የቅድስናው ጥሪ ከፍ የማለቱን ያህል ወደ ግብዝነት የመውረዱ ዕድልም የዚያኑ ያህል ከፍ የሚል ይመስላል:: አደጋው በሃይማኖት መሪዎች ላይ የከፋ ሲሆን ይችላል በማለት የማስበው በዚህ ምክንያት ነው፤ ፍጹም ሁኑ (5÷48)፤ ሆኖም ተጠንቀቁ (6÷1) «Carson» (ገጽ 55)::

[1]ሰዎች እንዲያዩላችሁ፣ መልካም ሥራችሁን በፊታቸው ከማድረግ ተጠንቀቁ፤ እንዲህ ካደረጋችሁ ከሰማዩ አባታችሁ ዋጋ አታገኙም። ማቴ 6፥1

የምዕራፍ ስድስት መጀመሪያ ቁጥር የዚህን ክፍል ዐብይ ሐሳብ ያቀርባል፣ ያም ነገሮችን በምሥጢር መያዝ መንፈሳዊነት እንደሆነ። ይሁን እንጂ ማቴዎስ 5÷16 ላይ ክርስቲያኖች ብርሃናቸው በሰው ሁሉ ፊት መታየት እንዳለበት መታዘዛቸው ይታወሳል። ሁለቱም ጥቅሶች አጽንዖት የሚሰጡት፣ (1) በሰዎች ፊት፣ (2) እንዲያዩላችሁ፣ እና (3) እግዚአብሔርን ማክበር ላይ ነው። ማቴዎስ 5÷16 በሰዎች ስለ መታየት ሲናገር፣ ማቴዎስ 6÷1 ግን ሁሉም ነገር በምስጢር መያዝ እንዳለበት ያመለክታል። ታዲያ ሁለቱን እንዴት ማጣጣም ይቻላል?

የሚቃረን የመሰለን በአንደበት መናገርን ብቻ የሚመለከት ነው። ክርስቲያኖች መሆናችንን፣ በተለይ ደግሞ ተቃውሞ በሚያይልበት ጊዜ ክርስቲያኖች መሆናችንን የመደበቅ ፈተና ሲገጥመን፣ ማቴዎስ 5÷16 ላይ ያለውን እናስታውስ። በሃይማኖታዊ ምግባሮቻችን፣ በተለይም ከቤተ ክርስቲያን ጋር በተያያዘ መልኩ ራሳችንን የማስተዋወቅ ፈተና ሲገጥመን ማቴዎስ 6÷1ን ልብ እንበል።

ከዚህ ስብከት ሌሎች ትእዛዞች እንደ ተመለከትነው ሁሉንም በተግባር መተርጐም ተገቢ ላይሆን ይችላል። ለምሳሌ ያህል ምጽዋት መስጠታችንን ከግራ እጃችን መደበቅ አይቻልም። ከዚህም ባለፈ በሕዝብ ፊት ይህን ያህል እሰጣለሁ በማለት ቃል መግባት ግለሰቡን ከፍ ከማድረግ ይልቅ ለሌሎች ክርስቲያኖች ታላቅ ማበረታቻ ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ ሐሥ 4÷36-37፤ 21÷24፤ ፊልጵ 4÷14-18)። በሕዝብ ፊት መጸለይንስ የሚቃወም ማነው? ጳውሎስስ በጋራ ስለሚደረግ ጸሎትና ጾም ተናግሮ የለ (1ቆሮ 7÷5)? እዚህ ላይ ኢየሱስ እየተቃወመ ያለው



ድርጊቱን ሳይሆን ከድርጊቱ በስተጀርባ ያለውን የተሳሳተ ዓላማ ነው (ከ5÷22፣28፣44 ጋር ያነ)።

## ስለ ምጽዋት አሰጣጥ

[2]በሰዎች ዘንድ ለመከበር ብለው በየጐዳናውና በየምኩራቡ ጥሩምባ እንደሚያስነፉ ግብዞች፣ እናንተም ለድኾች ምጽዋት በምትሰጡበት ጊዜ ደታደልኝ ብላችሁ አታድርጉ፤ እውነት እላችኋለሁ እንዲህ የሚያደርጉ ዋጋቸውን በሙሉ ተቀብለዋል። [3]እናንተ ግን ለድኾች ስትሰጡ ቀኝ እጃችሁ የሚያደርገውን ግራ እጃችሁ አይወቅ፤ [4]ምጽዋታችሁ በስውር ይሁን፤ በስውር የተደረገውን የሚያይ አባታችሁም ዋጋችሁን ይከፍላችኋል። ማቴ 6፥2-4

አይሁድ መንግሥታዊ የማኅበረሰብ ደኅንነት ወይም ድኾችን የሚረዳ ተቋም አልነበራቸውም። ስለሆነም ለድኾችና አካለ ስንኩላን በፈቃደኝነት መመጽወት በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነበር (ዘዳ 15÷11፤ መዝ 41÷1፤ ምሳ 19÷17)።[76] ብዙውን ጊዜ ገንዘብ ይሰጥ የነበረው ድኾችን ለመርዳት ወይም እግዚአብሔርን ለማክበር ሳይሆን የራስን ሃይማኖተኝነት ለማሳየት ነበር። «በየጐዳናውና በየምኩራቡ ጥሩምባ እንደሚያስነፉ» ሲል ምሳሌያዊ አነጋገር ይሁን፣ ወይም ቃል በቃል መወሰድ ያለበት ግልጽ አይደለም። (በዘመናችንም ቢሆን፣ «ጥሩምባህን ንፋ» የሚል አገላለጽ መኖሩን እናውቃለን)። ምናልባትም የተለያዩ ሙዳዮች ላይ ሳንቲም ሲወረውሩ የሚሰጠውን ድምፅ የሚመለከት ይሆናል ቢባል ተገቢ ግምት ይሆናል (ብሎመበርግ ገጽ 116)።[77] ስቶት

[76] በየሳምንቱ ዐርብ «የእርዳታ ሠራተኞች» ከቤት ወደ ቤት እየተዘዋወሩ ለድኾች ለ14 ጊዜ ቀለብ የሚሆን ምግብና ገንዘብ ይሰበስቡ ነበር። D. Gaertner, *Acts* (Joplin, MO: College Press, 1993), p. 119.

[77] N.J. McElency, “Does the Trumpet Sound or Resonnd?” *ZNW* 76 (1985): 43-46.

ደግሞ ድኾች ወደ ምጽዋት መቀበያው ቦታ እንዲመጡ ለመጥራት ጥሩምባ ይነፉ እንደ ነበር አመልክቷል።

ኢየሱስ እየተቃወመ ያለው ግብዝነትን ነው። ይህ ቃል ትክክለኛ ማንነታቸውን ለመሰወር የተለያዩ ጭምብሎችን ያጠልቁ የነበሩ የግሪክ ተዋናዮችን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የሚውል ነው። ወደ ቴአትር ቤት በተኬደ ጊዜ ሁሉ ጭምብል ያጠለቀ ሰው ሊኖር እንደሚችል ይጠብቁ ነበር። ሆኖም ማንም አይታለልላቸውም ነበር። በቤተ ክርስቲያን ግን እንዲህ ያለው ጉዳይ በፍጹም መታሰብ እንኳ የሌለበት ነው። ሰዎች መታወቅ ያለባቸው በትክክለኛ ገጽታቸው ብቻ መሆን አለበት። ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ገንዘብን በተመለከተ ስለሚኖረው ተጠያቂነት በመቃወም ወይም ደግሞ ለወጪ ስሌት ልግስናን በማስታወሻ ማስፈርን በማጣጣል አይደለም። ይልቁንም እየተቃወመ የነበረው የልግስና አድራጊዎቹ ስም ያለበትን ካርድ ከስጦታው ጋር ማያያዝንና ልግስና ያደረጉ ክርስቲያን ድርጅቶችን ጋዜጣ ላይ መዘርዘርን በተመለከተ ነው ቢባል የሚያስኬድ ይሆናል።

ዋጋችንን መቀበል የምንፈልገው ከማን መሆኑን መምረጥ አለብን (ቁ 4፣6፣18)። ፈሪሳውያን የሚወዱትን በሰዎች መመስገንን (ዮሐ 5÷44፤ 12÷43) ወይም በእግዚአብሔር መመስገንን መምረጥ አለብን። ከእግዚአብሔር ስለምንቀበለው ዋጋ ስናስብ የግድ ወደፊት የሚሆን እንደ ሆነ ማሰብ የለብንም (ለምሳሌ፣ መንግሥተ ሰማይ፣ አክሊል ወይም ሰማያዊ ቤት)። ጊዜአዊ ባርኮት፣ የጸሎት መልስ (ቁ 8)፣ የድኾች ችግር ሲቃለል በማየት የሚኖረን እርካታ፣ ፈተናን በድል መወጣት፣ ክርስቶስን የመምሰል ባሕርይን ማዳበርና የመሳሰሉ እዚህና አሁን የምንቀበላቸው በረከቶችን ማለት ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር የሚሰጠን ዋጋ ምንም ይሁን ምን፣ ከሰዎች ጊዜያዊ ምስጋና የበለጠ እንደሚሆን እርግጠኞች መሆን እንችላለን። ምንም እንኳ ምርጫው



ግልጽ ቢሆንም፣ አንዳንዴ ከሰዎች የምናገኘው ምስጋና ወይም ታዋቂነት የተሻለውን እንዳንመርጥ ሊያታልለን ይችላል።

## ጸሎት

**ማቴ 6፥5-8**



[5]«ስትጸልዩ እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ እነርሱ
ለሰዎች ለመታየት ሲሉ በየምኩራቡና በየመንገዱ ማእዘን
ላይ ቆመው መጸለይ ይወዳሉና። እውነት እላችኋለሁ፤
ሙሉ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። [6]አንተ ግን ስትጸልይ ወደ
ክፍልህ ግባ፤ በሩንም ዘግተህ በስውር ወዳለው አባትህ
ጸልይ፤ በስውር የተደረገውን የሚያይ አባትህ ዋጋህን ይከፍልሃል። [7]ስትጸልዩ ከንቱ
ቃላት በመደጋገም ጸሎታቸው የሚሰማላቸው እንደሚመስላቸው አሕዛብ ነገሬችሁን
አታስረዝሙ። [8]እነርሱን አትምሰሏቸው፤ አባታችሁ ከመለመናችሁ በፊት ምን
እንደሚያስፈልጋችሁ ያውቃልና።»

እንደ ፈሪሳውያን በሰዎች ለመታየት (ቁ 5-6) ወይም እንደ አሕዛብ፣ «ከንቱ ቃላት በመደጋገም» መጸለይ የለብንም (ቁ 7-8)። ኢየሱስ እንዲህ ሲል በሕዝብ ፊት የሚደረግ ጸሎትን መቃወሙ እንዳልሆነ መረዳት አለብን (ሐሥ 1÷24፤ 3÷1፤ 4÷24 ጋር ያነ)። እርሱ የተቃወመው በእውነት ለእግዚአብሔር ልመና ከማቅረብ ይልቅ አድማጮቹን የሚሰብክ ጸሎትንና የሰዎችን ይሁንታና አድናቆት ለማግኘት የሚደረግ ጸሎትን ነበር።

ሁለተኛ፣ ኢየሱስ የተቃወመው በድጋሚ ጸሎታችንን ማቅረብን አይደለም፤ ምክንያቱም እርሱ ራሱ በጸሎት መትጋት እንዳለብን ተናግሯል (ማቴ 7÷7-8፤ ሉቃ 1÷15-13፤ 18÷1-8)። እርሱ መልካሙን ሁሉ ሊሰጠን ስለሚወድ (ማቴ 7÷11) እግዚአብሔርን መነዝነዝ የለብንም፤ ይሁን እንጂ አንዳንድ ነገሮችን የሚሰጠው ለሚጸልዩ ሰዎች ብቻ ነው (ያዕ 4÷2)። ኢየሱስ የተቃወመው፣ «ከንቱ ቃላት መደጋገምን» ነው። መደጋገም የሚለው የተተረጐመው ከየትኛው

የግሪክ ቃል እንደሆነ በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም:: ይሁን እንጂ የሚያመለክተው ምን እያልን እንደሆነ እንኳ ሳናስብ በቃል የተጠና ጸሎት ማነብነብን፤ ጸሎትን ለማስረዘም ወይም የእግዚአብሔርን ትኩረት ለመማረክ በመሞከር ቃላት ማብዛትን ሊሆን ይችላል:: አረማውያን ትርጉማቸውን የሚያውቋቸውን ቃላት በመድገም አማልክቶቻቸው ጸሎታቸውን እንዲሰሙላቸው ማድረግ ይሞክራሉ:: እንዲህ ያለው በድግምት ወቅት አሕዛብ የሚያዘወትሩት ዐይነት የቃላት ጋጋታ የእግዚአብሔርን ይሁንታ ማግኘት አይችልም::

ስለሆነም ኢየሱስ የሚያስጠነቅቀው በጸሎት ጊዜ ከምንፈጽማቸው ሁለት ስሕተቶች እንድንጠበቅ ነበር:: የሰዎችን ትኩረት ለመማረክ በመሞከር መጸለይ የለብንም:: የምንፈልገውን እንዲሰጠን እግዚአብሔርን ወደ እኛ ፈቃድ ማምጣት እንደሚቻል በማሰብ መጸለይ የለብንም:: መጸለይ ያለብን ችግራችንን በፊቱ ለማኖርና ከእግዚአብሔር ጋር ተገቢ ግንኙነት ለማድረግ ብቻ መሆን አለበት::

## አርዓያ ጸሎት

ይህ ጸሎት በተለምዶ፣ «የጌታ ጸሎት» የምንለው ነው (ዮሐ 17 ላይ ያለውን ጸሎት እንዲህ ብንል ይበልጥ ትክክል ይሆናል):: እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እዚህ ላይ ያለው፣ «የደቀ መዛሙርቱ ጸሎት» ወይም፣ «አርዓያ ጸሎት» ሊባል ይችላል:: ክርስቲያኖች በዚህ መሠረት በቀን ሦስት ጊዜ መጸለይ እንዳለባቸው በደዳኬ (*Didache*) ተመልክቷል (8÷3):: ይሁን እንጂ አንዳንዶች ይህን የሚጸልዩት በተለምዶ ብቻ መሆኑና (ከቁ 7-8 ጋር ያነ)፣ ሌሎችም አርዓያነቱ ቀርቶባቸው (ቁ 9 ጋር ያነ) ይህን ጸሎት የሚጠቀሙት አልፎ አልፎ ብቻ መሆኑ በመጠኑም ቢሆን ግራ ያጋባል:: እዚህ ላይ እያየን ያለነው አርዓያ ሊሆነን የሚችል እንጂ፣ ጸሎታችን ሁሉ የግድ ይህን መምሰል



እንዳለበት አይደለም::[78] አንድ ጸሎት ማካተት ያለበት እግዚአብሔርን ማክበርን፣ ለእግዚአብሔር መገዛትን፣ ኀጢአትን መናዘዝንና ልመናን ነው:: በሌላ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ጸሎትን እንዲያስተምራቸው ሲጠይቁ ቃል በቃል ይህንኑ ጸሎት በድጋሚ ማቅረቡ ይህን ያህል ሊያስገርመን አይገባም (ሉቃ 11÷2-4)::

ማቴ 6÷9 «እናንተ ግን እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ፤ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤ ስምህ ይቀደስ::»

ጸሎት በኅብረት መደረግ ያለበት መሆኑ፣ «አባታችን» ከሚለው የመጀመሪያው ቃል መመልከት ይቻላል:: እዚህና እዚያ የተገነጣጠልን ሳይሆን በአንድነት የተያያዝን አካል ነን:: በግል ብንጸልይ እንኳ ከቤተ ክርስቲያን ጋር በተያያዘ መልኩ እየጸለይን ነው:: ስለሆነም ስለ ዕለት እንጀራችን፣ ስለ ኀጢአታችን ይቅርታና ከፈተና እንዲያድነን እንጸልያለን::

ሁለተኛው ቃል ከእግዚአብሔር ጋር ምን ያህል የተቀራረብን መሆናችንን ያመለክታል:: «አባት» የሚለው የግሪክ ቃል፣ ኢየሱስ ከተጠቀመበት፣ «አባ» ከሚለው የአረማይክ ቃል ጋር ተመሳሳይ ሲሆን (ማር 14÷36፤ ሮሜ 8÷15፤ ገላ 4÷6 ጋር ያነ)፣ «አባት» ወይም፣ «አባባ» ከሚለው ቃል ጋር አንድ ዐይነት ትርጉም አለው:: ምንም እንኳ አይሁድ እግዚአብሔር አባታቸው እንደሆነ ቢያስቡም፣ እንደዚያም ቢናገሩም፣ ከእርሱ ጋር ይህን ያህል መቀራረብ መቻሉን ግን የአይሁድ

[78] S.J Kistemaker, "The Lord's Prayer in the First Century, "*JETS* 21/4 (1978): 323-338, ይህ ጸሎት በመጀመሪያው መቶ ዓመት በተለይም ከአይሁድ እምነት በመጡት ክርስቲያኖች ዘንድ አርዓያነት እንዳለው ጸሎት ይጠቀሙበት እንደ ነበር አመልክቷል::

ሃይማኖት አያስተምርም::[79] ልጅነታችን በክርስቶስ ካገኘነው ታላላቅ መብቶች አንዱና ዋናው ነው (ዮሐ 1÷12፤ 20÷17፤ ሮሜ 8÷14-17፤ 1ዮሐ 3÷1):: ይሁን እንጂ፣ ለእግዚአብሔር ስም (ለባሕርዩና ለማንነቱ) ሊኖረን የሚገባውን ክበሬታ ለማመልከት ኢየሱስ፣ «ስምህ ይቀደስ» የሚል ሐረግ ጨምሮአል:: የአይሁድ ሃይማኖት የእግዚአብሔር ትልቅነትና ከሁሉ በላይነት ላይ አጽንዖት በመስጠት ከማንም ጋር ግንኙነት ሊኖረው እንደማይችል አቅርቧል፤ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጌል አማኞች የእግዚአብሔር የቅርብ አምላክ መሆን ላይ ብቻ በማተኮር እንድንዳፈር አድርገዋል::

[10]«መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች፣ እንዲሁ በምድር ትሁን::»

ማቴ 6÷10

ይህ ስለ ኢየሱስ ዳግም በአካል መመለስ ብቻ የቀረበ ጸሎት አይደለም::[80] በሰማይ ባለው ዙፋኑ እንደ ሆነ ሁሉ የእግዚአብሔር አገዛዝ፣ ዓላማና ዕቅድ በዚህ ምድርም ሙሉ ለሙሉ እንዲፈጸም የቀረበ ጸሎት ነው:: ኢየሱስ ኀጢአትን ከመናዘዝ ወይም ልመናን ከማቅረብ በፊት እግዚአብሔርን እንዲያከብሩትና ለእርሱ እንዲገዙ ክርስቲያኖችን እያሳሰበ መሆኑ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነም እግዚአብሔር ማን መሆኑን፣ እኛም በፊቱ ማን መሆናችንን እስካልተገነዘብን ድረስ የሚገባንን ያህል መጸለይ አንችልም (ኢሳ 37÷15-20 ጋር ያነ)::

[79] D.E. Garland "The Lord’s Prayer in the Gospel of Matthew," *Rev & Expos* 89/2 (1992): 215-228.

[80] ይሁን እንጂ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ልመናዎች aorist imperative እንደመሆናቸው መጠን R.E. Brown ይህ ጸሎት የሚያመለክተው የመጨረሻውን ዘመን እንጂ አሁን ያለውን የክርስትና ዘመን አይደለም ብሏል:: “The Pater Noster as an Eschatological Prayer,” *TS* 22 (1961): 175-208 ይመ::



ማቴ 6÷11

[11]«የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን::»

«የዕለት» ተብሎ የተተረጐመው ይህ አልፎ አልፎ የሚያጋጥም ቅጽል ኤፒዮስዮስ [*epiousios*] ምን ማለት እንደ ሆነ ግልጽ አይደለም::[81] አንዳንዶች «የነገን» ማለት ሊሆን እንደሚችል ቢያመለክቱም አንድምታው ግን በግልጽ የሚታይ ነው:: መጸለይ ያለብን አሁን ላለው ችግራችን እግዚአብሔር መልስ እንዲሰጠን ነው::[82] ኢየሱስ ያገለግል በነበረበት ዘመን ሰዎች ደመወዝ የሚቀበሉት በየዕለቱ ነበር:: ብዙውን ጊዜ የሚከፈላቸው ለቤተሰባቸው ዕለታዊ ፍላጐት ማሟላት የሚችሉበትን ያህል ብቻ ነበር:: ስለዚህም አንድ ዐይነት ጉዳት ከደረሰባቸው ሥራ ማግኘት አይችሉም:: ምናልባትም በዚያ ቀን የሚበሉት እንኳ ላይኖራቸው ይችላል ማለት ነው:: በተጨማሪም የግብርና ማኅበረሰብ እንደ መሆናቸው መጠን ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ በየዕለቱ በእግዚአብሔር መደገፍ ነበረባቸው:: እርሻው ሰብል ካልሰጠና በረዶ፣ አንበጣ ወይም ሌላ ዐይነት ጥፋት ከደረሰበት የሚበሉት አይኖራቸውም:: በዚህ ዘመን ላለን ይህን መረዳት ሊከብደን ይችላል:: አንድ ወር ሙሉ ቀለብ ሊሆን የሚችል ምግብ ቤታችን ውስጥ እያለ የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን ብሎ መጸለይ ትርጉም የለሽ ሊሆን ይችላል:: ራሳችንን ሙሉ ለሙሉ በከለልንበት ሁኔታ በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ ሊያዳግተን ይችላል::

[81] በግሪክ ሥነ ጽሑፍ *epiousios* የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለበትን በትክክል መጠቀም» ባይቻልም፣ (B.M. Metzger, “How Many Times Does '*Epiousios*' Occur Outside the Lord's Prayer?” *ExpT* 69 [1957-58]: 52-54), E.M. Yamauchi, "The 'Daily Bread' Motif in Antiquity,” *WTJ* 28 (1966): 145-156 ላይ በተለመደው መልኩ፣ «የዕለት እንጀራ» ማለት ሊሆን እንደሚችል ተከራክረዋል::

[82] እንጀራ የተባለው የእግዚአብሔር ቃል ወይም የጌታ ራት ሊሆን እንደሚችል ብዙ ጥንታዊያን የቤተ ክርስቲያን አባቶች መንፈሳዊ ትርጉም ሰጥተውታል:: ከእንዲህ ዐይነቱ ክብርና ገናናነት ቀጥሎ ስለ እንጀራ መጸለይ ለእነርሱ ሥጋዊነት መስሎ ታይቷቸዋል::

12«እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል፣ ማቴ 6÷12
በደላችንን ይቅር በለን።

በደል የተባለው ምንድነው? ከቁጥር 14-15 እና ሉቃስ 11÷4 ላይ እንደምንመለከተው ኀጢአት መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ መንፈሳዊ አጸፋ አሠራር (*lex talionis*) ነው። እንዲህ ሲባል በደላችን ይቅር የሚባለው እኛም ሌሎችን ይቅር ባልንበት መጠን ነው ማለት ነው። ምክንያቱን መረዳት ይህን ያህል አዳጋች አይደለም። ሰዎች እኛን ከበደሉን ይልቅ እኛ እግዚአብሔርን የበደልነው በጣም ይበልጣል፤ ስለሆነም እኛ ራሳችን የበደሉንን ይቅር በማለት ፈቃደኞች ሳንሆን እግዚአብሔር የራሳችንን በደል ይቅር እንዲለን መጠበቅ ምክንያታዊ ሊሆን አይችልም። «እንዲህ ሲባል ግን ሌሎችን ይቅር ማለታችን እኛ ይቅር እንድንባል መብት ይሆነናል ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ይልቁንም እግዚአብሔር ይቅር የሚለው በንስሐ ፊቱ የሚቀርቡትን ብቻ ነው። ለዚህም ዋናው ማስረጃ ሌሎችን ይቅር ባይ መንፈስ ነው» (ስቶስ፣ ገጽ 149)። ይህ በትክክል ሌላውን ይቅር ለማለት ስላልፈለገው አገልጋይ የተነገረው ምሳሌ ዋነኛ ነጥብ ነው (ማቴ 18÷21-35)።

13ወደ ፈተናም አታግባን፣ ከክፉው አድነን
እንጂ። 14እናንተ የበደሏችሁን ይቅር ብትሉ የሰማዩ
አባታችሁ ደግሞ እናንተን ይቅር ይላችኋል። 15ነገር ግን
የሰዎችን ኀጢአት ይቅር የማትሉ ከሆነ አባታችሁ
ኀጢአታችሁን ይቅር አይልላችሁም።

ማቴ 6÷13-15

የዐረፍተ ነገሩ ሁለተኛው ሐረግ የመጀመሪያውን እንድንረዳ ያስችለናል። ጸሎታችን፣ «ጌታ ሆይ፣ እንድፈተን አታድርግ» ሳይሆን፣ «ፈተናው እስኪበረታብኝ ድረስ ፈተና ውስጥ አትተወኝ» የሚል መሆን አለበት። አንዳንድ ነገሮችን ግምት ውስጥ ማስገባት ኢየሱስ የተናገረውን



ለመረዳት ያስችለናል። (1) ኢየሱስ ራሱ ተፈትኗል (ማቴ 4÷1)፤ እኛም ከዚያ ያነሰ መጠበቅ የለብንም። (2) «ፈተና» ተብሎ የተተረጐመበት የግሪኩ ቃል አንድ ቢሆንም ሁለት ጽንሰ ሐሳቦችን ግን አዝሏል፡ ዋናው ነገርም ቃሉ የገባበት አግባብ ነው። እግዚአብሔር በፈተናው እንድንወድቅ አድርጐ አይፈትነንም (ያዕ 1÷13)። እግዚአብሔር የሚፈትነን ወደ ብስለት ሊያመጣን ነው (ያዕ 1÷2-4፤ 1ጴጥ 1÷6-9)። (3) እግዚአብሔር ፈተና ሲያመጣ የምንቋቋምበትንም ዐቅም አብሮ ይሰጠናል (1ቆሮ 10÷13)። ስለሆነም ጸሎታችን ሰይጣንን የምንቋቋምበት ዐቅም እንዲኖረን መሆን አለበት።[83]

«መንግሥት፣ ኃይል፣ ክብርም ለዘለዓለሙ ያንተ ነውና አሜን» የሚለውና በብዙዎቻችን ዘንድ የታወቀው የጸሎቱ መደምደሚያ በዳዳኬ (*Didache*)[84] ውስጥ ተካቶ ቢገኝም በመጀመሪያው የማቴዎስ ወንጌል ቅጂ ግን እንዳልነበር በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ይህ ክፍል ካልታከለበት ደግሞ የጸሎቱ መደምደሚያ ያልተለመደ ዐይነት ነው የሚሆነው። ስለሆነም ምናልባት 1ዜና መዋዕል 29÷11-13 ላይ ያለውን መሠረት በማድረግ የተጨመረ ሳይሆን አይቀርም። ይህም ሆኖ ግን እንደ አርዓያነት ከሚያገለግል ከዚህ ጸሎት ማውጣቱ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። ለጸሎቱ ያማረ መቋጫ ከመስጠቱ በላይ መኖሩ ምንም ችግር አይፈጥርም።

---

83 የፈተና ምንጭ ሰይጣን መሆኑ እስኪታወቀ ድረስ ቁ13ን «ክፉ» ወይም፣ «ክፉው» ተብሎ መተርጐሙ ይህን ያህል ለውጥ አያመጣም። See note in Brown, p. 207.

84 A. Bandstra, "The Lord's Prayer and Textual Criticism: A Response," *CTJ* 17 (1982): 88-97. ይሁን እንጂ J. Van Bruggen, "The Lord's Prayer and Textual Criticism," *CTJ* 17 (1982): 78-87 ላይ KJVን በመደገፍ ረዘም ያለው የጌታ ጸሎት ትክክል እንደሆነ ተከራክሮአል።

ማቴ 6÷16-18

[16]«ስትጾሙ እንደ ግብዞች ስትጠውልጉ፤ እነርሱ
ጠጾማቸው እንዲታወቅላቸው ሆነ ብለው በፊታቸው ላይ
የሐዘን ምልክት ያሳያሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፤ እንዲህ
የሚያደርጉ ዋጋቸውን በሙሉ ተቀብለዋል:: [17]አንተ ግን በምትጾምበት ጊዜ ፊትህን
ታጠብ፤ ራስህንም ተቀባ፤ [18]በዚህም ጠጾምህ በስውር ያለው አባትህ ብቻ
የሚያውቀው፣ ከሰዎች ግን የተሰወረ ይሆናል፤ በስውር የተደረገውን የሚያይ አባትህም
ዋጋህን ይከፍልሃል::»

ይህም ቢሆን እንደ ፊተኞቹ ነው:: ስንመጸውትም ሆነ ስንጸልይ ማድረግ እንዳለብን ሁሉ ስንጾምም ሰዎች መንፈሳዊነታችንን እንዲያውቁልን መሆን የለበትም፤ አለበለዚያ ዋጋ የምናገኘው ከሰዎች ብቻ ይሆናል:: መንፈሳዊ ልምምዳችንን በእግዚአብሔር ፊት ብቻ ብናደርግ ግን እርሱ ያየናል፤ ዋጋም ይሰጠናል:: ስለዚህ ስንጾም፣ (ኢየሱስ እንደዚያ እንደምናደርግ በመጠበቅ መናገሩን ማሰብ ይቻላል) ሁሌም እንደምናደርገው ፊታችንን ታጥበን፣ ጸጉራችንን አበጥረን ወደ ሥራችን መሄድ አለብን:: እንደሀ ሲባል ግን መጾማችንን ማንም አያውቅም ማለት አይደለም:: ለምሳሌ ያህል መጾማችንን ከትዳር ጓደኛችን መደበቅ አንችልም ይሁን እንጂ በየቦታው እየዞርን መጾማችንን ማውራት የለብንም:: እግዚአብሔርን ወይም ሰውን ደስ ከማሰኘት አንዱን መምረጥ አለብን::

እዚህ ላይ ያለውን ሐሳብ ሁሉ (ማቴ 6÷1-18) «በዋነኛነት እንዲያውቅላችሁ የምትፈልጉት ማንን ነው?» በሚል ጥያቄ ማጠቃለል ይቻላል:: ሁልጊዜ ሃይማኖታችንን በምስጢር መያዝ አይቻልም፤ እንዳንዴም ተገቢ ላይሆን ይችላል:: ምንጊዜም ሰዎች ያዩናል፤ የምናደርገውንም ይከታተላሉ፤ ግን የምናደርገው ለእነርሱ ለማሳየት ነው? ወይስ ሰዎች ቢያዩንም ባያዩንም የራሳችንን መንፈሳዊ ሕይወት



እንለማመዳለን? እውነተኛ የመንግሥቱ ዜጋ የሚመዘነው እዚህ ላይ ነው::

## ሀብት 6÷19-24

**§ 54ሠ**
**ሦስት የተከለከሉ ነገሮች፣**
**(ማቴ 6÷19-76፤ ሉቃ 6÷37-42)**

ገንዘብ ጊዜና ቀልባችንን አብዝቶ ከመውሰዱ የተነሣ ልናመልከው የሚገባውን እግዚአብሔርን ከስፍራው ያርቅብናል (ኤፌ 5÷5):: ብዙ ጊዜ:: ቤተ ክርስቲያን ስለ ገንዘብ ማስተማር ትፈራለች:: ኢየሱስ ግን እንደዚያ አልነበረም:: ከዚህ አሁን ከያዝነው ክፍል እንደምንመለከተው ገንዘብን በተመለከተ በግልጽ ነበር የተናገረው፤ ምክንያቱም የገንዘብ አያያዛችን የመንፈሳዊ ሕይወታችን ነጸብራቅ በመሆኑ ነው::

*ምድራዊና ሰማያዊ ሀብት*

ማቴ 6÷19-21

[19]«ብል ሲበላው፣ ዝገት ሲያበላሸው፣ ሌባም
ቁፍሮ ሲሰርቀው በሚችልበት በዚህ ምድር ላይ ለራሳችሁ
ሀብት አታከማቹ :: [20]ነገር ግን ብል ሲበላው ሌባ ቁፍሮ[85] ሲሰርቀው በማይችልበት
በዚያ በሰማይ ለራሳችሁ ሀብት አከማቹ፤ [21]ሀብትህ ባለበት ልብህም በዚያው
ይሆናልና::»

«ገንዘብህን ይዘኸው መሄድ አትችልም» መባሉ ትክክል ነው:: ኢየሱስ ግን ቀድሞህ እንዲሄድ ማድረግ ትችላል እያለ ነው:: እንዴት? ገንዘባችንን ድኾችን ለመርዳት በማዋል (ጢሞ 6÷17-19):: ስለ ንፉግ ባለ ሀብት የተነገረው ምሳሌ መልእክትም ይኸው ይመስላል:: ከሉቃስ 16÷9 እንደምንመለከተው ኢየሱስ፣ «ስለዚህ እላችኋለሁ የዚህ ዓለም ገንዘብ ባለቀ ጊዜ በዘላለም ቤት ተቀባይነት እንዲኖራችሁ በዚሁ ገንዘብ

---

[85] በቁሙ «ቈፍሮ» የሚያመለክተው ከጭቃ ጡብ የተሠራ ቤትን ነው::

ወዳጆችን ለራሳችሁ አፍሩበት ብሏል (ማቴ 25÷31-46 ጋር ያነ)፡፡ በመጀመሪያው መቶኛ ዓመት ገንዘብ ልብሶች መሐል ወይም ሌሎች የከበሩ ዕቃዎች ውስጥ እንጂ እንደዚህ ዘመን ባንክ ውስጥ አይቀመጥም ነበር፡፡ ስለሆነም ብልና ዝገት በቀላሉ ያጠቁት ነበር፡፡ ብል ወይም ዝገት ባያጠቃው እንኳ በቀላሉ ሊሰረቅ ይችል ነበር፡፡ ብል ሊበላው ሌባም ሊሰርቀው የሚችለውን ሀብታችንን ስንሞት ትተነው እንሄዳለን (ሉቃ 12÷15-21)፡፡ ስለሆነም ምድራዊ ሀብት ጊዜያዊ ነው፡፡

ቁጥር 21 ለመጠቀስ የሚበቃ ነው፡፡ ሀብትና ጊዜን ትኩረታችንን በማሳጣት ከመንፈሳዊ ጉዳይ ያዘናጋናል፡፡ ለምሳሌ ያህል ሞተር ብስክሌት ብንገዛ መቆለፍ ይኖርብናል፡፡ ጎማው ሲተነፍስ ማስነፋት አለብን፡፡ ሌባ እንዳይሰርቀው ጥሩ ቦታ ማስቀመጥ አለብን፡፡ በየጊዜው ዘይት ማስደረግ አለብን፣ ወዘተ፡፡ ልንነዳው ወይም ለሌሎች ማሳየት ካልቻልን ጥቅሙ ምንድን ነው? የዚህ ዓለም ሀብት ይኸው ነው፡፡ ክርስቲያንም፣ ሀብታምም መሆን አስቸጋሪ ሊሆን ቢችልም፣ የማይቻል ግን አይደለም (ማቴ 19÷23-26)፡፡ በሀብት፣ «የተባረኩ» ሰዎች ገንዘባቸው ሲያዘናጋቸው ወይም ሲወርሳቸው ይታያል፡፡ የደቀ መዝሙርነት ሕይወት ተቃራኒ ነው ማለት ባይቻል እንኳ፣ ብዙ ጊዜ ግን ኢየሱስን እንዳንከተል እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡ ሀብት ማነቆ ከሆነብን በቀላሉ መላቀቅ አይቻልም፤ ይሁን እንጂ ዘለቄታ ያለው ነገር ላይ ማዋል ከተፈለገ ግን የግድ ልንላቀቀው ይገባል (ማቴ 19÷21)፡፡

ሀብት አደጋ ሊሆን የሚችልበት ሌላው መንገድ ደግሞ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋትና ድኾችን ለመርዳት ከምናውለው ይልቅ የበለጠ ገንዘብ እንድንሰበስብ ወደ ማዘንበል ማነሣሣቱ ነው፡፡ ገንዘባችንን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት እንድንሰጥ ስንጠየቅ፣ «ለክፉ ቀን» ካስቀመጥነው አንሥተን መስጠት ያሳሳናል፡፡



ትልቁ ችግራችን የራሳችንን ፍሎጎት በጣም አክብደን ማየትና ለድኾች ግን ዝቅተኛ ግምት መስጠታችን ነው፡፡[86]

*ብርሃንና ጨለማ*

**ማቴ 6÷22-23**

[22]«ዐይን የሰውነት መብራት ነው፤ ስለዚህ ዐይንህ
ጤናማ ከሆነ መላው ሰውነትህ በብርሃን የተሞላ ይሆናል፡፡
[23]ዐይንህ ታማሚ ከሆነ ግን መላው ሰውነትህ በጨለማ
የተሞላ ይሆናል፡፡ እንግዲህ በአንተ ውስጥ ያለው ብርሃን
ጨለማ ከሆነ፣ ጨለማው እንዴት ድቅድቅ ይሆን?»

ዲ.ሲ. ኤሊሰን፣ ዐይን ብርሃን ወደ ሰውነት የሚገባበት ሳይሆን፣ ብርሃን ከሰውነት የሚወጣበት መሆኑን አመልክቷል፡፡[87] አንዳንድ የጥንት ሰዎች የእንስሳት «ዐይን ነጸብራቅ» እና የሰዎች ዕይታ ብርሃንን ከሰውነት እንደሚረጭ ያስቡ እንደ ነበር ይናገራል፡፡ ስለዚህም በብርሃን የተሞላ አካል በልግስና [*haplous*] ብርሃን ይረጫል፡፡ በጨለማ የተሞላ ሰውነት ግን ለሌሎች የሚፈነጥቀው ብርሃን አይኖረውም፡፡ ከዚህም የተነሣ ያ ሰው ንፉግ ይሆናል፡፡ ይህን ገለጻ በሁለት ምክንያቶች እንቀበለዋለን፡፡ አንደኛው፣ ከዐውዱ ጋር በሚገባ የሚጣጣም በመሆኑ ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ ልግስና "*haplous*" የሚለውን ቃል «ለጋስ» በማለት መረዳቱ ጠንካራ ድጋፍ ያለው በመሆኑ ነው፡፡[88] ያም ሆኖ ግን ዐይን ብርሃንን የሚቀበል ሳይሆን ብርሃንን የሚፈነጥቅ ነው ማለት በመጠኑ ግር የሚል ነው፡፡ በተጨማሪም ኢየሱስ ብርሃን በዐይን በኩል ወደ ሰውነት ይገባል አለ እንጂ በዐይን በኩል ከሰውነት ይወጣል አላለም፡፡

---

[86] C.L. Blomberg, "On Wealth and Worry: Matthew 6:19-34- Meaning and Significance," *CTR* 6/1 (1992): 73-89 በግለሰብም ሆነ በማኅበረሰብ ደረጃ ክርስቲያኖች ገዘባቸውን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ጠቃሚ ምክሮች አቅርቧል፡፡

[87] D.C. Allison, "The Eye is the Lamp of the Body," *NTS* 33 (1987): 61-83.

[88] H.J. Cadbury, "The Single Eye" *HTR* (1954): 69-74.

ምናልባትም የተሻለ ገለጻ የሚሆነው ይህ ነው፤ ዐይን የብርሃን ክፍል ነው፤ ይህም ማለት ብርሃን ወደ ሰውነት ያስገባል ማለት ነው። እንዲህ ከሆነ በምሳሌያዊ መልኩ ዐይን ክፉና ደጉን የምንለይበት የአካል ብልት ነው ማለት ይቻላል። «መልካም» የሚለው ቃል [*haplous*]፣ «ያልተከፋፈለ አስተሳሰብ፣ የማያወላውል ታማኝነት» ቢባል ይበልጥ ትክክል ይሆናል።[89] ከዐውደ ምንባቡ አንጻር ኢየሱስ ማለት የፈለገው፣ «በምድራዊና በመንፈሳዊ ሀብት መካከል ያለውን ልዩነት ማስተዋል ከቻላችሁ ያለ ጥርጥር ሁለንተናችሁ ብሩህ ይሆናል። ታማኝነታችሁ በእግዚአብሔርና በገንዘብ መካከል የሚዋልል ከሆነ ግን፣ ሕይወታችሁ ጨለማ ይሆናል» የሚለውን ነው።

*እግዚአብሔርና ገንዘብ*

[24]«አንድ ሰው ሁለት ጌቶችን ማገልገል አይችልም፤ አንዱን ጠልቶ ሌላውን ይወዳል፤ ወይም አንዱን አክብሮ ሌላውን ይንቃል። እግዚአብሔርንና ገንዘብን በአንድነት ማገልገል አይቻልም።» **ማቴ 6÷24**

ሦስት ነገሮችን ብናገናዝብ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ምን ማለቱ እንደ ነበር በሚገባ ግልጽ ይሆንልናል። (1) እዚህ ላይ ጌታ የተባለው ባሪያ አሳዳሪ እንጂ አለቃ አይደለም። ተጨማሪ ሥራን የሚመለከት ምንም የተባለ ነገር የለም። (2) መጥላትና መውደድ ሲባል ቃል በቃል ሳይሆን በአንጻራዊ መልኩ ነው (ከሉቃ 14÷26 ጋር ያነ)። በዘመናችን አነጋገር፣ «ከሁለት አንዱ ቅድሚያ ማግኘት አለበት» እንደ ማለት ነው። (3) የንጉሥ ጀምስ ትርጉም (KJV) «ማሞን» [*Mammon*] የሚል የአራማይክ ቃል ተጠቅሟል፤ ይህም የአንድን ሰው ሀብት በሙሉ

[89] T. Thiennaman, "A Comment on an Interpretation by Prof. Cadbury," *GR* 1 (1955):9-22.



የሚያካትት ነው። ብዙዎች የሁለቱም ዓለሞች ተጠቃሚዎች፣ ያም ሀብታም መሆንና እግዚአብሔርንም ማምለክ እንደሚቻል ያምናሉ። ኢየሱስ ግን እንደማይቻል ነው የሚናገረው። ከሁለት አንዱ ጊዜያችንንና ትኩረታችንን ይቆጣጠራል። የኋላ ኋላ ደግሞ ሁለቱም «ጌቶች» በአንድ ጊዜ ትኩረታችንን እነርሱ ላይ ብቻ እንድናደርግ ይጠይቁናል። በዚያ ጊዜ የቱን አብልጠን እንደምንወድ ግልጽ ይሆናል።

**መጨነቅ፣ 6÷25-34**

«መጨነቅ»፣ የሚለውን «ስለዚህ» በሚለው ቃል አንጻር ቀደም ሲል ከተመለከትነው ከገንዘብ ጉዳይ ጋር እንደተያያዘ ከገባን የክፍሉ ዋነኛ ሐሳብ እንደሆነ እንገነዘባለን (ቁ 25፣27፣28፣31፣34)። ከአድማጮቹ አንዳንዶቹ፣ «ለገንዘብ ቅድሚያ ካልሰጠን፣ እንዴት የሚያስፈልገንን ማሟላት እንችላለን?» በማለት ሳያስቡ አልቀሩም። ኢየሱስ፣ «በእግዚአብሔር ታመኑ» በሚል አጭር ቃል ጭንቀታቸውን እንዲተዉ ይመክራል። ኢየሱስ እንደ ገና ዕይታችንን ከምድራዊው ወደ ሰማያዊው እንድናቀና ያሳስበናል።

ኢየሱስ ሰዎች ይበልጥ የሚጨነቁላቸውን ሁለት ነገሮች፣ እነዚያም ምግብን (ቁ 26-27) እና ልብስን (ቁ 28-30) ለእነዚህ ነገሮች መጨነቅ እንደማይገባ ሦስት ምክንያቶችን አቅርቧል፤ (1) በሕይወት ከምግብና ከልብስ የሚበልጡ ነገሮች አሉ (ቁ 25)። ጊዜያችንና ዐቅማችንን በመጨነቅ ከማሳለፍ ይልቅ እነዚህ ነገሮች ላይ ማሳለፍ ይሻላል። (2) እግዚአብሔር ይወደናል፤ የሚያስፈልገንንም ሊሰጠን ይፈልጋል (ቁ. 26፣30፣32)። ሐሳቡን በምክንያት ለማስደገፍ ኢየሱስ በአይሁድ ዘንድ የተለመደውንና ከትንሽ ተነስቶ ታላቁን የሚመለከተውን አመክንዮ ተጠቅሞ ወፎችና የሜዳ ሣርን አቅርቧል። እግዚአብሔር ለወፎችና ለሜዳ ሣሮች እንኳ የሚያስፈልጋቸውን የሚሰጥ ከሆነ ከእነርሱ ለሚበልጡ የሰው ልጆችም ይሰጣቸዋል ማለት ነው። (3)

ጭንቀት ምንም የሚያመጣው ለውጥ የለም (ቁ 27፣34):: ጅዋጅዌ የመጫወት ያህል ነው፤ ይነቀንቃችኋል፤ ግን የትም አያደርሳችሁም::

ማቴ 6÷25-27

[25]«ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ስለ ኑሮአችሁ ምን
እንበላለን? ምን እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? በማለት
አትጨነቁ:: ሕይወት ከምግብ፣ ሰውነትስ ከልብስ
አይበልጥምን? [26]እስቲ የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ፤ አይዘሩም፤ አያጭዱም፤ በጐተራም
አያከማቹም ይሁን እንጂ የሰማዩ፣ አባታችሁ ይመግባቸዋል:: እናንተ ከእነርሱ እጅግ
አትበልጡምን? [27]ስመሆኑ ከእናንተ መካከል ተጨንቆ በዕድሜው ላይ አንዲት ሰዓት
መጨመር የሚችል አለን?

«የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ» (ቁ 26) የሚለው አንድምታ፣ «ተመልክታችሁ ተማሩ» የሚል ነው:: «ተመልከቱ» [*katamathete*] (ቁ 28)፣ ከዚህም ላቅ ያለ ትርጉም አለው፤ «በጥንቃቄ ተማሩ» እንደ ማለት ነው:: ከእነዚህ ትንንህ ፍጥረታት ብዙ የምንማረው ይኖራል:: ብዙ ይሠራሉ፤ ግን አይጨነቁም:: ጐተራ ባይኖራቸውም ለየቀኑ የሚያስፈልጋቸውን ያገኛሉ:: ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር ለእነርሱ ለጋስ መሆኑን ነው:: ለእኛ ደግሞ ልግስናው የበለጠ ነው:: አካባቢያችንን የመቆጣጠር ችሎታ አለን:: እህል ማምረት፣ እንስሳት ማርባት፣ እህል በጐተራ ማኖር እንችላለን:: ከወፎች የበለጠ ለራሳችን ምግብ ማዘጋጀት መቻላችን ብቻም ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ዐይኖች ፊት ክቡር ዋጋ ያለን ነን (ማቴ 10÷29-31):: እንዲህ ከሆነ ደግሞ ጨርሶ መጨነቅ የለብንም ማለት ነው::

«አንዲት ሰዓት» የሚለው በተለያዩ ትርጉሞች፣ «በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ»፣ «በቁመቱ ላይ አንዲት ስንዝር»፣ «በዕድሜው ላይ አንዲት ሰዓት» ተብሏል:: ችግሩ ግን የሚከተለው ነው፤ «የሕይወት ዘመን» ተብሎ የተተረጐመው «ሄሊኪያን» [*helikian*] የተሰኘው የግሪክ



ቃል፣ አካልን ወይም ዘመንን በሚያመለክት መልኩ፣ «የሕይወት ርዝመት» ወይም፣ «ቁመት» (ለምሳሌ ርዝመት/ስፋት) ማለት ሊሆን ይችላል:: ክንድ ዐሥራ ስምንት ጫማዎች ያህል ርዝመት ያለው የአካል መለኪያ ነው::

ማቴ 6÷28-30

[28]«ደግሞስ ስለ ልብስ ስለምን ትጨነቃላችሁ?
እስቲ የሜዳ አበቦችን ተመልከቱ፤ አይለፉም፣ ወይም
አይፈትሉም:: [29]ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ያን ያህል ክብር
የነበረው ንጉሥ ሰሎሞን እንኳ ከእነዚህ አበቦች እንደ አንዲቱ አልለበሰም:: [30]እናንተ
እምነት የጐደላችሁ! እግዚአብሔር ዛሬ ታይቶ በነጋታው እሳት ውስጥ የሚጣለውን
የሜዳ ሣር ይህን ያህል ካለበሰ እናንተንማ እንዴት አብልጦ አያለብሳችሁ::»

«የሜዳ አበቦች» የሚለው የትኛውንም የአበባ ዘር ሊወክል ይችላል:: «የሰማይ ወፎች» ከሚለው ጋር ትስስር የሚፈጥርም ነው:: በመስክ ላይ ፈክተው የሚታዩ የሜዳ አበቦች ዐይንን መማረካቸው እርግጥ ነው:: እነዚህ ውብት የተላበሱ ፍጥረታት አይደክሙም አይፈትሉም (ይህም የወንድና የሴትን የሥራ ድርሻ ሳያመለክት አይቀርም):: ይሁን እንጂ ከእነርሱ ጋር ሲነጻጸር ሰሎሞን እንኳ ያን ያህል ያማረ ልብስ አልለበሰም::

እንግዲህ እግዚአብሔር ነገ ወደ እሳት ለሚጣለው ነገር (ቁ 30) እንኳ ይህን ያህል ቸር ከሆነ፣ ለእኛስ ከዚያ ያነሰ ቸር ይሆናል ማለት እንችላለን? «እናንተ እምነት የጐደላችሁ» በማለት ኢየሱስ ቢገሥጸን ሊያስገርመን አይችልም:: በመኝታ ቤት መስኮታችን በኩል ወደ ውጭ መመልከት ብቻ የመጨነቅን ከንቱነት ሊያሳየን ይችላል ሞውንስ የተባለ ሰው እንደተናገረው፣ «መጨነቅ እግዚአብሔርን የሚዳፈር ክህደት ነው::»[90]

[90] R.H. Mounce, *Matthew* (Peabody, MA: Hendrickson, 1991): p.80.

31ስለዚህ ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን?
ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤ 31አሕዛብ
እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለማግኘት ይጨነቃሉና፤ የሰማዩ
አባታችሁም እነዚህ ሁሉ ለእናንተ እንደሚያስፈልጓችሁ ያውቃል። 33ከሁሉ አስቀድማችሁ
ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል።
34ስለዚህ ስለነገ በማሰብ አትጨነቁ፤ የነገ ጭንቀት ለነገ ይደር፤ እያንዳንዱ ዕለት የራሱ
የሆነ በቂ ችግር አለውና።

ማቴ 6÷31-34

በመጀመሪያ፣ የተጠራነው በሀብት ሳይሆን በእግዚአብሔር እንድንታመን ነው። አረማውያን ቅድሚያ የሚሰጡትን ነገር የምናሳድድ ከሆነ ጨውና ብርሃን የምንሆነው እንዴት ነው? ክርስትና ማኅበረሰቡ ላይ ለውጥ ማምጣት የሚችለው ከዓለማውያን የተለየ ሆኖ በሚገኝበት መጠን ነው። በአራተኛው መቶ ዓመት የሮም ንጉሠ ነገሥት የነበረው አረማዊው ዩሊያን ክርስቲያኖችን በተመለከተ እንዲህ ብሎ ነበር፤ «ማፈር አለብን፤ በአይሁዳውያን መካከል አንድ ለማኝ እንኳ አይገኝም፤ እነዚያ አምላክ የለሽ ገሊላውያንም ቢሆኑ የራሳቸውን ወገን ብቻ ሳይሆን፣ የእኛንም እየመገቡ ነው። የራሳችን ወገኖች ግን ከእኛ ምንም የሚያገኙት የለም»።

ሁለተኛ፣ የእርሱን መንግሥትና ጽድቅ አዘወትረው ለሚፈልጉ እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንደሚሰጥ ቃል ገብቷል (ቁ 33)። እግዚአብሔር ልግስና ስለተደረገላቸው ወገኖች እጅግ ብዙ ምስክርነቶችን ማቅረብ ይችላል። ይሁን እንጂ «ክርስቲያኖች የሚራቡት ለምንድን ነው?» ለሚለው ከባድ ጥያቄ መልስ መስጠት ይኖርብናል። እምነት ስለሌላቸው ነው የሚል መልስ አንቀበልም። ቁ 33 ላይ ያለው በተሟላ መልኩ የሚፈጸመው ወደፊት መሆኑን ብንቀበልም፣ አሁን ላለው ሕይወታችን ተግባራዊ መሆን እንደሚችል የማንቀበል ከሆነ ግን አሁን ላለው ችግር መጨነቅ እንደማይገባ የቀረበው ትምህርት ጨርሶ የማይጠቅም መሆኑ ነው።

ይህን ጥቅስ በሚገባ ለመረዳት አንዳንድ ነጥቦችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል። (1) እንደማንኛውም ሰው ሁሉ ክርስቲያኖችም የተለያየ መከራ ይደርስባቸዋል፤ አንዳንዱ ለተግሣጽ ሊሆን ይችላል (ዕብ 12÷7)፣ አንዳንዱ ለክርስቶስ ለመመስከር ሊሆን ይችላል (ማቴ 5÷10-12፤ ሮሜ 8 ÷17፤ ፊል 3÷10፤ 4÷12፤)፣ አንዳንዱ ደግሞ የምንኖረው በኀጢአት በወደቀ ዓለም ውስጥ በመሆኑ ብቻ ሊሆን ይችላል። በዚህ ዓለም ሁሉንም መመገብ የምንችልበት በቂ ምግብ አለ። ችግሩ የእግዚአብሔር ልግስና ላይ ሳይሆን፣ ሰዎች ያላቸውን ለማካፈል ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ነው። (2) ክርስቲያኖች ድኾችን የመርዳት ኀላፊነት አለባቸው (ምሳሌ 22÷9፤ 25÷21፤ ኢሳ 32÷6፤ 58÷6፤ ሕዝ 16÷49፤ 18÷7፤ ማቴ 25÷42፤ ማር 10÷21፤ ሉቃ 3÷11፤ 12÷33፣48፤ ሐሥ 4÷32)። በመንፈስ በሚመሩ ሰዎች በኩል እግዚአብሔር መልካም ነገርን ያደርጋል። የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን የመፈለግ ዋናው ክፍል ይኸው ነው። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓለም እንደ እግዚአብሔር እጅ በመሆን ትሠራለች። ስለሆነም በዓለማችን ያለው አብዛኛው ረሃብ የቤተ ክርስቲያን ራስ ወዳድ የመሆን ነጸብራቅ እንጂ የእግዚአብሔር ቸልተኝነት አይደለም ማለት ነው። (3) ቁጥር 34፣ ቁጥር 33 ላይ ያለውን የሚያጠናክር ይመስላል። በመሠረቱ ኢየሱስ የዕድሜ ዘመናችን በመከራ የተሞላ መሆኑን ይገነዘባል። ይሁን እንጂ ወደ ፊት ሊገጥመን የሚችለውን በማሰብ መጨነቅ ምንም እንደማይጠቅመን ያውቃል። እያንዳንዱ ቀን ትኩረታችንን የሚስብ የራሱ የተለያዩ ነገሮች አሉት።

**መፍረድ 7÷1-6 (ሉቃ 6÷37-42 ጋር ያነ)**

ማቴ 7÷1

1እንዳይፈረድባችሁ በማንም ሰው ላይ አትፍረዱ፤

ሉቃ 6÷37-38

37አትፍረዱ፤ አይፈርድባችሁም፤ አትኰንኑ፤ አትኰነኑም።
ይቀር በሉ ይቀር ትባላላችሁ። 38ስጡ፤ ይሰጣችኋል፤
በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ስለሚሰፍርላችሁ ጫን
በተደረገ፣ በተነቀነቀና በተትረፈረፈ መልካም መስፈሪያ
ተሰፍሮ በዕቅፋችሁ ይሰጣችኋል።

ማቴ 7÷2

2በምትፈርዱበትም ዐይነት ይፈርድባችኋል፤
በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል።

«መፍረድ» [*krino*] የሚለው ቃል፣ «መመርመር» ወይም፣ «መገምገም» ወይም ደግሞ፤ «መኰነን» ማለት እንኳ ሊሆን ይችላል። ክርስቲያኖች ሰዎችን በጠባያቸው መሠረት መመርመርና መገምገም ይኖርባቸዋል (ማቴ 7÷5-6፣16፤ 1ቆሮ 5÷5፤ 1ዮሐ 4÷1)። ያም ሆኖ ግን በማንም ላይ የመፍረድ መብት የለንም። ይህ የእግዚአብሔር ብቻ ሥልጣን ነው (ሮሜ 14÷4፣10፤ 1ቆሮ 4÷4-5)። የዚህ ዐይነት ፍርድ ሰዎችን መኰነን እንጂ መገምገም እንዳልሆነ ሉቃስ (6÷37) በግልጽ ያመለክታል። በቀላል አነጋገር አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት የመፍረድ ችሎታውም ሆነ ሥልጣኑ የለንም። ክርስቲያን ያልሆነው ዓለም ይህን ክፍል ጠንቅቆ ያውቀዋል። ይህንኑ ክፍል ነጩን ነጭ፣ ጥቁሩን ጥቁር በማለት ግልጹን የሚናገሩ ክርስቲያኖችን ለማደናገጥ ይጠቀሙበታል (ቁ 6)። ኢየሱስ ግን እንዲህ ያለ ከዐውደ ምንባቡ ተነጥሎ የተወሰደ አስተሳሰብ አይቀበልም።[91] በዚህ ዓለም ስንኖር

---

[91] J.D.M. Derrett, "Christ and Reproof (ማቴ 7÷1-5፤ ሉቃ 6÷37-42)" *NTS* 34 (1988): 271-281 እንደሚሉት በአይሁድ አስተሳሰብ ባሕል መሠረት ኢየሱስ



ክርስቲያን ግብረገባዊ ድምፅ መሆኑ ወደኋላ መባል የለበትም (5÷13-16 ጋር ያነ)።

በሌሎች የምንፈርድ ከሆነ እግዚአብሔርም በእኛ ላይ ይፈርድብናል። ከዚህም ሌላ ሉቃስ የዚህ ተቃራኒ፣ እውነት መሆኑን ይናገራል። ሌሎችን ይቅር የምንል ከሆነ የሞላና የተትረፈረፈ የእግዚአብሔር ጸጋ ይበዛልናል (ሉቃ 6÷37-38)።

ማቴ 7÷3-5

3«በዐይን ውስጥ ያለውን ግንድ ሳትመለከት፣
በወንድምህ ዐይን ያለውን ጉድፍ ለምን ታያለህ?
4በዐይንህ ውስጥ ግንድ እያለ ወንድምህን፣ «ዐይንህ
ውስጥ ያለውን ጉድፍ ላውጣልህ ማለት እንዴት ትችላለህ? 5አንተ ግብዝ፤ አስቀድመህ
በዐይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ አውጣ፤ ከዚያም በወንድምህ ዐይን ውስጥ ያለውን
ጉድፍ ለማውጣት አጥርተህ ታያለህ።»

እዚህ ላይ ኢየሱስ ያቀረበው ሐሳብ በመጠኑም ቢሆን ፈገግ ሊያሰኝ የሚችል ነው። የብዙዎቻችን ችግር በመሆኑ ግን እውነቱ ለሁላችንም ግልፅ ነው። ከራሳችን ይልቅ የሌሎችን ስሕተት ለማየት ፈጣኖች ነን። ከራሳችን ይልቅ ሌሎች ላይ የምናየው ስሕተት ያናድደናል (2ሳሙ 12 ጋር ያነ)። ለምሳሌ ያህል ራሱ ቁጡ የሆነ ሰው፣ ሌላው ሰው ቢቈጣ የተሳደበ ያህል ይሰማዋል። ይህን በተመለተ ስቶት ሲናገሩ፣ «ስለ ራሳችን ጥሩ አመለካከት ያለንን ያህል ለሌሎች የተጣመመ አመለካከት አለን። እንደ እውነቱ ከሆነ ሌሎች ላይ የምንመለከተው የእኛን የራሳችንን ነጸብራቅ ነው፤ ጥፋቱ የራሳችንም ቢሆን ሌሎች ላይ እንፈርዳለን፤ ከዚህም የተነሳ ራስን የማጽደቅ እርካታ እንዲኖረን ለማድረግ እንሞክራለን» (ገጽ 178)። ጳውሎስም በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ ኢየሱስ ከተናገረው ጋር የሚስማማ ነገር ተናግሯል፤

---

ሰዎችን ለእርምት መገሠጽን መቃወሙ እንዳልነበር ሰሚዎቹ በቀላሉ ይረዳሉ።

ስለዚህ አንተ በሌላው ላይ የምትፈርድ፣ የምታመካኝበት የለህም፤ በሌላው ላይ በምትፈርድበት ነገር ሁሉ፣ ራስህን ትኰንናለህ፤ ፈራጅ የሆንኸው አንተ ያንኑ ታደርጋለህና ... እንግዲህ አንተ ሰው በሌሎች ላይ እየፈረድህ፣ ያንኑ የምታደርግ ከሆነ ከእግዚአብሔር ፍርድ የምታመልጥ ይመስልሃል? (ሮሜ 2÷1፣3)::

እንዲህ ስለተባለ ግን ጥፋትን እየፈጸሙ ያሉ ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን ከመገሠጽ ኀላፊነት ነጻ አያደርገንም (ገላ 6÷1):: ይሁን እንጂ ስንገሥጽ አንዳንድ ማገናዘብ ያለብን ነጥቦች ይኖራሉ:: በመጀመሪያ ደረጃ፣ ሌላው አማኝ ላይ ትክክል እንዳልሆነ ከምንመለከተው ነገር አኳያ እኛ እራሳችን ግብረ ገባዊ ንጽሕና ሊኖረን ይገባል:: እንዲህ ሲባል ግን፣ «ይህን በተመለከተ እኔ ከአንተ የተሻልኩ ነኝ» እንድንል ሳይሆን፣ «እኔም እንዳንተ ይህ ዐይነት ችግር ነበረብኝ፤ ግን አሁን ችግሩ የሚፈታበትን መንገድ ልነግርህ እፈልጋለሁ» ለማለት እንዲያስችለን ነው:: ሁለተኛ፣ ወደ ንስሐ የሚመራ፣ የእግዚአብሔርን፣ «ቸርነት፣ ቻይነትንና ትዕግስትን» (ሮሜ 2÷4) በተመለከተ ጥብቅ አድናቆት ሊኖረን ይገባል:: ሦስተኛ፣ በ«ወርቃማው ሕግ» (ቁ 12) ያለው፣ «የእጅን የማግኘት ሕግ»፣ ወደ ጌታ ጸሎት (ማቴ 6÷12፣14-15) እንዲሁም ስለ ብጽዕና ወደ ተነገረው ክፍል (ማቴ 5÷7) ሊመራን ይገባል:: አራተኛ፣ ያልሆነውን መስለን ለመታየት መሞከር የለብንም:: እዚህም ላይ ቢሆን ስለ ግብዝነት የተባለው አብይ ሐሳብ ሊነሳ ይችላል (ማቴ 6÷2፣5፣16):: ኢየሱስ የሰዎችን ስሕተት እንድናሳይ የሚፈልገው (ቁ 5) የራሳችንንም ደካማነት በመረዳትና በትሕትና ነው:: ዓላማው ዕርቅ እንጂ በሃይማኖተኝነት ሽፋን ራስን ማግነን አይደለም::



ሮሜ 7÷6

[6]«በእግራቸው እንዳይረግጡት፣ ተመልሰውም ነክሰው እንዳይበጫጭቋችሁ፣ የተቀደሰ ነገር ለውሾች አትስጡ፤ ዕንቁቻችሁንም በእሪያ ፊት አትጣሉ::»

ውሾችና እሪያዎች በአይሁድ ዘንድ እንደ ርኩስ የሚቆጠሩ እንስሳት ነበሩ:: በተለምዶአዊ አነጋገር ውሾች ሲበጫጭቁ፣ እሪያዎች ግን መሬት ላይ እንደሚረጋግጡ ነበር የሚታሰበው:: በመሠረቱ ለመሥዋዕት የቀረበው ሥጋ ለውሾች አይሰጥም፤ ዕንቁም በእርያዎች ፊት አይጣልም:: ክፍሉ ስለ ማን ወይም ምን እየተናገረ እንደሆነ በቀላሉ ማወቅ ቢቻልም የመልእክቱን ጭብጥ መተርጐም ግን አዳጋች ነው::

ኢየሱስ ይህን የተናገረው በሌሎች ላይ መፍረድን አስመልክቶ ያቀረበውን ትምህርት ሚዛን ለማስያዝ ነበር:: ሰዎችን በውሾች ወይም በእርያዎች ምድብ ከማስቀመጣችን በፊት አስቀድሞ እነርሱን የምንገመግምበት መለኪያ ሊኖር እንደሚገባ ግልጽ ነው:: ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው? አንዳንዴ አይሁድ ስለ አሕዛብ ሲናገሩ በውሾችና በእርያዎች ይመስሏቸው ነበር (ማቴ 15÷26፣27):: በእግዚአብሔር መንግሥት ግን ይህ ልዩነት ተሽሯል (ገላ 3÷28):: ስለሆነም፣ አሕዛብም ይሁኑ አይሁድ (ፊልጵ 3÷2) ውሾችና እሪያዎች ተብለው የተጠሩት እውነትን የሚንቁ (2ጴጥ 2÷22)፣ እና በግብረ ገባዊ ሕይወታቸው የዘቀጡ ሁሉ ናቸው (ራእ 22÷15)፣ የሚል መደምደሚያ ላይ ብንደርስ ትክክል ይሆናል::

ለእነዚህ ሰዎች መስጠት የሌለብን የተቀደሰ ነገርና ዕንቁዎችስ ምንድናቸው? ጥንታዊት ቤተክርስቲያን ይህ ስለ ጌታ ራት የሚናገር መሆኑን ነበር የምትረዳው:: ለምሳሌ ያህል በዲዳኬ [*Didache* 9:5]፣ «በጌታ ስም የተጠመቀ ካልሆነ በቀር ማንም ከቅዱስ ቁርባናችሁ አይብላ፤ ምክንያቱም ይህን በተመለከተ ጌታ ራሱ፣ 'የተቀደሰ ነገር

ለውሾች አትስጡ' ብሏል» ይላል። ይሁን እንጂ ይህ የተነገረው ቅዱስ ቁርባን ከመሰጠቱ በፊት እንደ ነበር ግልጽ ነው። የተሻለ የሚሆነው ግን ዋጋው እጅግ ውድ ስለሆነው እንቁ ከተነገረው ምሳሌ (ማቴ 13÷16) እና እነዚህ «የከበሩ ነገሮች» የእግዚአብሔር መንግሥት መሆናቸውን ከሚያመለክተው 2ጴጥሮስ 2÷22 ሐሳብ አንጻር ብንረዳው ነው። ስለሆነም ትክክለኛው ትርጉም፣ «አንድ ሰው እውነትን መቀበል ካልፈለገ ለእርሱ መስበክ ወይም መመስከር ይብቃችሁ» የሚል ሐሳብ ይይዛል። ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት በላከ ጊዜ ያደረገው ይህንኑ ነበር (ማቴ 10÷14)፤ የጳውሎስ አሠራር መንገድም ይኸው ነበር (ሐሥ 13÷44-51፤ 18÷5-6፤ 28÷17-28 ጋር ያነ)።[92]

**§ 54**
**ማጠቃለያ**
**(ማቴ 7÷7-27፤ ሉቃ 6÷31, 43-49 ጋር ያነ)**

የተራራው ስብከት የመጨረሻ ክፍል፣ «ክርስቲያናዊ ግንኙነት» በሚል የወል ዐበይት ርዕስ ሥር ፈታ ብለው የተሳሰሩ የተለያዩ ክፍሎች አሉት። ይህም አንዳንዶችን አሁን በምናውቀው መልኩ ስብከቱ ከተለያየ ጊዜ፣ ስፍራ ወይም ምንጭ የተወሰዱ ጠቃሚ የአነጋገር ስብስብ ናቸው ብለው እንዲያስቡ ምክንያት ሆኗል። በመሠረቱ ግን እንዲህ መታሰብ የለበትም። ስብከቱ እጥር ምጥን ያለ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ይህንኑ ለመጠበቅ ሲባል አንዳንድ አያያዦችን ወይም መሸጋገሪያ ሐሳቦችን ማስቀረት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቶአል ማለት ይቻላል። ከዚህም

[92] T.J. Bennett, "Mt 7:6 – A New Interpretation," *WTJ* 49 (1987): 371-386 ላይ እንደሚለው ኢየሱስ፣ «ቅዱስ ነው ብላችሁ የምታስቡትን፣ ውሾች ናቸው ለምትሉዋቸው አትስጡ» በማለት ስላቅ እየተጠቀመ ነበር። በሌላ አነጋገር «በፍጹም በሌሎች ላይ አትፍረዱ!» ማለቱ ነበር። ስለሆነም ይህ ኢየሱስ ሰዎችን ውሾች አለማለቱንና በቁጥር 1 እና 6 መካከለም ምንም ተቃርኖ አለመኖሩን ያሳያል ማለት ነው። ከውሾችና አሳማዎች ሊመጣ የሚችልን በቀል እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ያሳያል። ይሁን እንጂ እንዲህ ለማለት በጽሑፍ ካለው የተለየ ሐሳብ መጨመር ሊኖርብን ነው።



በተረፈ፣ ለሐሳቦቹ የተሰጡ ድምዳሜዎች እርስ በርስ ብዙም ወዳልተሳሰሩ አንድምታዎች ስለሚያመሩ ዳግም ስብከቱን ማየት ግድ ይሆናል።

**ማቴ 7÷7-11**

7«ለምኑ፣ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ፣ ታገኛላችሁ፤
አንኳኩ በሩም ይከፈትላችኋል። 8የሚለምን ሁሉ ይሰጠዋል፤
የሚፈልግም ያገኛል፤ ለሚያንኳኳም በሩ ይከፈትለታል።
9ከእናንተ መካከል ልጁ ዳቦ ቢለምነው፣ ድንጋይ የሚሰጥ አባት አለ?
10ወይንም ዓሣ ቢለምነው እባብ የሚሰጥ ይኖራልን? ታዲያ እናንተ ክፉዎች ሳላችሁ
ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፣ የሰማዩ አባታችሁማ ለሚለምኑት
መልካም ስጦታን እንዴት አብልጦ አይሰጣቸውም?»

ከምንናገረው ይልቅ የጸሎት ሕይወታችን፣ በዚህ ዐውድ ባለው ትምህርት ለማመናችን ማስረጃ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር መልካም መሆኑን ታምናላችሁ? እንደዚያ ከሆነ ትጸልያላችሁ። ማንም ምድራዊ አባት ዳቦ የሚመስል ድንጋይ በመስጠት ልጁን የሚያታልል የለም። ዓሣ የሚመስል እባብ ወይም ሌላ ፍጡር ለልጁ የሚሰጥ አባት አይኖርም። እግዚአብሔር ሊነጻጸር የሚችለው ፍጹምነትን ከጠበቀ አባት ጋር ነው፤ ይህ ደግሞ ለአይሁዶች ጸሎት እንግዳ ሐሳብ ነበር። ኢሳይያስ 49÷15፣ «እናት የምታጠባውን ልጇን ልትረሳ ትችላለችን? ለወለደችውስ ልጅ አትራራለትምን? ምናልባት እርሷ ትረሳ ይሆናል፤ እኔ ግን አልረሳሽም» በማለት እግዚአብሔርን ልጁን ፈጽሞ ከሚወድ አባት ጋር አመሳስሎታል።

ይህ ደግሞ የተለያዩ አንድምታዎች ይኖሩታል፤ (1) እግዚአብሔር መልካም ነገርን ሊሰጠን ይፈልጋል (ሉቃ 11÷13 ላይ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተመሳስሏል)። (2) በግላችንና አዘውትረን በመጠየቅ ልንቀርበው እንችላለን («ለምኑ፣ ፈልጉ፣ አንኳኩ» በተባለው

መሠረት):: (3) የሚጐዳንን ነገር ብንጠይቅ ወይም በራስ ወዳድነት (ያዕ 4÷2-3) ወይም ያለ እምነት (ያዕ 1÷6-8) ብንለምን እግዚአብሔር ለጸሎታችን መልስ አይሰጥም:: ለጸሎታችን መልስ የሚሰጠን እንደ ፈቃዱ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው:: አንዳንዴ የእግዚአብሔር መልስ፣ «እሺ» የሚል ሊሆን ይችላል፤ አንዳንዱም፣ «አይሆንም» የሚል ሊሆን ይችላል፤ አንዳንዴ ደግሞ፣ «ቆይ፣ ጠብቅ» የሚል ሊሆን ይችላል::

ጸሎት መልስ የሚያገኝበትን መንገድ በተመለከተ ብዙ ምሥጢር የሆኑ ነገሮች አሉ:: እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው፤ ፈቃዱ መፈጸሙ የማይቀር ነው:: ከዚህም በላይ የሚያስፈልገንን ሁሉ ያውቃል:: ታዲያ፣ አዘውትረን ወይም በጽናት መጸለያችን ነገሮችን መለወጥ እንደሚችል የምናስበው ለምንድነው? በዋነኛነት ደረጃ የምንጸልየው ቅዱሳት መጻሕፍት ስላዘዙ ነው:: ለምሳሌ የሙሴ ጸሎት በእስራኤል ላይ ሊመጣ የነበረውን መቅሠፍት አስቀርቷል (ዘፀ 32÷9-14):: ይሁን እንጂ የተለወጠው የሰዎች ልብ እንጂ የእግዚአብሔር ሐሳብ እንዳልነበር ማወቅ አለብን:: ብዙ ጊዜ ጸሎት ከእግዚአብሔር ዕይታ አንጻር ነገሮችን የማየት ችሎታን በእኛ ውስጥ ይፈጥራል፤ እግዚአብሔር ላዘጋጀው በረከት ብቁ ሆነን እንድንገኝና ለፈቃዱ እንድንገዛ ያደርጋል:: የምንጸልየው እምነትን መሠረት ካደረገ መታዘዝ የተነሣ ብቻ እንጂ፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና ለጸሎት መልስ በመስጠቱ መካከል ላለው ተጻራሪ መሰል ጉዳይ መፍትሔ በማግኘታችን አይደለም::

12«ሌሎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ነገር እናንተም አድርጉላቸው፤ ሕጉም ነቢያትም በዚህ ይጠቃለላሉና:: ማቴ 7÷12



ይህ ወርቃማ ሕግ ብዙ ነገሮችን አጠቃሎ ይዟል:: የመላው ብሉይ ኪዳንን መልእክት መጠቅለል ብቻ ሳይሆን የተራራው ስብከትንም ሙሉ በሙሉ የሚወክል ነው:: «ስለዚህ» የሚለው መንደርደሪያ በቀጥታ ወደ 5÷17 የሚመልሰን ይመስላል:: ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው፣ 5÷17 እና 7÷12 ይህን ስብከት ቅንብብ ውስጥ ያሰፍራሉ:: አስቸጋሪ የሆነው ነገር ሁሉ በአንድ ግልጽ ዐረፍተ ነገር በሚገባ ይብራራል:: አዎን፣ መረዳት ጥሩ ነገር ነው፤ ተግባር ላይ ማዋሉ ግን በጣም አዳጋች ነው::[93]

አልፎ አልፎ ብርማው ሕግ በመባል የሚታወቀውን የዚህ ሕግ ተቃራኒ በአብዛኛው የምናገኘው ሃይማኖታዊ ጽሑፎች ውስጥ ነው:: ሌላው ቀርቶ ኮንፊሽየስ እንኳ፣ «በራሳችሁ ላይ እንዲደረግ የማትፈልጉትን እናንተም በሌሎች አታድርጉ» በማለት መናገሩ ይጠቀሳል:: ጦቢት 4÷15፣ «አንተ ራስህ የምትጠላውን፣ ሌሎች ላይ አታድርግ» ይላል:: የአይሁድ ሃይማኖት መቀበል የሚፈልግ አንድ ሰው ወደ አይሁዳዊው መምህር ሒላል:: መጥቶ፣ በአንድ እግሬ መቆም በምችልበት ፍጥነት ሕጉን ሁሉ ልታብራራልኝ ትችላለህ ወይ? በማለት በጠየቀው ጊዜ ሒላል፣ «አንተ የምትጠላውን ሌላው ላይ አታድርግ:: ሕጉ በሙሉ የሚለው ይህንን ነው:: የተቀረው ግን ማብራሪያ ነው» ነበር ያለው (*Shabbath* 31):: በእነዚህ አሉታዊና በኢየሱስ አዎንታዊ ሕጎች መካከል ያለው ልዩነት ወዲያውኑ ግልጽ ይሆናል:: ምንም ነገር ባናደርር እንኳ ብርማው ሕግ የሚጠይቀውን አሟልተን መገኘት

---

[93] በዚህ ዐውድ ላይ የ20ኛው ክፍለ ዘመን ሥነ ልቦናዊ አስተሳሰብ የሆነውን ለራስ ዋጋ የመስጠትን ጉዳይ ማያያዝ ከነገሮች አፈታት አኳያ በፍጹም አብሮ የማይሄድ ነው:: እርግጥ ነው ራሳቸውን የማይወዱ፣ ሌላውን የመውደድም ችግር ይኖራቸዋል:: ይሁን እንጂ ምንባቡ የሚናገረው ስለዚህ አይደለም:: ከዚህም በተጨማሪ ሌሎችን ስለማገልገል ኢየሱስ ያቀረበውን የምንከተል ከሆነ በጣም ከፍ ባለም ሆነ በጣም በተዋረደ ደረጃ ስለ ራሳችን ማሰብ አዳጋች ይሆንብናል::

እንችላለን:: ወርቃማው ሕግ ግን የተሟላ ተግባራዊነትን ይጠይቃል:: ከፍቅር መንገድ ቢያፈነግጡ እንኳ ሰዎች አንዲት ነጥብ እንኳ ሳያስቀሩ ሃይማኖት የሚጠይቃቸውን ሁሉ ሊያሟሉ ይችላሉ፤ ኢየሱስ ወደ ጽድቅ እንድንመጣ የሚያቀርበው ግልጽ ጥሪ ግን በጣም ትሑት በመሆኑ ግብዝነታችንን ያጋልጣል::

### ሁለቱ መንገዶች

ማቴ 7፥13-14

[13]በጠባቡ በር ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው
መንገድ ትልቅ፣ በሩም ሰፊ ነውና፤ ብዙዎችም በዚያ
ይገባሉ:: [14]ወደ ሕይወት የሚያደርሰው ግን መንገዱ ቀጭን፣
በሩም ጠባብ ነው፤ የሚገቡበትም ጥቂቶች ብቻ ናቸው::

«ጠባብ» እና፣ «ሰፊ» የሚሉት የሚያመለክቱት ክርስቲያኖች የሚሆኑ ሰዎችን አንጻራዊ ብዛት ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ መንገድ ቀላል ወይም አዳጋች መሆኑንም ጭምር ነው:: «ጠባብ» የሚለው፣ «ችግርን፣ አስጨናቂ ሁኔታን» ያመለክታል:: እንዲህ ሲባል ግን እንደ ልብ የሚሄዱበት፣ መለኪያ ሚዛን የሌለውና ምንም ዋጋ የማያስከፍለው አሕዛብ የሚሄዱበት መንገድ የደስታ ሕይወት ነው ማለት አይደለም:: እርስ በርሱ የሚጋጭ በሚመስል መልኩ ሥጋዊ ምኞታችንን ለማሳካትና ለማሟላት በምናደርገው ውጣ ውረድ ለዘለቄታው ሕይወታችንን እንጐዳለን:: በሌላ በኩል ደግሞ ራሳችንን ለክርስቶስ ስናስረክብ እውነተኛ ሕይወትና ደስታ ይኖረናል (ማቴ 10፥39፤ ዮሐ10፥10):: መጀመሪያ ላይ አስጨናቂና አዳጋች የሚመስል ይህ መንገድ ውሎ አድሮ ነጻነትን የሚያጎናጽፍ፣ በጎና የሚያሳርፍ ይሆናል (ማቴ 11፥28-30)::

ኢየሱስ መልካምና ክፋውን በእንዲህ ያለ ግልጽነት ለያይቶ ማቅረቡ፣ ነገሮችን መሸቃቀጥ የለመደ ማኅበረ ሰብን ሊያስቆጣ ይችላል:: እንዲህ ያለውን ትምህርት ጠባብነት፣ ምስኪንነትና ሌላው ቀርቶ አክራሪነት እንኳ በማለት እንጠራዋለን:: ምናልባት አንዳንዶች አእምሮአቸውን የሳቱት አእምሮአቸው ከመጠን በላይ ሰፊ በመሆኑ ይሆን?

### ሁለት ዐይነት ፍሬዎች

ማቴ 7፥15-20

[15]በውስጣቸው ነጣቂ ተኩላዎች ሆነው ሳሉ የበግ
ለምድ ለብሰው መካከላችሁ በመግባት ከሚያሸመቁ ሐሰተኛ
ነቢያት ተጠንቀቁ:: [16]ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፤ ከእሾህ
ቁጥቋጦ ወይን፣ ኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? [17]እንዲሁም ጥሩ ዛፍ ሁሉ ጥሩ ፍሬ፣
መጥፎ ዛፍ ግን መጥፎ ፍሬ ያፈራል:: መጥፎ ፍሬ፣ መጥፎም ዛፍ ጥሩ ፍሬ ማፍራት
አይችልም:: [19]ጥሩ ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል::
[20]ስለዚህ በፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ::

ሉቃ 6፥45

[45]መልካም ሰው በልቡ ከሞላው መልካም ነገር
መልካሙን ያወጣል፤ ክፉ ሰውም በልቡ ከሞላው ክፉ ነገር
ክፋውን ያወጣል፤ ሰው በልቡ ሞልቶ የተረፈውን በአፉ
ይናገራልና::

ነቢይ ከእግዚአብሔር መገለጥን የሚቀበልና ለሰዎች የሚናገር ነው:: አንዳንዴ እነዚህ መገለጦች የወደፊቱ ሁኔታን፣ አንዳንዴ አሁን ያለውን፣ አንዳንዴም ያለፈውን ያመለክታሉ:: አንድን ሰው ነቢይ የሚያሰኘው እየተናገረ ያለው ስለ የትኛው ጊዜ የመሆኑ ጉዳይ ሳይሆን፣ መልእክቱን የተቀበለው ከእግዚአብሔር መሆኑ ላይ ነው (ኤር 23፥16 18 22) ስለሆነም ሐሰተኛ ነቢይ (ከማቴ 24፥11-14፤ 2ጴጥ 2፥1-3፣17-22 ጋር ያነ) እግዚአብሔር ሳይናገረው፣ «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ...» የሚል ነው:: በተጨማሪም ሐሰተኛ ነቢያት (2ቆሮ 11 ፥13-15)፣

ሐሰተኛ መምህራን (2ጴጥ 2÷1) እና ሐሰተኛ ክርስቶሶች (ማቴ 24÷24) አሉ:: ዋናው ነጥብ አንዳንዶች እውነተኛ ባሕርያቸውን በመሰወር (ቁ 15) የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመበዝበዝ እንዲያመቻቸው ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው ሊናገሩ እንደሚችሉ ማመልከት ነው:: ምንም እንኳ የምንባቡ ዐላማ የሐሰት ትምህርትን ለይተን ማወቅ ስለምንችልበት ሁኔታ መመሪያ መስጠት ባይሆንም፣ ቤተ ክርስቲያን መዘናጋት እንደሌለባት ያሳስባል:: መንጋውን ለመበተን ሰይጣን በማንኛ ውም መንገድ ሊጠቀም ይችላል (ዮሐ 10÷11-13):: ብዙውን ጊዜ ሥልጣን ፈላጊ በሆኑ ሰዎች ይጠቀማል (ሐሥ 20÷29-30):: ኢየሱስ የዋህነትና ጥበብን መጥነን መያዝ እንዳለብን አመልክቷል (ማቴ 10÷16)::

የሐሰት ነቢይን ማወቅ የሚቻለው እንዴት ነው? በመጀመሪያ፣ ከፍሬአቸው የተነሳ ነው:: ምንጊዜም ቢሆን በስም ብቻ ክርስቲያን የሆኑ ሰዎች ይኖራሉ:: በጠባቡ መንገድ እየሄዱ እንደሆነ እየተናገሩ እነርሱ ግን በሰፊው መንገድ ይሄዳሉ:: አንዳንድ የዛፍ ዐይነቶች በሚገርም ሁኔታ ይመሳሰላሉ:: ምን ዐይነት ዛፍ መሆናቸውን ለይቶ መናገር ከመቻሉ በፊት ለዓመታት ያድጋሉ:: ፍሬያቸውን መሰወር ግን አይቻልም:: በተወሰነ ደረጃ እውነተኛ ባሕርያችንን መደበቅ ይቻላል:: ፍሬያችን ግን ማን መሆናችንን ይገልጣል::

ሁለተኛ፣ ስለ ጠባብና ሰፊ የሚናገረውን ዐውድ በሚገባ መረዳት ይኖርብናል:: «በቀላሉ» ድነት ማግኘት እንደሚቻልና ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ የተለያዩ መንገዶች እንዳሉ የሚናገር ሁሉ ሐሰተኛ ነቢይ ነው:: እንደ ጥንቱ ሐሰተኛ ነቢያት ሁሉ፣ «ሰላም ሳይኖር፣ ሰላም ነው» ይላሉ (ኤር 6÷13-15):: ከትንቢተ ኤርምያስ ስለ ሐሰተኛ ነቢያት ሁለት የወል ባሕርያት እንመለከታለን:: ጥቅም ለማግኘት የሚስገበገቡና እፍረት የሌላቸው መሆናቸውን:: የፍትወት ርኩሰትና ገንዘብ ወዳድነት



ከሐሰተኛ ትምህርትና ቅጥረኛ አገልግሎት የማይነጣጠሉ ባሕርያት ናቸው::

**ማቴ 7÷21-23**

21በሰማይ ያለውን ያባቴን ፈቃድ ሳይፈጽም 'ጌታ
ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤' የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ
አይገባም:: 22በዚያ ቀን ብዙዎች፣ 'ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤
በስምህ ትንቢት አልተናገርንም? በስምህስ አጋንንት
አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ታምራት አላደረግንምን?
ይሉኛል:: 23በዚያ ጊዜ፣ ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ
ክፉዎች፣ ከእኔ ራቁ!' ብዬ በግልጽ እነግራቸዋለሁ::

ሰዎች ከመንፈሳዊው ነገር ይልቅ ስሜት ቀስቃሽ ለሆኑ ጉዳዮች ትኩረት በመስጠታቸው ብዙዎች በአስመሳይ ፍሬዎች እየተታለሉ ነው:: አስመሳይ ፍሬዎች ስል ተአምራትን አስመስሎ ማቅረብ ማለቴ ነው (ቁ 22):: ማንም በቀላሉ ተአምራት መሰል ነገሮችን ማድረግ ስለሚችል፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ስለ ማግኘት ትክክለኛ ማስረጃ ሊሆኑ አይችሉም:: ከተአምር ናፋቂዎቹ መካከል አንዳንዶቹ ተራ አጭበርባሪዎች ናቸው:: አንዳንዶቹ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ፈንታ ብዙ ሕዝብ መሰብሰብ መቻልን እንደ አገልግሎት ስኬት የሚቆጥሩና ራሳቸውን ያሳቱ ናቸው::

«ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ» በማለት ተነግሮናል:: ችግሩ ግን የአንዳንዶቹ ዓላማ በጣም ስውር ሆኖ መዝለቁ ነው:: በፍርድ ቀን ግን የተሰወረው ሁሉ ይገለጣል (1ቆሮ 4÷5)::

እርግጥ ነው፣ እግዚአብሔር ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች እኛ ቅድሚያ የምንሰጣቸው ነገሮችን ያህል የሚያጓጉ አይደሉም፤ የውስጥም ናቸው:: የእግዚአብሔር መንግሥት ምንም ችግር የሌለበትና ሁሌ

የደስታ ፈንጠዝያ ያለበት አይደለም፣ የእግዚአብሔርን መንገድ ለመከተል የሚችልን የተሰበረን መንፈስ ይጠይቃል::[94]

### ሁለቱ ቤቶች

**ማቴ 7÷24-27**

[24]«እንግዲህ ይህን ቃሌን ሰምቶ በተግባር
የሚያውል፣ ቤቱን በዐለት ላይ የሠራን ብልኅ ሰው
ይመስላል:: [25]ዶፍ ወረደ፤ ጐርፍም ጐረፈ፤ ነፋስም
ነፈሰ፤ ያንን ቤት መታው፤ በዐለት መሠረትም ላይ ስለ ተመሠረተ አልወደቀም::
[26]ይህን ቃሌን ሰምቶ በተግባር የማያውለው ግን ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራን ሞኝ ሰው
ይመስላል:: [27]ዶፍ ወረደ፤ ጐርፍም ጐረፈ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንን ቤት መታው፤ ቤቱም
ወደቀ፤ አወዳደቁም የከፋ ነበር::»

«ከፍ ብሎ ባለው አንቀጽ ንጽጽሩ በመናገርና በማድረግ መካከለ ነበር፤ አሁን ግን 'በመስማት' እና 'በማድረግ' መካከል ሆኗል» (ስቶት፣ ገጽ 208):: በረሃነት ባለው ፓለስቲና ቤትን በዐለት ላይ ከመሥራት አሸዋ ላይ መሥራት ይቀላል (ሉቃ 6÷48):: በተመሳሳይም ለእርሱ ከመታዘዝ ይልቅ (ቁ 24) የኢየሱስ ቃል መስማትና (ቁ 26) ከእርሱ ጋር ኅብረት እንዳለ (ቁ 21-22) መናገር ይቀላል:: ይሁን እንጂ ጠንካራ መሠረት የሚኖረው ለሰሙት መታዘዝ ሲኖር ብቻ ነው::

ለአንድ መንገደኛ ሁለቱ ቤቶች አንድ ዐይነት መስለው ሊታዩት ይችላሉ:: ሆኖም ነፋስ ሲመጣ የተለያዩ መሆናቸው በግለጽ ይታያል:: በተመሳሳይ መልኩም ሁለት ክርስቲያኖች ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዱ፣ ይጸልዩ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ያነቡና ይዘምሩ ይሆናል:: ማንነታቸውን

[94] ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን የሚለማመዱ አብያተ ክርስቲያናት ከቁጥር 15-23 ያሉትን፣ በተለይም ለሐሰተኛ ነቢያትና ለተአምራዊ አሠራር የተለየ አጽንዖት የሚሰጡትን አስመልክቶ የተለያየ ችግር ገጥሟቸዋል:: ሆኖም ይህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን የሚለማመዱ ሰዎች ችግር ነው የምንል ከሆነ፣ ከቁጥር 1-5 ያለው ይመለከተናል ማለት ነው::



የሚገልጠው ግን ዐውሎ ነፋስ ሲመጣ ነው:: ይህን ምሳሌያዊ አነጋገር የምንጠቀመው፣ «በሕይወት ዘመን ስለሚያጋጥም ዐውሎ ነፋስ ለመናገር ነው:: አባባሉ እውነትነት አለው:: የመከራና ችግር ጊዜ የአንድን ሰው እምነት እውነተኛነት ይገልጣሉ:: አይሁድ ግን ይህን ምሳሌ የሚጠቀሙበት በተለይ ከፍርድ ጋር ለተያያዘው ጉዳይ ነው (ከሕዝ 13÷10 ጋር ያነ):: ስለሆነም በዐውዱ መሠረት በፍርድ ቀን የገነባነው ቤት ጽናት ይፈተናል (1ቆሮ 3÷12-15)::

### § 54
### ሕዝቡ ያሳየው ምላሽ
**(ማቴ 7÷28-8÷1)**

[28]ኢየሱስ ማስተማሩን በፈጸመ ጊዜ፣ ሕዝቡ
በትምህርቱ ተደነቁ:: [29]ምክንያቱም እንደ አይሁድ
ሃይማኖት መምህራኖቻቸው ሳይሆን እንደ ባለ ሥልጣን
አስተምሮአቸው ስለ ነበር ነው::
[1]ከተራራው በወረደ ጊዜም ብዙ ሕዝብ ተከተለው::

አንድን ስብከት ስለ ፍርድ በሚናገር ዐረፍተ ነገር መደምደም በጣም አስደንጋጭ ነው:: ይሁን እንጂ የመልእክቱ ግልጽነት የሚያሻማ አይደለም:: ምንም ማምለጫ መንገድ እስክናጣ ድረስ መልእክቱ ሥር ነቀል ቢሆንም ከመስማማት በቀር ሌላ ምርጫ ሊኖረን አይችልም:: ትእዛዙን ዐውቀን እንዳላወቀ ማለፍ ብንሞክር እንኳ ከልብ የማይወጡ ምሳሌያዊ ንግግሩ እንደ ገና ወደ ቦታችን ይመልሱናል:: በትምህርቱ መሠረት ለመኖር ስንወስን የራሳችን ግብዝነትና ስውር ዐላማ ሊተናነቁን ይችላሉ:: ጸጥ ብሎ ሲያደምጥ የነበረው ሕዝብም በእንዲህ ዐይነቱ ትምህርት መገረሙ ሊያስደንቀን አይገባም:: ከዚያ በፊት እንዲህ ያለ ነገር ሰምተው አያውቁም:: ታዋቂ መምህሮቻቸው አንዳቸው የሌላውን ወይም የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል እየጠቀሱ ነበር የሚያስተምሯቸው:: ኢየሱስ ግን ከየትኛውም የሃይማኖት መምህር አልጠቀሰም:: ከቅዱሳት መጻሕፍት በመጥቀስ በተናገረበት ጊዜ ሁሉም፣ «እኔ ግን እላችኋለሁ»

በማለት በጽሑፍ ካሰፈረው ቃለ አልፎ ለመሄድ እንኳ ነጻ ነበር:: «እንዲህ ያለው ስብከት የሚያሳየው አጉል አስመሳይነትንና ከፍተኛ ስሕተትን ወይም ደግሞ በፍጹም ችላ ልንለው የማይገባ የእግዚአብሔር አንደበት መሆኑን ነው» በማለት የነገሩን ጭብጥ አንጸባርቋል (ገጽ 135)::

የማቴዎስ ወንጌል፣ «ኢየሱስ ማስተማሩን በፈጸመ ጊዜ» በሚል ሐረግ በሚደመድሙ አምስት ትምህርቶች ዙሪያ ያጠነጥናል (7÷28-29፤ 11÷1፤ 13÷53፤ 19÷1፤ 26÷1):: ይህ ስብከትም ታዲያ የማቴዎስ ወንጌል የመጀመሪያው ክፍል ያበቃበት ነው::

## እየሰፋ የመጣው የኢየሱስ ዝና

**§ 55**
**የመቶ አለቃው አገልጋይ መፈወስ**
**(ሉቃ 7÷1-0፤ ማቴ 8÷5-13**

[1]ኢየሱስ ይህን ሁሉ በሕዝቡ ፊት ተናግሮ ከጨረሰ
በኋላ ወደ ቅፍርናሆም ገባ:: [2]በዚያም አንድ የመቶ
አለቃ ነበረ፤ እጅግ የሚወደው አገልጋዩም ታሞበት
ለሞት ተቃርቦ ነበር:: [3]እርሱም ስለ ኢየሱስ በሰማ ጊዜ
አገልጋዩን እንዲፈውስለት ይለምኑት ዘንድ አንዳንድ
የአይሁድ ሽማግሌዎችን ላከበት:: [4]መልእክተኞቹም ወደ
ኢየሱስ በመጡ ጊዜ እንዲህ ብለው አጥብቀው ለመኑት፤
«ይህን ልታደርግለት ይገባዋል፤ [5]ምክንያቱም ይህ ሰው
ሕዝባችንን ይወዳል፤ ምኩራባችንንም ያሠራልን እርሱ
ነው::» ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ሄደ::

ኢየሱስ ታላቁን ስብከት ከጨረሰ በኋላ ወደ ቅፍርናሆም ተመለሰ:: እዚያ በነበረ ጊዜ አንድ ታዋቂ መቶ አለቃ የአይሁድ ሽማግሌዎችን ላከበት:: የመቶ አለቃውን አገልጋይ እንዲፈውስለት ኢየሱስን ለመኑት:: ማቴዎስ ግን መቶ አለቃው ራሱ ወደ ኢየሱስ መምጣቱን ይናገራል:: ይህ ማለት ማቴዎስና ሉቃስ እርስ በርሱ



የሚቃረን ነገር አቅርበዋል ማለት ነውን? የግድ እንዳዚያ ነው ማለት አይደለም:: ማቴዎስ ሁኔታውን በአጭሩ ነበር ያቀረበው፤ መልእክተኞቹን የላከው እርሱ እንደ መሆኑ መጠን፣ እርሱ ራሱ ወደ ኢየሱስ መጣ ማለት ይቻላል::[95] ከዚያም በተጨማሪ ማቴዎስ ስለ አይሁድ መሪዎች ቀና ቀናው ስላላስተጋባ ይህን ክፍል መግደፉ ከአጻጻፉ ጋር የሚስማማ ነበር::[96] በአንጻሩ ደግሞ ሉቃስ ለአሕዛብ የተደረገ መልካም ነገርን ለማሳየት ዝርዝር ጉዳዮችን ይጽፍ ነበር:: ስለሆነም እዚህ ላይ የምንመለከተው እርስ በርሱ የተምታታ ነገርን ሳይሆን የአቀራረብ ልዩነትን ይሆናል::

ምንባቡ አጽንዖት የሚሰጠው ለመቶ አለቃው እንጂ ለታመመው አገልጋይ አይደለም:: ምንም እንኳ የዐረፍተ ነገሩ ርዕሰ ጉዳይ አገልጋዩ ቢሆንም ጉላ ብሎ እንዲታይ በዐውዱ አግባብ ከፍ ያለ ቦታ የተሰጠው፣ «መቶ አለቃ» ለሚለው ቃል ነው::

መቶ አለቃ በሮም መንግሥት ሠራዊት ውስጥ የሚያገለግል ወታደራዊ መሪ ነበር::[97] «መቶ አለቃ» የሚለው መጠሪያ እንደሚያመለክተው አንድ መቶ ያህል ወታደሮች ላይ ኀላፊነት ነበረው:: አዲስ ኪዳን የተወሰኑ የመቶ አለቃዎችን የጠቀሰ ሲሆን ስለ ሁለም

---

[95] Z.C. Hodges, "The Centurioan’s Faith in Matthew and Luke" *BibSac* 121 (Oct 1964): 321-332, ማቴዎስ እንደሚለው መቶ አለቃወ ወደ ኢየሱስ መጥቷል፤ እንደዚያ ያደረገው፣ «በአንተ ፊት ለመቅረብ እንኳ እንደሚገባኝ ራሴን አልቆጠርሁም» ካለ በኋላ ነበር (ሉቃ 7÷7):: ስለሆነም ዐውዱ እርስ በርስ መቃረኑን ሳይሆን መቶ አለቃው ሐሳቡን መለወጡን ነው የሚያመለክተው ብሏል:: ይሁን እንጂ ይህ አሳማን አይደለም፤ ምክንያቱም፣ (1) የታሪኩ አንኳር ሐሳብ የመቶ አለቃውን እምነት ማሳየት ነበር ሐሳቡን ለውጦአል የሚለው ከዚህ ጋር አይስማማም፤ (2) ወደ ቤቱ እንዳይመጣ እንዲነግሩት መቶ አለቃው ሁለተኛ የመልእክተኞች ቡድን ወደ ኢየሱስ ልኮአል::

[96] በተጨማሪም ማቴዎስ ይህን ታሪክ ያሰፈረው ከለምጻሙ መፈወስ ቀጥሎ በመሆኑ ተመሳሳይነታቸውን አጉልቶታል:: ለምጻሙም ሆነ መቶ አለቃው ወደ ኢየሱስ መጥተዋል፤ ሁለቱም በእስራኤል የተናቁ ነበሩ፤ ሁለቱም ታላቅ እምነት ስለ ነበራቸው ኢየሱስ ተቀብሏቸዋል::

[97] E. Ferguson, *Background of Early Christianity* (Grand Rapids: Eerdmans, 1987), pp. 38-42.

የሚናገረው በመልካም ነው፤ (1) ኢየሱስ በተሰቀለ ጊዜ በስፍራው የነበረ መቶ አለቃ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መስክሯል (ማቴ 27÷54፤ ማር 15÷39፤ ሉቃ 23÷47):: (2) ከሐዋርያት ሥራ 10-11 የምንመለከተው ቆርኔሌዎስ ሙሉ በሙሉ በኢየሱስ ማመኑን አሳይቷል:: እርሱም ሆነ ቤተሰቡ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል፤ በኋላም ተጠምቀዋል:: (3) ከሐዋርያት ሥራ 27 እንደምንመለከተው ጳውሎስ ወደ ሮም በተወሰደ ጊዜ ይጠብቀው የነበረ ዩልያስ የሚባል መቶ አለቃ ነበር:: ይህ ሰው ቀና እና ደግ ነበር:: (4) ምናልባት ክፉ ልንለው የምንችለው ሐዋርያት ሥራ 22÷25-26 ላይ የምንመለከተው መቶ አለቃ ብቻ ሊሆን ይችላል:: ጳውሎስን ሊገርፍ ነበር፤ ይህን ቢያደርግ እንኳ ሰው ስለሆነ ሊሆን ይችላል:: ያም ሆኖ ግን ጳውሎስ ሮማዊ ዜግነት ያለው መሆኑን ሲያውቅ ሐሳቡን ትቶታል:: አጠቃላይ በሆነ መልኩ ስናየው አዲስ ኪዳን መቶ አለቆችን ያቀረበው በአዎንታዊ ገጽታቸው ነበር፤ ምክንያታዊ፣ የሚያመዛዝኑና ሥልጣን አክባሪዎች መሆናቸውን ነው የምንመለከተው::

አገልጋዩ፣ «እጅግ የሚወደው» ነበር፤ የዚህ ጥቅስ ሌሎች ምንባቦች እንደሚሉት ይህ ከፍተኛ ክብርን የሚያመለክት አባባል ነበር:: በሉቃስ 7÷7 እና ማቴዎስ 8÷6 መሠረት እንደ አገልጋይ ሳይሆን እንደ ልጅ ነበር የተነገረለት:: በሌላ አነጋገር ከአገልጋይ የበለጠ ነበር ማለት ነው፤ ለመቶ አለቃው እንደ ልጅ ሆኖለታል::

መቶ አለቃው ኢየሱስ ሰዎችን በመፈወስ ስለ ነበረው ዝና ሲሰማ እንዲረዳው እንዲነግሩለት የአይሁድ ሽማግሌዎችን ወደ ኢየሱስ ላከ:: አይሁድ ከመንገድ ወጥተው አረማውያንን መርዳታቸው በፍጹም የማይታሰብ ነበር:: ይህ ሰው ግን የተለየ አረማዊ ነበር:: የነበረውን ሥልጣን በመጠቀም፣ ምናልባትም የራሱን ገንዘብ ጭመር በመስጠት ጭምር በቅፍርናሆም የነበረውን ምኩራብ እንዲሠሩ ረድቷል:: መልካም ላደረገ ደግሞ መልካም ሊደረግለት ይገባል::



ሉቃ 7÷6-8

6እርሱም ወደ ቤቱ በተቃረበ ጊዜ፣ የመቶ
አለቃው ወዳጆቹን ልኮ እንዲህ አለው፤ «ጌታ ሆይ፤
ከቤቴ ጣራ በታች ልትገባ የሚገባኝ ሰው አይደለሁምና
አትድከም፤ 7ከዚህም የተነሣ በአንተ ፊት ለመቅረብ እንኳ እንደሚገባኝ ራሴን
አልቆጠርሁም፤ ብቻ አንድ ቃል ተናገር፤ አገልጋዬ ይፈወሳል:: 8እኔ ራሴ የበላይ አለቃ
አለኝ፤ ከበታቼም የማዛቸው ወታደሮች አሉኝ፤ አንዱን፣ 'ሂድ' ስለው ይሄዳል፤
ሌላውን፣ «ና» ስለው ይመጣል፣ አገልጋዬንም፣ 'ይህን አድርግ' ስለው የታዘዘውን
ያደርጋል::

መልእክተኞቹ ኢየሱስ ወደ ሰውየው ቤት እንዲሄድ በመጠየቃቸው የራሳቸውን ገደብ ሳያልፉ ወይም ቢያንስ የመቶ አለቃው ፍላጐት ያልነበረ ነገር ሳይጠይቁ አልቀረም:: ስለሆነም ኢየሱስ ወደቤቱ እንዳይመጣ ለመናገር የመቶ አለቃው ቅርብ ወዳጆች ያሉበት ሁለተኛ የመልእክተኞች ቡድን ተላከ::

መልእክቱ ግልጽ ነው፤ «አትድከም»! (ቃል በቃል «አትጣደፍ»):: ዋናው አንኳር ሐሳብ እያደረግህ ያለውን «አቁም» እንደ ማለት ይሆናል:: መቶ አለቃው ከኢየሱስ ጋር የነበረውን ሕዝብ አይቷል ወይም ምን ያህል ሕዝብ እየመጣ መሆኑን ሰምቷል፤ ስለዚህም ኢየሱስ ወደ ቤተ በመምጣት ተጨማሪ ድካም እንዲደርስበት አልፈለገም:: ምናልባትም ኢየሱስ ያን ሁሉ መንገድ ተጉዞ ወደ ቤቱ መምጣቱ አልነበረም እርሱን ያሳሰበው:: ኢየሱስ ወደ አንድ ከአሕዛብ ወገን ወደ ሆነ ሰው ቢገባ፣ በገዛ ሕዝቡ ሊነቀፍ ይችላል (ከሐሥ 10÷28 ጋር ያነ):: ያ መቶ አለቃ የኢየሱስ ስም እንዳይጐድፍ የተቻለውን ሁሉ ለማድረግ እየሞከረ ነበር::

ወታደር እንደ መሆኑ መጠን ቃል ምን ያህል ሥልጣን እንዳለው ይገነዘባል:: ኢየሱስ የግድ በቦታው መገኘት ወይም አገልጋዩን መዳሰስ አልነበረበትም:: ከእርሱ የሚጠበቀው ማዘዝ ብቻ ነበር (ከመዝ

107÷20 ጋር ያነ)። ሥልጣን ይህን ይመስላል። ኢየሱስ ሠላሳ ሁለት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሆኖ በቅፍርናሆም የነበረውን የሹሙን ልጅ ከመፈወሱ በቀር «በርቀት መፈወስ» መቻሉን እንዲያምን የሚያደርገው ከዚያ አስቀድሞ የተፈጸመ ሁኔታ አልነበረም (ዮሐ 4÷46-54)። ምናልባትም ያ ሰው ስለዚያ ታሪክ ሳይሰማ አልቀረም። ያም ሆኖ ግን እምነቱ በጣም አስደናቂ ነበር።

መቶ አለቃው፣ በነበረው ወታደራዊ ሥልጣንና ኢየሱስ በነበረው መንፈሳዊ ሥልጣን መካከል ተገቢ የሆነ ንጽጽር አድርጓል። ለእርሱ ሥልጣን የሰጠው የበላይ አካል አለ፤ እርሱ የሚያዛቸውም ከእርሱ በታች ያሉ ሰዎችም አሉ። ኢየሱስ ከአብ ዘንድ ሥልጣን መቀበሉንና ከበታቹ ያሉ ነገሮችን ማዘዝ እንደሚችል ተገንዝቧል (ለምሳሌ ሕመምና ተፈጥሮን)።

ማቴ 8÷10-13

10ኢየሱስም በሰማ ጊዜ ተደንቆ ይከተሉት ለነበሩት እንዲህ አላቸው፤ «እውነት እላችኋለሁ፣ ከእስራኤል መካከል እንኳ እንዲህ ያለ እምነት ያለው አንድ ሰው አላገኘሁም፤ 11እላችኋለሁ፣ ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ በመንግሥተ ሰማይ ማእድ ዙሪያ ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር ይቀመጣሉ፤ 12መንግሥተ ሰማይ ተዘጋጅቶላቸው የነበሩት ግን ወደ ውጭ ወደ ጨለማው ይጣላሉ። በዚያም ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።»

13ኢየሱስም መቶ አለቃውን፣ «ሂድ እንደ እምነትህ ይሁንልህ» አለው። አገልጋዩም በዚያች ቅጽበት ተፈወሰ።

ሉቃ 7÷10

10የተላኩት ሰዎችም ወደ ቤት በተመለሱ ጊዜ፣ አገልጋዩን ድኖ አገኙት።

ይህ ኢየሱስ መደነቁን ከገለጸባቸው ሁለት አጋጣሚዎች መካከል አንዱ ነው። እዚህ ላይ የተደነቀው በዚያ አረማዊ ታላቅ እምነት ሲሆን፣ ከማርቆስ 6÷6 እንደምንመለከተው በናዝሬት የራሱ ወገኖች ባለማመናቸው ነበር። ቅዱሳት መጻሕፍት የነበራቸው አይሁድ (ሮሜ 3÷1-2) ማመን ሲያቅታቸው፣ አሕዛብ ግን ያንን የመሰለ እምነት ማሳየታቸው ግራ የሚያጋባ ነበር።

ኢየሱስ ራሱም ቢሆን ሌላ እርስ በርሱ የሚቃረን የሚመስል ነገር አቅርቧል። በመሲሑ ግብዣ ላይ ለመገኘት ይጠብቁ የነበሩ አይሁድ (ኢሳ 25÷6፤ ማቴ 26÷29 ሉቃ 22÷30) ወደ ውጭ ተጥለዋል። ባዕዳን ግን ወደ ውስጥ ገብተዋል። ከዚህ ታሪክ የምንመለከተው ግልጽ ትምህርት ኢየሱስ ዘርን ሳይሆን እምነትን የሚያከብር መሆኑን ነው። ስለሆነም አሕዛብ ወደ መንግሥቱ እንደሚጨመሩ የተናገረ አስገራሚ ንግግር ነው የምናየው (ሐሥ 10÷11)።

## § 56 በናይን የመበለቲቱ ልጅ ከሞት መነሣት (ሉቃ 7÷11-17)

ማቴዎስ ተመሳሳይነታቸውን ለማሳየት የመቶ አለቃውን አገልጋይ መፈወስ፣ ከለምጻሙ መፈወስ ጋር አያይዞ አቅርቦታል። ሉቃስ ግን የሚያያይዘው ከመበለቲቱ ልጅ ከሞት መነሣት ጋር ነው። ከሁለቱም የምንመለከተው ያልታሰቡ ወገኖች የጌታን ትኩረት መሳብ በመቻላቸው ውድ የሆነው፣ «ልጅ» ከሞት መነሣቱ ነው።

ይህ ኢየሱስ ከሞት ካስነሣቸው ሦስት ሰዎች የመጀመሪያው ነው። ሁለቱ ግን የኢያኢሮስ ልጅ (ማቴ 9÷18-26፤ ማር 5÷22-43፤ ሉቃ 8÷49-56) እና የኢየሱስ ወዳጅ የነበረው አልዓዛር ናቸው (ዮሐ 11)። ኤልያስ የመበለት ልጅ እንዳስነሣ ሁሉ (1ነገ 17÷17-24፤ በ2ነገ 4÷32-37 ካለው ከኤልሳዕ ታሪክ ጋር ያነ)፣ ኢየሱስም እንዲሁ

አድርጓል:: ስለሆነም የኢየሱስ አገልግሎት ከታላቁ ነቢይ ከኤልያስ ጋር ተመሳስሏል ማለት ነው::[98]

[11]ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ብዙ ሳይቆይ፣ ናይን
ወደምትባል ከተማ ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱና ብዙ ሕዝብም
አብረውት ሄዱ:: [12]ወደ ከተማዋ መግቢያ በር ሲደርስም፣
እነሆ ሰዎች የአንድ ሰው አስከሬን ተሸክመው ከከተማዋ ወጡ፤ ሟቹም ለእናቱ አንድ
ልጅ ብቻ ነበር፤ እናቱም መበለት ነበረች፤ ብዙ የከተማውም ሕዝብ ከእርሷ ጋር
ነበር:: [13]ጌታም ባያት ጊዜ ራራላትና «አይዞሽ አታልቅሺ» አላት::

ሉቃ 7÷11-13

በናይን የዚህች መበለት ልጅ ከሞት የተነሳው የመቶ አለቃው አገልጋይ እንደ ተፈወሰ ጥቂት ጊዜ ቆይቶ፣ ምናልባትም በማግሥቱ ነበር::[99] ትንሿ የናይን («አስደሳቿ») ከተማ ከቅፍርናሆም ደቡብ ምሥራቅ አምስት ማይሎች፣ ኤልያስ የሱናማዊቷን ልጅ ከሞት ካስነሣበት ከሱናም ኮረብቶች ባሻገር ነበር የምትገኘው:: ለአካባቢው ሰዎች ይህ የተለየ ትዝታ ያለው መሆኑ ግልጽ ነው:: በአሁኑ ጊዜ ከሱናም የቀረ ነገር ቢኖር ከከተማዋ ውጪ ከኮረብቶች ተፈልፍለው የተሠሩ መቃብሮች ብቻ ናቸው:: ምናልባትም በዚህ ቀን ቀትር ላይ የናይን ነዋሪዎች ከእነዚህ መቃብሮች ወደ አንዱ እየሄዱ ሊሆን ይችላል:: ያቺ ምስኪን ሴት ባልዋንና ልጇን አጥታለች:: ያለምንም ረዳት ብቻዋን ቀርታለች:: የመንደሩ ሰው በጣም ሳያዝንላት አልቀረም::

[98] C.A. Evans, "Luke's Use of the Elijah/Elisha Narratives and the Ethic of Election" *JBL* 106/1 (1987): 75-83 ሉቃስ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ የኤልያስ/ኤልሳዕን ተአምር ጭብጥ ሐሳብ፣ በተለይም በመካከለኛው ክፍሉ እንደ ተጠቀመበት ያሳያል (ሉቃ 4÷25-27፤ 7÷11-17፤ 9÷52-55፣ 61-61):: እንዲህ በሚያደርግበት ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት ደጅ ለአሕዛብ ከከፈተው ታላቁ ነቢይ ጋር ኢየሱስን ማነጻጸሩ ይመስላል:: ይህ ደግሞ የመቶ አለቃውን አገልጋይ ከመፈወሱ አንጻር እዚህ ላይ መነሣቱ ተገቢ ነው::

[99] *"hexes"* የሚለው የግሪክ ቃል አንዳንድ ጊዜ ቀጣዩን ቀን ያመለክታል እንጂ በፍጹም ረጅም ወቅትን አያመለክትም::



ከከተማው ውጪ ወደ ነበረው መቃብር ብዙ ሕዝብ ተከትሎ እያመራ ነበር:: መንገድ ላይ ወደ ከተማው በመግባት ላይ ካለ ብዙ ሕዝብ ጋር ተገናኙ:: በገሊላውያን ቀብር ሥርዓት መሠረት የመጀመሪያው ወገን መጐናጸፊያዋን በቀደደች ሴት የሚመራ ነበር (*Jer. Moed. K.* 83 d)::[100] ቀኑን ሙሉ ከቅፍርናሆም ሲጓዝ የነበረው ሁለተኛው ወገን በኢየሱስ እየተመራ ነበር:: ወደ መቃብር እየሄደ ያለ ሕዝብ በእንዲህ ያለ የመንገድ መጨናነቅ ውስጥ መሆኑ ያልተለመደ፣ ምናልባትም አስደንጋጭ ሊሆን ይችላል::

የአይሁድ ቀብር ደንብ ሰው መሞቱን በሚያሳውቅ መለከት፣ ዋሽንትና በስልታዊ መልክ በሚንሿሿ ጸናጽል ድምፅ የሚታጀብ ደመቅ ያለ ሥርዓት ነበረው:: ሌላው ቀርቶ በጣም ድሆች የሆኑ አይሁድ እንኳ ቢያንስ ሁለት ዋሽንት ተጫዋቾችንና አልቃሽ ሴት ማቆም ይጠበቅባቸው ነበር (*Kethub*. iv. 4):: የአስከሬኑ ፀጉር ይላጫል፤ ጥፍሩም ይቆረጣል:: ከዚያ በኋላ ፊቱ ወደ ላይ ተደርጐ፣ ክንዶቹ ደረቱ ላይ ተመሳቅለው ቃሬዛ ላይ እንዲጋደም ይደረጋል:: ሟቹን የመሸከም ክብር ለማግኘት አስከሬኑ ከቤት ሲወጣ ወዳጅ ዘመዶቹን ጨምሮ ብዙ ሰዎች ተራ በተራ ይሸከሙታል:: «ሟቹ ወደ መጨረሻ ማረፊያው ሲሄድ አለመሸኘት ፈጣሪን የመሳደብ ያህል ነው» ስለሚባል በአካባቢያቸው ሲያልፍ የናይን ነዋሪዎች ከለቀስተኛው ጋር ሆነው ሬሳውን ይሸኛሉ (Edersheim I:556):: አንድ ሰው መሸኘት ባይችል እንኳ ቢያንስ ለቀስተኛው ሲያልፍ መቆየት ይኖርበታል:: በአንድ በኩል እግዚአብሔርን በመፍራት፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ «የሟቹ መንፈስ ገና ባልተቀበረ አካሉ ዙሪያ ያንዣብባል» (Edersheim I:554) ከሚል አፈ ታሪክ የተነሣ የቀብር ሥርዓት የተለየ አክብሮት ይደረግለታል::

[100] ሚድራህ የሚያቀርበው ምክንያት ሞትን ያመጡ ሴቶች በመሆናቸው ወደ ቀብር በሚደረገው ጉዞም መቅደም አለባቸው የሚል ነው::

ኢየሱስ የሰውን ስሜት የሚጋራ በመሆኑ በሁኔታው አላዘነም ማለት አይቻልም:: ለሴትየዋ በጣም አዘነላት (*Splanchnizomai*):: ቃል በቃል ከወሰድነው መበለቲቱን «አታልቅሺ» ነበር ያለው:: በእንዲህ ያለ ሁኔታ ውስጥ ላለ ሰው እንዲህ ማለት የሌላው ቁስል የማይሰማው ጨካኝ ሊያሰኝ ይችላል:: ይሁን እንጂ የኢየሱስ ድምፀትና ሁኔታ የተሻለ ነገር ፊትዋ መኖሩን ሳያረጋግጥላት አልቀረም::

[14]ቀረበ ብሎም ቃሬዛውን ነካ፤ የተሸከሙትም
ሰዎች ቀጥ ብለው ቆሙ:: ኢየሱስም፣ «አንተ ጐበዝ ተነሥ    ሉቃ 7÷14-17
እልሃለሁ» አለው:: [15]የሞተውም ሰው ቀና ብሎ ተቀመጠ፤
መናገርም ጀመረ:: ኢየሱስም ወስዶ ለእናቱ ሰጣት::
[16]ሁሉም በፍርሀት ተውጠው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ «ታላቅ ነቢይ
በመካከላችን ተነሥቶአል»፤ [17]ይህም የኢየሱስ ዝና በመላው ይሁዳና″ በአካባቢው ባለው
አገር ሁሉ ወጣ::»

*″17ወይም በአይሁድ ምድር*

እንደ ደንቡ ቢሆን ኖሮ፣ ኢየሱስ ያደረገውን ማንኛውም አይሁዳዊ ማድረግ አልነበረበትም:: በአይሁድ ሥርዓት ሬሳን የመንካት ያህል ሰውን ያረክሳል የሚባል ነገር አልነበረም (ዘሌ 19÷11፣16):: የሞተው ወደ ሕይወት በሚመለስበት ጊዜ ግን እነዚያ ደንቦች መከበር ነበረባቸውን? የአይሁድ ሕግ መምህራን እንዲህ ያለውን ነገር በተመለከተ ምንም ደንብ ወይም መመሪያ አልነበራቸውም:: በጣም ከመደንገጣቸው የተነሣ ቃሬዛውን የተሸከሙት በድንገት ቀጥ ብለው ቆሙ::

ኢየሱስ ሲያዝ ጐልማሳው ተነሥቶ ተቀመጠ፤ ይናገርም ጀመረ:: ሬሳ ውስጡ ታምቆ ከነበረ አየር የተነሣ ስለ መቀመጡ ወይም ስለ መንቀሳቀሱ አንዳንድ አስደንጋጭ ታሪኮችን የሬሳ ቤት ሠራተኞች ይነግሩን ይሆናል:: መናገር ስለ ቻለ አስክሬን ግን ምንም የሚነግሩን



ነገር የላቸውም:: ከሞት የተነሣው ሰው ምን ማለት እንደሚችል አእምሮአችን የተለያዩ ነገሮችን አያስብም? ምናልባት፣ «የት ነው ያለሁት? ምን እያደረጋችሁ ነው» ብሎ ይሆናል፤ ወይም ደግሞ፣ «ጐበዝ፣ ጥሩ እንቅልፍ ወስዶኝ ነበር:: እንደዚህ ቀሎኝ አያውቅም» ብሎ ሊሆን ይችላል::

ሕዝቡ ያሳየው ስሜት በፍጹም የማይረሳ ነበር:: እንዲህ ያለው ሁኔታ ኢየሱስ ተአምር ባደረገ ጊዜ ሁሉ የተለመደ ነበር:: በጣም ፈርተዋል፤ እንዲያውም፣ «በፍርሃት ተውጠው» ነበር:: ይህ ደግሞ የሚገርም አይሆንም:: በኋላ ግን ፍርሀታቸው ወደ ምስጋና ተለወጠ:: ኢየሱስ ከኤልያስ እንኳ የሚበልጥ ኃይል ያለው ታላቅ ነቢይ መሆኑን ሕዝቡ ተረድተዋል:: በእርሱ በኩል እግዚአብሔር ሕዝቡን ጐብኝቷል:: ችግራቸውን ለማስወገድ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ተገኝቷል:: አነጋገራቸው መሲሑን በተመለከተ ሕዝቡ ይጠብቀው የነበረ ነገርን ያንጸባርቃል (ማቴ 1÷23፤ ሉቃ 1÷68፣78፤ 19÷44፤ መዝ 8÷4፤ ኢሳ 29÷6፤ ሶፎ 2÷7፤ ሐሥ 15÷14፤ ዕብ 2÷6):: ወሬው በአካባቢው ወደ ነበረው አገር ሁሉ ተዳረሰ::[101]

ሳይንሳዊ አመለካከት ያለው ማኅበረሰብ ይህን ክፍል በተመለከተ ምን ማለት ይችላል? በታሪክ ውስጥ የተፈጸመ ሐቅ መሆኑን መቀበል እንችላለን? ተአምርን አስመልክቶ ቀድሞውኑ በአእምሮን ሊኖር ከሚችል ትችት ውጪ ይህን ሐቅ እንዳንቀበል የሚያደርገን ምንም ዓይነት ታሪካዊ ወይም ነገረ መለኮታዊ ምክንያት አይኖርም:: ኢየሱስ ሙታንን ለማስነሣት ስላለው ኀይል ሉቃስ የሚያቀርበውን ምስክርነት ለማመን ግን በቂ ምክንያት ይኖረናል (Edersheim, I:558-560)::

[101] «ይሁዳ» የሚለው፣ «ደቡባዊ ፖላስቲናን» ብቻ ሳይሆ፣ «የአይሁዶችን አገር» ሁሉ ይመለከታል፤ ናይን የምትገኘው ገሊላ ውስጥ በመሆኑ እንደዚያ ማለቱ ከዐውዱ ጋር አይስማማም:: ይህ ወሬ በደቡባዊ ፖለስቲና ወዳለችው ኢየሩሳሌም ተዳረሰ ቢባል ግን ምክንያታዊ ይሆናል::

1. ይህ ታሪክ ግነት የበዛበት ነው ለማለት ወይም ለክስተቱ ተፈጥሮአዊ ምክንያት ማቅረብ በፍጹም አይቻልም:: ስለሆነም ሁለት ምርጫዎች ብቻ ይኖሩናል፤ ታሪኩ እውነት ነው፤ ወይም ሙሉ በሙሉ ፈጠራ ነው የሚሉ::[102]
2. ምንም እንኳ ኢየሱስ በናይን የመበለቲቱን ልጅ ከሞት እንዳስነሣ በወንጌሉ ያሰፈረ ሉቃስ ብቻ ቢሆንም፣ ሌሎቹ ሦስት ወንጌሎችም ኢየሱስ ከሞት ያስነሣው ሰው መኖሩን አስፍረዋል:: ስለሆነም ኢየሱስ ሰዎችን ከሞት የማስነሣት ኀይል ያለው መሆኑን የሚመሰክር ሉቃስ ብቻ አይደለም ማለት ነው::
3. አይሁድ መሲሑ ሲመጣ ሰዎችን ከሞት እንደሚያስነሣ እየጠበቁ አልነበረም:: ስለሆነም እንዲህ ያሉ ታሪኮችን ፈጥሮ ማውራት አስፈላጊ ሊሆን አይችልም ማለት ነው::
4. ምንም እንኳ ይህ ሁኔታ በብዙ መልኩ ከኤልያስና በሰራጵታ ከነበረችው መበለት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም (1ነገ 17÷8-24፣ በተለይ ቁ 10 እና 23 )[103] ኢየሱስ የመበለቲቱን ልጅ ከሞት ማስነሣቱ በዚህ ታሪክ ላይ የተመሠረተ እንዳልሆነ የሚያሳዩ ብዙ ልዩነቶች አሉ::
5. ታሪኩ የፈጠራ ቢሆን ኖሮ እንዲህ ላለው ታላቅ ተአምር ይህን ያህል ታዋቂነት ያልነበራት ናይን የታሪኩ መፈጸሚያ ስፍራ ለመሆን አትመረጥም ነበር::

[102] ፊሎስትራተስ ከሞት ስለ ተመለሱ ሰዎች ተመሳሳይ ነገር መጻፉ (*Life of Apollonius* 4.45) ሁለቱም ታሪኮች የፈጠራ ናቸው ለማለት `ምክንያት ሊሆን አይችልም:: እውነተኛነቱንና ታማኝነቱን ለማረጋገጥ እያንዳንዱን ታሪክ በተናጠለ መመርመር ነው ያለብን::

[103] T.L.Brodie, "Towards Unravelling Luke's Use of the Old Testament: Lk 7:11-17 as an *IMITATIO* of 1 Kings 17:17-24," *NTS* 32 (1986): 247-267, catalogues a number of these similarities, but also shows some significant differences.



6. ተአምሩ የተፈጸመው ብዙ ሰዎች ባሉበት ስፍራ ነበር:: አንዳንዶቹ በሕይወት ስለ ነበሩ በንጉሡ ፊት መመስከር ይችሉ እንደ ነበር ኳድራተ የተባለው ሰው አመልክቷል::
7. በጥንት ቤተ ክርስቲያን ከሞት የመነሣት ጉዳይ እንግዳ ነገር ያልነበረና ሐዋርያቱ ለመሞት ፈቃደኛ እስኪሆኑ ድረስ እምነቱን ተቀብለው ነበር (ከማቴ 10÷8፤ ሐሥ 9÷40፤ 20÷9-10 ጋር ያነ)::

**§ 57**
**የመጥምቁ ዮሐንስ ጥያቄ**
**(ማቴ 1÷12-19፤ ሉቃ 7÷18-35)**

ይህ በዮሐንስ ሕይወት የጨለማ ጊዜ ነበር:: ዐሥር ወሮችን ያህል በእስር ቤት አሳልፎአል (ከማቴ 4÷12፤ 14÷1-12፤ ሉቃ 3÷14-20 ጋር ያነ):: ቅዱሳት መጻሕፍት ምክንያቱንም ይናገራሉ:: ዮሐንስ ዘማዊውንና ከሥጋ ዘመዱ ጋር ጋብቻ የፈጸመውን ሄሮድስ ፊት ለፊት ገሥጾታል:: ሚስቱ ሄሮድያዳ ቂም ይዛበት ስለ ነበር ፀጥ እንዲያሰኘው ባልዋን መጐትጐት ጀመረች (ማቴ 4÷3-5):: ስለዚህም ወደ እስር ቤት ተጣለ:: ይሁን እንጂ፣ ታሪኩ ከዚህ የተለየ ገጽታም አለው:: ዮሐንስ ብዙ ተከታዮችን አፍርቶ ነበር:: የሄሮድስ ተወዳጅነት ግን እያሽቆለቆለ ነበር:: ይህ ደግሞ ለዐመፅ መነሣት ምክንያት ሊሆን ይችል ነበር:: ስለሆነም ዮሐንስ የታሰረው በእርሱ ምክንያት ዐመፅ እንዳይነሣ ታስቦ ነበር (Josephus, *Ant.* 18.5.2):: በተጨማሪም የአይሁድ መሪዎች እጅ ሳይኖርበት እንደማይቀር ጥርጣሬ ይኖረናል:: ኢየሱስን እንደሚጠሉ ሁሉ ዮሐንስንም አይወዱትም ነበር:: ምናልባት የእነርሱ ሤራ ሳይኖርበት እንደማይቀር መገመት ይቻላል::

ሉቃ 7፥18-20
ከማቴ 11፥2 ጋር

18የመጥምቁ ዮሐንስ (በእስር ቤት ሆኖ[ማቴ]) ደቀ
መዛሙርት ይህንን ሁሉ (ክርስቶስ በማድረግ ላይ
ያለውን[ማቴ]) ለዮሐንስ ነገሩት። እርሱም ከመካከላቸው
ሁለቱን ጠርቶ፣ ይመጣል የተባለልህ አንተ ነህ? ወይስ ሌላ
እንጠብቅ? በሉት» ብሎ ወደ ጌታ ላካቸው።
20ሰዎቹም ወደ ኢየሱስ መጥተው፣ «መጥምቁ ዮሐንስ ይመጣል የተባለልህ
አንተ ነህ? ወይስ ሌላ እንጠብቅ? ብሎ ወደ አንተ ልኮናል አሉት።

እስር ቤት ሆኖ ዮሐንስ ለማሰብ ሰፋ ያለ ጊዜ አግኝቶአል። ሞት ከእርሱ የራቀ አልነበረም። «ሕይወቴን በከንቱ አባክኜ ይሆን? ኢየሱስ በእርግጥ መሲሑ ነው፣ ወይስ አስተሳሰቤ ነድቶኝ ይሆን?» የሚሉ ሐሳቦች በዮሐንስ አእምሮ ሳይመላለሱ አልቀሩም። ስለሆነም ከእርሱ ጋር ከቀሩ ጥቂት ደቀ መዛሙርት ሁለቱን ኢየሱስን እንዲጠይቁ ላካቸው።

«ይመጣል የተባለልህ አንተ ነህ?»[104] የሚል ቃል ከዮሐንስ አንደበት ሲወጣ ወይም ጥርጥሩን ሲገልጽ መስማት የማይጠበቅ ነበር። በመጀመሪያ ደረጃ ኢየሱስን ያስተዋወቀው ዮሐንስ ራሱ ነበር። እናቱ ኤልሳቤጥ ስለ ክርስቶስ ልደት የምትናገረው ታሪክ ነበራት፤ እርሱም ሆነ ኢየሱስ ትንቢትን እየፈጸሙ እንደሆነም ይገነዘባል። ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜም በርግብ አምሳል የመጣ መለኮታዊ ማረጋገጫ አግኝቶ ነበር (ዮሐ 1፥32-34)። ታዲያ አሁን ለምን ተጠራጠረ?

ዮሐንስ ከአንድ ዓመት ያላነሰ በእስር ቤት ሳያሳልፍ እንዳልቀረ ማስታወስ አለብን። ይህ ራሱ መደበትንና ጥርጣሬን ለማምጣት በቂ ጊዜ ነው። በዚያ ላይ ደግሞ ኢየሱስ በወቅቱ ስለ መሲሑ ይታሰብ የነበረውን አሟልቶ አልተገኘም ነበር። ለዮሐንስ በተነገረው መሠረት ኢየሱስ አንዳንድ ያልተለመዱ ነገሮችን እያደረገ ነበር። ለመሆኑ፣

---

104 እዚህ ላይ ግሡ የአሁን ጊዜን የሚያመለክት በመሆኑ በኋላፊ ጊዜ ካስቀመጠው አመት ይልቅ፣ «የመጣው አንተ ነህ?» ቢባል የተሻለ ይሆናል።



ከአመንዝራዎችና ከቀረጥ ሰብሳቢዎች ጋር ምን የሚያገናኘው ነገር ነበር? እንደ ሌሎቹ ሁሉ የማይጾመው ለምንድነው? የተጠራበት ግብዣ ሁሉ የሚገኘው ለምንድነው? አገልግሎቱ የዮሐንስ ዓይነት አገልግሎት አልነበረም። ከዚያም በላይ ኢየሱስ ዮሐንስን ከእስር ቤት ነጻ የማያደርገው ለምንድነው? መሲሕ እስረኞቹን ነጻ እንደሚያወጣ በቅዱሳት መጻሕፍት ትንቢት ተነግሮ የለምን (ኢሳ 61፥1)? ምን እየጠበቀ ነው?

ዮሐንስ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያቀርበው ተጠራጣሪ ስለ ነበር ከመሆኑ ይልቅ ትዕግሥት ከማጣቱ እንደ ነበር ማሰብ ይቻላል። ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ያለ ጥርጥር ያምናል። እርሱ የሚፈልገው በሥራ ድርሻው መሠረት እንዲሠራ ብቻ ነበር። ከሚቀጥለው ንግግር መመልከት እንደሚቻለው ዮሐንስ የነበረበትን ጨለማ ማብራት በሚችል ሁኔታ ኢየሱስ ስለ ማንነቱና ስለ ዮሐንስም ጭምር በአጽንኦት ተናግሯል።

ሉቃ 7፥21-23

21በዚያኑ ጊዜ ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን ከበሽታ፣
ከደዌና ከርኩሳን መናፍስት ፈወሳቸው፤ የብዙ ዐይነ
ስውራንንም ዐይን አበራ። 22ከዮሐንስ ተልከው
የመጡትንም እንዲህ አላቸው፤ «ሄዳችሁ ያያችሁትንና
የሰማችሁትን ለዮሐንስ ንገሩት፤ ዐይነ ስውራን ያያሉ፤
ዐንካሶች በትክክል ይራመዳሉ፤ ለምጻሞች ነጽተዋል፤
ደንቆሮዎች ይሰማሉ፤ ሙታን ተነሥተዋል፤ ለድኾችም
ወንጌል ይሰበካል፤ 23በእኔ የማይሰናከል ሰው ሁሉ የተባረከ
ነው።»

*22የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያዩ የቆዳ በሽታዎችን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል።*

የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት በትክክለኛ ጊዜ ነበር የደረሱት:: ስለ ማንነቱ ኢየሱስን እየጠየቁ እያለ የተለያዩ ተአምራት ያደርግ ጀመር:: ምንም እንኳ ማቴዎስ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ተአምራቱ ሲደረጉ ማየታቸውን ባይነግረንም ከ8-9 ባሉት ምዕራፎች የተጠቀሱ ተአምራቶችን አቅርቧል:: ይህ ስለ መሲሑ ከተነገሩ ትንቢታዊ ምልክቶች አንዱ ነበር (ኢሳ 29÷18-19፤ 35÷5-6፤ 42÷7፤ 61÷1-3):: ስለ እነዚህ ነገሮች ለዮሐንስ መንገር ከመቻላቸው በተጨማሪ ኢየሱስ ስለ ራሱ ለተናገረው ምስክር መሆን የሚችሉ ብዙዎች ነበሩ፤ አንዳንዶቹም ያለ ጥርጥር በኢየሱስ ተአምር ከሕመማቸው የተፈወሱ ነበሩ::

እንደ ሌሎቹ ሁሉ ኢየሱስ ዮሐንስንም በመጠኑ ገሥጾታል (ሉቃ 7÷23)፤ «በእኔ የማይሰናከል ሰው ሁሉ የተባረከ ነው::» ኢየሱስ ያደረጋቸው ተአምራት መሲሕ መሆኑን ያረጋግጣሉ:: ስለዚህም እኛ ስለ እርሱ ባለን አስተሳሰብ መሠረት እንደሆነ ለማድረግ ከመሞከር ይልቅ እርሱ ስለ ማንነቱ የተናገረውን መቀበል ይኖርብናል:: ኢየሱስ ያደረጋቸው ተአምራት መሲሕ መሆኑን ያረጋግጣሉ:: ስለዚህም እኛ ስለ እርሱ ባለን አስተሳሰብ መሠረት እንዲሆን ለማድረግ ከመሞከር ይልቅ እርሱ ስለ ማንነቱ የተናገረውን መቀበል ይኖርብናል:: ኢየሱስ እንደ ፈለጉ የሚያደርጉት አልነበረም:: ምናልባትም ከተለመደው መንገድ ወጣ ያለ ነው ይባል ይሆናል:: ያኔ እንደ ነበረው ሁሉ ዛሬም ያው ነው:: ሌላውን ጉንጭ ስለመስጠት፣ አስቀድሞ በራስ ዐይን ውስጥ ያለውን ግንድ ማውጣት እንደሚገባ፣ ያለንን ሁሉ ስለ መሸጥ፣ ቤተሰብን ስለመጥላት፣ መስቀልን ስለ መሸከም የተናገረው ሁሉ ዛሬም እውነት ነው:: በብዙ መልኩ ካለንበት አገር ባሕል ጋር ሊጋጭ ይችላል:: ከለመድነው ባሕል ጋር የተጣጣመ እንዲሆን እንፈልጋለን:: እርሱ ግን እንዲህ ያለ አማራጭ አልሰጠንም:: ስለ ራሱ በተናገረው መሠረት እንቀበለዋለን ወይም ደግሞ ጨርሶ አንቀበለውም::



**ሉቃ 7÷24-28**
**ከማቴ 11÷7-11**
**ጋር**

[24]የዮሐንስ መልእክተኞች ከሄዱ በኋላ፣ (የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ከሄዱ በኋላ[ማቴ]) ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ ዮሐንስ ይናገር ጀመር፤ «ወደ በረሓ የወጣችሁት ምን ልታዩ ነው? ነፋስ የሚያወዛውዘውን ሸምበቆ? እኮ! ምን ልታዩ ወጣችሁ? ያማረ ልብስ የለበሰውን ሰው ነውን? ባማረ ልብስ የሚሽሞነሞኑና በድሎት የሚኖሩ በቤተ መንግሥት (በነገሥታት ቤት[ማቴ]) አሉላችሁ:: [26]እኮ! ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን ለማየት
ይሆን? አዎን፣ እላችኋለሁ፤ ለማየት የወጣችሁት ከነቢይም የሚበልጠውን ነው::
[27]እንዲህ ተብሎ የተጻፈለትም እርሱ ነው፤ 'መንገድህን በፊትህ የሚያስተካክል (ከሚል
1÷2፤ ዘፀ 23÷20 ጋር ያነ) መልእክተኛዬን ከአንተ አስቀድሜ እልካለሁ::'
[28]እላችኋላሁ፤ ከሴት ከተወለዱት መካከል ከዮሐንስ (መጥምቁ[ማቴ]) የሚበልጥ
የለም፤ በእግዚአብሔር መንግሥት (መንግሥተ ሰማይ[ማቴ]) ግን ከሁሉ የሚያንሰው
ይበልጠዋል::»

ሁለቱ መልእክተኞች ወደ ዮሐንስ ከተመለሱ በኋላ ኢየሱስ ሕዝቡን ማስተማር ጀመረ:: ከመጠነኛ ግሣጼ በኋላ ወዲያውኑ ዮሐንስን በማድነቅ መናገር ጀመረ:: «ዮሐንስ ማነው?» ለሚለው ጥያቄ ኢየሱስ ትክክል ያልሆኑ ሁለት አማራጮች አቀረበ፤ (1) ነፋስ የሚያወዛውዘው ሸንበቆ? ዮሐንስ ያን ያህል ደካማ አልነበረም:: በምድረ በዳ ያደገ እንደ መሆኑ መጠን በአካል ጠንካራ ብቻ ሳይሆን፣ ጽኑ ግብረ ገባዊ አቋም የተጎናጸፈም ነበር፤ (2) ያማረ ልብስ የለበሰ ሰው በፍጹም የግመል ጠጉር ያማረ ልብስ አልነበረም::

እንደ ነቢይነቱም ሆነ ሰብዓዊ ፍጥረቱ የመጥምቁ ዮሐንስ ተጠሪነት ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነበር:: ይህ ከባድ፣ ከዚያም በላይ የሚያስገርም አባባል ነው:: ዮሐንስ ከታላላቅ የእምነት ሰዎች ዝርዝር

በጣም ርቆ ነበር ያለው፤ አብርሃም፣ ሙሴ፣ ኤልያስ፣ ዳዊት፣ ወዘተ:: ታዲያ፣ የዮሐንስን ታላቅ ያደረገው ምንድነው?

(1) ዮሐንስ ለክርስቶስ መንገድን ያዘጋጀ ነበር (ሚል 3÷1):: ወደ እርሱ የማመልከትም ሆነ አምላክም ሰውም የሆነውን መሲሕ የማጥመቅ መብት ለማንም አልተሰጠም:: ዮሐንስ አንድም እንኳ ከዚህ ኀላፊነቱ አልተዘናጋም:: ሥራው ታላቅ ነበር፤ እርሱም በአስደናቂ ሁኔታ ተወጥቶታል::

(2) የነቢያት ድምፅ መስማት የተቋረጠበት የአራት መቶ ዓመታት ዝምታ የተሰበረው በእርሱ ነበር:: በተጨማሪም በሚገርም ሁኔታ ታዋቂ ነበር:: እርሱን ለመስማትና በእርሱ ለመጠመቅ ሕዝቡ ሁሉ ግልብጥ ብሎ ወጥቷል:: ብዙ ደቀመዛሙርት ነበሩት፤ ይህም ለነበረው ሥልጣንና ተወዳጅነት ምስክር ነበር::

(3) ዮሐንስ የትሕትና ምሳሌ ሆኗል፤ ያን ያህል ተወዳጅ ቢሆንም እርሱ ግን ኢየሱስን ከፍ ከፍ ያደርግ ነበር:: እንዲያውም የጫማውን ማሰሪያ ክር ለመፍታት እንኳ ብቁ አለመሆኑን ተናግሮ ነበር:: የኢየሱስ ታዋቂነት እየጐላ የመምጣቱን ያህል የእነርሱ ተሰሚነት እያነሰ መሄዱን በተመለከተ የዮሐንስ ደቀመዛሙርት በጠየቁት ጊዜ፣ «እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ይገባል» በማለት ነበር የመለሰው (ዮሐ 3÷30)::

«ከሴት ከተወለዱት መካከል» የሚለው፣ «ከሰዎች» ለማለት የሚጠቀሙበት የሴማውያን አነጋገር ፈሊጥ ነው:: ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር በዚህ ዓለም ማንም ታላቅ የለም:: ይሁን እንጂ የሚያስገርም ቢሆንም እንኳ በእግዚአብሔር መንግሥት በጣም ታናሽ የተባለው ከዮሐንስ ይበልጣል:: በጣም ታናሽ የተባለ ክርስቲያን ከዮሐንስ፣ (ከፍ ሲል ከአብርሃም፣ ከሙሴ፣ ከዳዊት፣ ወዘተ) የበለጠ የሚሆነው እንዴት ነው? (1) ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ በመሞላቱና በእርሱ ውስጥ የሚኖር በመሆኑ (ዮሐ 7÷38 -39፤ 16÷7፤ ሐሥ 1÷7-8):: (2) የተሻለ ኪዳን ተካፋይ በመሆኑ (ዕብ 8÷8-12፤ 2ቆሮ 3÷7-18)፣ ከዚህም የተነሣ፣ (ሀ) የእግዚአብሔር ሕግ በልቡና በአምሮው ተጽፎል፣ (ለ) በግሉ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ስለሚችል፣ (ሐ) በግሉ እግዚአብሔርን ስለሚያውቅ፣ (መ) ኀጢአቱ ይቅር ስለ ተባለለት:: (3) የተስፋው ልጅ ከሥጋ ወይም ከሕግ በታች ባለመሆኑ (ሮሜ 9÷8፤ ገላ 4÷28)::

ክርስቲያኖች ከዮሐንስ የበለጠ መብት ስላላቸው፣ ከእርሱ የበለጠ ኀላፊነት አለባቸው:: እዚህ ላይ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ግን ስለ ባሕርይ እንጂ መብት አይደለም:: ከላይ የተዘረዘሩት መብቶች በስጦታ የተቀበልናቸው እንጂ በራሳችን ጥረት ያገኘናቸው አይደለም:: በክርስቶስ ያገኘነውን አዲስ ባሕርይ በእርሱ ከምንቀበላቸው ስጦታዎች መለየት አይቻልም:: በመንፈስ ቅዱስ የተሞላን እንደ መሆናችን መጠን የመለኮቱ ተካፋዮች ሆነናል:: የኀጢአት ይቅርታ ስለ ተቀበልን ኀጢአት የሌለብን ሆነናል:: በግል ሕይወታችን እግዚአብሔርን ስለምናውቅ የእግዚአብሔር ወዳጆች ሆነናል:: ክርስቲያኖች ከዮሐንስ የበለጡ የሆኑት ለእግዚአብሔር ካደረጉት የተነሣ ሳይሆን እግዚአብሔር ካደረገላቸው የተነሣ ነው::

**ማቴ 11÷12-15**

12ከመጥምቁ ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን
ድረስ መንግሥተ ሰማያት በብዙ ትገፋለች፤ የሚያገኟትም
ብርቱዎች ናቸው፤ 13ነቢያትም፣ የሙሴ ሕግም ሁሉ እስከ
ዮሐንስ ድረስ ትንቢት ተናገሩዋልና:: እንግዲህ
ልትቀበሉት ከፈቀዳችሁ ይመጣል የተባለው ኤልያስ እርሱ
ነው:: 15ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ::

ቁጥር 12 ለትርጉም ያስቸግራል (ከሉቃ 16÷16 ጋር ያነ):: አንዳንዶች አዎንታዊ ገጽታ እንዳለው ያስባሉ:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ ብርቱ እምነት ያላቸው ኀይለኞች በራሳቸው ክርስቶስን መከተል

የሚያስችላቸው ዐቅም ይኖራቸዋል::[105] ይሁን እንጂ *ቢያዜታይ* እና *ሐርፖዞ* የተሰኙት ቃላት የሚያመለክቱት አመጽን ሲሆን አጠቃላይ በሆነ መልኩም አሉታዊ አንድምታ አላቸው:: ጆሴፈስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ሁለት ቃላት የተጠቀመባቸው ከጦርነት፣ ከዐመፅና ጭቆና ጋር በተያያዘ መልኩ ነበር:: እንዲያውም «የሚያገኟትም ብርቱዎች ናቸው» (ቁ 12) የሚለው ሐረግ አስገድዶ መድፈርን የሚያመለክት ነው::[106] ስለሆነም እነዚህ ብርቱ ሰዎች ከመግባባት ይልቅ ኀይል የሚጠቀሙና የእግዚአብሔርን መንግሥት ያልተረዱ መሆናቸው ግለጽ ነው::[107] ስለሆነም ቁጥር 12 ላይ ያለው ቀደም ሲል ቁጥር 11 ላይ ከቀረበው ጋር በንጽጽር የቀረበ ነበር ማለት ነው::

ይህ ታሪካዊ መቼትንም ያመለክታል:: ሕዝቡ በከፍተኛ ጉጉት መሲሐዊውን መንግሥት ጠብቀዋል:: ሲጠብቁ የኖሩት ሲመጣ ግን ምላሻቸው የዐመፅ ነበር፤ (1) መጥምቁ ዮሐንስ ታስሮ አንገቱ የሚቀላበትን ጊዜ እየጠበቀ ነበር:: (2) አሁን ደግሞ ፈሪሳውያን በየአጋጣሚው ኢየሱስን እየተቃወሙና ትውፊቶቻቸውን መሠረት በማድረግ ትምህርቶቹን ለማስተባበል እየሞከሩ ነው:: (3) ተራው ሕዝብ ኢየሱስን የዐመፅ መሪ በማድረግ ፖለቲካዊ ሥልጣን ለማስያዝ እየፈለጉ ነበር (ከዮሐ 6፥15 ጋር ያነ):: ይህን አዲስ የታወጀ መንግሥት ለማጥፋት ሰይጣን እያሤረ መሆኑ ግልጽ ነበር::

ዮሐንስ በአካል የተወለደ ኤልያስ ሳይሆን፣ የኤልያስ ፍጻሜ እንደ ነበር ኢየሱስ አመለክቷል (ከሚል 3፥1፤ 4፥6፤ ከሉቃ 1፥17 ጋር ያነ)፤ የአዲሱ ዘመን ዐዋጅ ነጋሪ እንጂ በአካል የመጣ ኤልያስ እንዳልነበረ ዮሐንስ ራሱ ተናግሮአል::

**ሉቃ 7፥29-30**

[29]ቀረጥ ሰብሳቢዎች እንኳ ሳይቀሩ፣ ይህን
የኢየሱስን ቃል የሰሙ ሁሉ፣ በዮሐንስ እጅ በመጠመቅ
ለእግዚአብሔር ተገቢውን ክብር ሰጡት፤ [30]ፈሪሳውያንና
ሕግ ዐዋቂዎች ግን በዮሐንስ እጅ ባለመጠመቃቸው
እግዚአብሔር በእነርሱ ያለውን ዐላማ አውቃለሉ::

ኢየሱስ ዮሐንስን አስመልክቶ የሰጠው ገለጻ በሕዝቡ ዘንድ ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች እንዲኖሩ አድርጓል:: ሕዝቡ ቀረጥ ሰብሳቢዎችን ጨምሮ «አዎን፣ ልክ ነው» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል:: እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ በዮሐንስ እጅ ተጠምቀዋል:: በሌላ በኩል ደግሞ ፈሪሳውያን የዮሐንስን ጥምቀት በዚያም ሳቢያ ራሱ ኢየሱስን ጭምር አቃልለዋል:: ዮሐንስ እውነተኛ መሆኑን መቀበል አልፈለጉም (ማቴ 21፥23-27):: ምንም እንኳ ለይስሙላ ያህል አንዳንድ ፈሪሳውያን ለመጠመቅ ወደ ዮሐንስ ቢመጡም፣ አብዛኞቹ ግን እርሱን ለመሞገትና ለማጥመድ ነበር የሚመጡት:: ኢየሱስ ተወዳጅ እየሆነ መምጣቱ እርሱን ለመግደል በቅንነት እንዲነሡ ካደረገ፣ የዮሐንስ ተወዳጅ መሆን ፈሪሳውያንን አያስቆጣቸውም ማለት ይከብዳል::

**ሉቃ 7፥31-35**
**ከማቴ 11፥19 ጋር**

[31]እንግዲህ የዚህን ትውልድ ሰዎች በምን
ልመስላቸው? ምንስ ይመስላሉ? [32]በገበያ ቦታ ተቀምጠው
እርስ በርሳቸው እየተጠሩ እንዲህ የሚባባሉ ልጆችን

[105] ቢያዜታይ (*Biazetai*) የሚለው ቃል አዎንታዊ ሊሆን የሚችለው ከተደራጊ (Passive) ይልቅ በመካከለኛ ድምፀት (middle voice) የቀረበ እንደሆነ ነው፤ ይሁን እንጂ ፔክታ የተሰኘው የሶሪያውያን አነጋገር ዘዬም ሆነ ጥንታዊው የሶሪያ ትርጉም በተደራጊ መልኩ ነው የሚያስቀምጠው:: ስለዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት፣ «በኃይል ትስፋፋለች» ከማለት ይልቅ፣ «ኃይለኞች ያጠቋታል» ማለት ነው፤ በተጨማሪም ፔሽታ የተሰኘው የሶሪያ አነጋገር ዘዬ፣ «ብርቱዎች» የሚለውን፣ «እረኛ መሪዎች» በማለት ተርጉሞታል:: ምናልባትም ይህ የሕዝ 34ን ነገረ መለኮታዊ ሐሳብ ያንጸባርቃል፤ ፈሪሳውያን በዚህ አዲስ በተቋቋመ መንግሥት ላይ እየተሰነዘረ ያለውን ጥቃት እየመሩ ነበር የሚለውን ይበልጥ ተአማኒ ያደርገዋል:: E. Moore. “Violence to the Kingdom,” *ExpT* 100 (1980): 174-177.

[106] እዚህ ላይ የተሰኘው እንስታዊ መጠሪያ የእግዚአብሔር መንግሥትን እንጂ ሴትን የሚያመለክት አይደለም::

[107] E. Moore “*BIAZO, HARPAZO* and Cognates in Josephus, “*NTS* 21(1975): 519-543.

ይመስላሉ፤ ዋሽንተ ነፋንላችሁ፤ አልጨፈራችሁም፤ ሙሾ አወረድንላችሁ
አላለቀሳችሁም። [33]ምክንያቱም መጥምቁ ዮሐንስ እህል ሳይበላና የወይን ጠጅ ሳይጠጣ
ቢመጣ፣ ጋኔን አለበት አላችሁት፤ [34]የሰው ልጅ ደግሞ እየበላና እየጠጣ ቢመጣ፣
በላተኛና ጠጪ፣ የቀረጥ ሰብሳቢዎችና 'የኀጢአተኞች' ወዳጅ አላችሁት። [35]እንግዲህ
የጥበብ ትክክለኛነት በልጆቿ ሁሉ ዘንድ ተረጋገጠ።

ኢየሱስ በዘመኑ የነበሩ ሰዎችን በገበያ ቦታ በማስመሰል እየተጫወቱ ባሉ ሰዎች መስሎአቸዋል። መጀመሪያ ላይ «የሠርግ ቤት» ዓይነት በማስመሰል ተጫወቱ፤ ሌሎቹ ልጆች ግን አላጀቧቸውም። በኋላ ደግሞ፣ «ቀብር ላይ» ያሉ በማስመሰል ይጫወቱ ጀመር፤ ሆኖም ሌሎቹ ልጆች በጨወታው መካፈል አልፈለጉም። በኢየሱስና በፈሪሳውያን፣ እንዲሁም በሰዱቃውያን መካከል የነበረው ሁኔታ ይህን ይመስላል። የሃይማኖት መሪዎቹ ኢየሱስም ሆነ ዮሐንስ መጫወት በማይፈልጉት ዓይነት ጨዋታ እየተሳተፉ ነበር። እንዲያውም አስቆጣቸው። ስለዚህ መሪዎቹ አጠቋቸው። ዮሐንስን ጋኔን አለብህ ሲሉት፣ ኢየሱስንም ጠጪ ነህ አሉት። በእንዲህ ዓይነት ምድብ ውስጥ ካስቀመጧቸው የስብዕናቸውም ሆነ የትምህርታቸው ተካፋይ አይሆኑም። ሆኖም ጉዳዩ በዚህ ብቻ አያበቃም። የነገሩን መቋጫ የምንመለከተው ቁጥር 35 ላይ ነው።

«የጥበብ ትክክለኛነት ተረጋግጠ»፤ «ትክክለኛነት ተረጋገጠ» የሚለው ግስ (ትእዛዛዊ ኀላፊ አንቀጽ)፣ «ጥበብ በልጆቿ ጸደቀች» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። ገና ሙሉ በሙሉ ተጨባጭ ባይሆንም፣ በሥራዋ መረጋገጡን ያመለክታል። ኢየሱስም ሆነ ዮሐንስ ከነቀፋ በላይ የሆነ ሕይወት ኖረዋል። ማንም ሊነቅፋቸው ወይም ሊተቻቸው አይችልም። ስለሆነም በሕይወታቸው ወይም በአኗኗራቸው ጠቢብነታቸውን አሳይተዋል። በተቃዋሚዎቻቸው ትችትና ስም ማጥፋት ቢደረግባቸውም እነርሱ ግን ትክክል ነበሩ።



ዮሐንስ ያሳየው ጥርጣሬ ሕዝቡን ሳያስገርም አልቀረም። ዮሐንስ ከተጠራጠረ የኢየሱስን ማንነት ጥያቄ ውስጥ ለማግባት በቂ ምክንያት ሊኖር ይችላል ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ፈሪሳውያን የሚያቀርቡት ክስና «ከሥርዓት የወጣ» የኢየሱስ አኗኗርና የአሰባበክ መንገድ ሕዝቡ የየራሳቸው ጥርጥር እንዲኖራቸው ሊያደርግ ይችላል። ኢየሱስ እርሱን አስመልክቶ ዮሐንስ ባነሣው ጥያቄ መልስ መስጠት ብቻ ሳይሆን፣ የዮሐንስን ታላቅነትም አረጋግጧል። ኢየሱስ አሁንም ጥርጣሬ ላላቸው ሰዎች ስለ ማንነቱ የሚሰጠው ማረጋገጫ አይኖርም። ሥራዎቹ ለራሳቸው ስለሚመሰክሩ ቀይታችሁ ተመለከቱ ብቻ ነው የሚለው።

**§ 58**
**ወዮ፣ ንስሐ ላልገቡ ከተሞች**
**(ማቴ 11፥20-30፤ ከሉቃ 10፥13-15 ጋር ያነ)**

እዚህ ላይ እንግዳ የሆነ ክፍል ነው የምንመለከተው። ኢየሱስ ላደረጋቸው ተአምራት በጐ ምላሽ መስጠት የነበረባቸው ከተሞች እንደዚያ ሲያደርጉ አልታዩም (ቁ 20-24)። እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ ይታሰቡ የነበሩ ሰዎች ገና ጨለማ ውስጥ ነበሩ። ምንም አያውቁም የተባሉት ግን አውቀው ተገኝተዋል (ቁ 25-26)። የእግዚአብሔር ሰው የሆነው ኢየሱስ የዋህና ትሑት ሆኖ ቀርቧል (ቁ 29፣ ከማቴ 3፥15፤ 8፥17፤ 12፥19፤ 21፥5 ጋር ያነ)። አንገታችን ላይ የአገልግሎትን ቀንበር ቢያኖር እንኳ ቀንበሩ ቀላልና ነጻ የሚያወጣ ነው (ቁ 28-30)።

**ማቴ 11፥20-24**

[20]ከዚያም ኢየሱስ ብዙውን ታምራት
ያደረገባቸው ከተሞች ንስሐ ባለመግባታቸው እንዲህ ሲል
ወቀሳቸው፤ [21]«ወዮልሽ ኮራዚን፤ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ፤
በእናንተ የተደረገው ታምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ
ቢሆን ኖሮ፣ ገና ድሮ ማቅ ለብሰው፣ ዐመድ ነስንሰው
ንስሐ በገቡ ነበር። [22]ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ለፍርድ ቀን

ከእናንተ ደሰቀ ሰጢሮስና ለሲዶና ቀጣቱ ደቀለላቸዋል:: 23አንቺም ቅፍርናሆም ወደ
ሰማይ ከፍ ከፍ ማለት ፈለግሽ? ነገር ግን ወደ ሲዖል ትወርጃለሽ፤ በአንቺ የተደረገው
ታምራት በሰዶም ቢደረግ ኖሮ፣ እስከ ዛሬ በቀየች ነበር:: 24ስለዚህ እልሻለሁ፤ በፍርድ
ቀን ከአንቺ ደለቀ ቀጣቱ ለሰዶም ደቀለላታል::

*23 ግሪኩ ሀዴስ ደባሪ*[108]

ኮራዜንና ቤተ ሰይዳ በገሊላ አገልግሎቱ ኢየሱስ እንደ መነሻ ከተጠቀመባት ከቅፍርናሆም ወጣ ብለው የሚገኙ ከተሞች ናቸው:: ከማንኛውም የአካባቢ ከተሞች ይልቅ ኢየሱስ እነዚህን ከተሞች ያዘወትር ነበር፤ ያደረጋቸውን ተአምራት የማየት ስለ ዕድልም ነበራቸው:: የሹሙን ልጅ፣ ሽባውን፣ በምኩራብ አጋንንት የነበሩበትን፣ የጴጥሮስን አማች፣ የመቶ አለቃውን አገልጋይ፣ የኢያኢሮስን ልጅ፣ ደም ይፈስሳት የነበረችውን ሴት፣ ሁለቱን ዐይነ ስውሮች፣ አጋንንት የነበሩበትን ዲዳ፣ እንዲሁም ሌሎች ብዙዎችን ኢየሱስ የፈወሰው እዚህ ነበር:: ኢየሱስ እዚያ በመገኘቱ ብዙዎቹ ደስተኞች ነበሩ፤ ይሁን እንጂ በተገቢው መንገድ ንስሐ በመግባት ምላሽ አልሰጡም::

ከእነዚህ ከተሞች ጋር በማነጻጸር ኢየሱስ ቀንደኛ የእስራኤል ጠላቶች የነበሩትን ጢሮስና ሲዶናን (ከኢሳ 23፤ ሕዝ 26-38፤ አሞ 1÷9-10 ጋር ያነ)፣ እንዲሁም በኀጢአቷ የምትታወቀውን ሰዶምን አንሥቷል (ዘፍ 19):: አይሁድ ለእነዚህ ቦታዎች ከፍተኛ ንቀት ነበራቸው፤ የኢየሱስ አነጋገርም የበትር ያህል ነበር:: ኢየሱስ ወደ እነዚህ አረማውያን ከተሞች ሄዶ ቢሆን ኖሮ ንስሐ በገቡ ነበር፤ ሌላው ቀርቶ አይሁድ ከፍተኛ ሐዘንን በሚገልጹበት ዓይነት ማቅ ለብሰው ዐመድ ነስንሰው ንስሐ ይገቡ ነበር (አስ 4÷1፣3፤ ኢሳ 58÷5፤ ኤር

[108] ያም ማለት የሙታን መኖሪያ ነው:: እዚህ ላይ ግን ጥልቀትን፣ ያም አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል ርቆ እንደሚሄድ ለማመልከት ነው የዋለው::



6+26፤ ዳን 9÷3፤ ሉቃ 10÷13):: ድሪቶ የሆነ ሻካራ ጨርቅ እንደ ማቅ ሲያገለግል፣ የማይጠቅም በፍታ ነበር:: የተንጨባረረ ፀጉርና ዐመድ የተቀባ ፊት አንድ ሰው ውስጡ የዘለቀውን ጥልቅ ሐዘን የሚገልጽበት መንገድ እንደሆኑ ይታሰብ ነበር::

ዋናው ነጥብ ምንም ዕድል ካልነበራቸው ይልቅ ክርስቶስን ለመቀበል ዕድል በነበራቸው፣ ሆኖም ባልተቀበሉት ላይ የበለጠ ፍርድ የሚጠብቃቸው መሆኑ ነው:: የተቀበልነው መገለጥ ታላቅ የመሆኑን ያህል ኀላፊነታችንም የዚያኑ ያህል ታላቅ ይሆናል (ከሮሜ 2÷12-16 ጋር ያነ):: ኢየሱስ በእነዚህ ከተሞች ተአምራት ስላደረገ ምላሽ ተጠብቆባቸው ነበር:: እንደዚያ ባለማድረጋቸው ግን ሊፈረድባቸው ነው::[109]

25በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «የሰማይና
ማቴ 11÷25-27 የምድር ጌታ አባት ሆይ፤ ይህንን ከጥበኞችና ከዐዋቂዎች
ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፤ 26አዎን
አባት ሆይ፤ ይህ በፊትህ በጐ ፈቃድህ ሆኖ ተገኝቶአልና::
27ሁሉ ነገር ከአባቴ ተሰጥቶኛል፤ ከአብ ሌላ ወልድን የሚያውቅ የለም
ከወልድና ወልድ ራሱ ፈቅዶ ከሚገልጥላቸው ሌላ አብን የሚያውቅ የለም::

በዚህ ታሪክ ኢየሱስ ድጋሚ እርስ በርሱ የሚጋጭ የሚመስል ነገር ተናግሮአል፤ ብዙ እንደሚያውቁ የምናስባቸው ጥበበኞች ምንም አያውቁም፤ ምንም አያውቁም የምንላቸው ሕፃናት ግን የተለየ መገለጥ አግኝተዋል:: ያም ሆኖ ግን ጥበበኞቹ ትምህርት የሌላቸው ወይም ሞኞች ናቸው ማለት አይደለም:: ስለ ዓለም፣ ምናልባትም ስለ እግዚአብሔር ብዙ ሊያውቁ ይችላሉ:: ሆኖም፣ በግል ሕይወታቸው

[109] ማካጋርቬ እንደሚሉት በሠላሣ ዓመት ውስጥ እነዚህ ሦስት ከተሞች ሊደመሰሱ ነበር (ገጽ 288):: ሆኖም፣ «ጢሮስና ሲዶና ወንጌልን ተቀብለዋል (ሐሥ 21÷3፤ 27÷3) ጥብርያዶስም የአይሁድ ማዕከል ሆናለች (ገጽ 286-287)::

አያውቁትም፤ እንዲህ ያለው ዕውቀት የሚገኘው በመገለጥ ብቻ ነው:: እንዲህ ያለው መገለጥ ለሕፃናት ተሰጥቶአል:: እግዚአብሔር አብን በተለየ ሁኔታ የሚያውቅ ኢየሱስ ብቻ ነው፤ እርሱ ደግሞ ለትሑታን፣ ለተዋረዱት፣ ለታናናሾችና ለጠፉት ሊገልጠው ወዷል:: ብርቱ የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ (ማቴ 28÷18፤ ቈላ 1÷16-19) የለዚህ ዓለም ደካሞችን ብርቱዎች በማድረግ በርቱዎችን ረታ::[110]

[28]«እናንተ ሸክም የከበዳችሁነስ የደከማችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም ዕረፍት እሰጣችኋለሁ:: [29]ቀንበሬን ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ በልቤ የዋህና ትሑት ነኝና፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ [30]ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና::

ማቴ 11÷28-30

ምንኛ ክቡር ጥሪ ነው! ጥድፊያ ውስጥ ላሉት፣ በተለይም ኢየሱስን በሚጠሉ ሰዎችና ዕረፍት በሌለበት ሁኔታ ላሉት ይህ እጅግ የሚያጽናና ቃል ነው:: ስለሆነም ይህ ጥሪ በተለያየ ነውጥ ውስጥና በተለያየ ኹካታ ውስጥ ያሉ ወደ ርጋታ እንዲመጡ የቀረበ ጥሪ ነው:: ይሁንና አባባሉ እርስ በርሱ የሚቃረን ይመስላል:: ቁጥር 28 ላይ ኢየሱስ፣ «ዕረፍት እሰጣችኋላሁ» ብሏል:: ከዚሁ ጋር አያይዞም፣ «ቀንበሬን ተሸከሙ» ብሏል:: ብዙ ጊዜ ቀንበር የሚያመለክተው ሕግን ነው (ገላ 5÷1፣ ሐሥ 15÷10 ፤ ሲራክ 51÷26):: አይሁድ ሕጉ ስጦታ እንጂ ባርነት ነው ብለው አያስቡም:: ልዩ የእግዚአብሔር ሐዝብ

[110] ኢየሱስ ከአብ ጋር ስላለው ግንኙነት በእንዲህ ያለ ሁኔታ በድፍረት መናገሩን ግምት ውስጥ በማስገባት አንዳንድ ምሑራን ስለ ራሱ ይህን የተናገረው እርሱ ሊሆን አይችልም ብለዋል:: ምናልባትም በጥንት ቤተ ክርስቲያን የተጨመረ ሊሆን ይችላል ይላሉ:: አይ ኤች ማርሻል ግን ኢየሱስ ስለ ራሱ እንደዚያ ያስብ እንደ ነበርና ያንንም መናገሩን አመልክቷል:: I.H. Marshall, “The Divine Sonship of Jesus,” *Int* 21 (1967):89-103



መሆናቸውን እንደሚያረጋግጥ ነበር የሚረዱት:: ስለሆነም የሕግ ቀንበር አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ለመገዛትና እርሱን ለማገልገል ሲል በፍቃዱ የሚሸከመው እንጂ የጭቆና ቀንበር አይደለም ማለት ነው:: ፈሪሳውያን ግን ለመሸከም የሚከብድ እስከሆነ ድረስ በእግዚአብሔር ሕግ ውስጥ የተለያዩ ሥርዓቶችና ደንቦችን ጨምረው ነበር፤ «ማቴዎስ የኢየሱስን ቀንበር የተረዳው በሰው ልጆች መካከል እግዚአብሔርን በመወከል ላለው ኢየሱስ ስለሚገባው ራስን መስጠት እንጂ ለሥርዓቶችና ደንቦች ታማኝ ሆኖ መገኘትን አይደለም::»[111]

ኢየሱስ፣ ማቴዎስ 10÷38 ላይ መስቀሉን ተሸክመን እንድንከተለው ጠርቶን እያለ አሁን ቀንበሬ ልዝብ፣ ሸክሜም ቀላል ነው ከማለት የሚናገረው እንዴት ነው? በመሠረቱ፣ ቀላል ሲል፣ «ተገቢ»፣ «የሚመች» ወይም «በጐ» ነው ማለት እንጂ ምንም «ውጣ ውረድ» የሌለበት ነው ማለት አይደለም:: የኢየሱስ ሥራ፣ «የሚመች» እንጂ «አታካች» አይደለም:: እንዲህ ስለ ተባለ ግን ክርስቲያን መከራ ወይም ችግር አይገጥመውም ማለት አይደለም:: መስቀሉ ቀላል ቢሆንም፣ ነጻ የሚያወጣ ነው:: ከዚህ ዓለም ባርነትና ጥፋት፣ (ማቴ 6÷33)፣ ሕግ ከሚያስከትለው ቅጣት፣ (ገላ 5÷1-4)፣ የሰዎችን ምስጋና ከመፈለግ (ዮሐ 5÷41-44) ነጻ ወጥተናል:: በእርግጥም፣ ይህ የምሥራች ነው:: ይህ ዕረፍት በእንዴት ዓይነት ሁኔታ እውን ሊሆን እንደሚችል ማቴዎስ ሰንበትን በተመለከተ የተነሡ ሁለት አለመግባባቶችን አቅርቧል (ማቴ 12÷1-14):: የመጀመሪያው ኢየሱስ እሸት ቀጥፎ መብላቱን በተመለከተ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን እጁ የሰለለውን ሰው መፈወሱን በተመለከተ ነበር:: እንደሚለው እነዚህ በተራቸው ኢየሱስ በሚሰጠው ዕረፍት ውስጥ ጉልህ ስፍራ ያላቸው ሁለት ዐቢይ ሐሳቦችን አቅርበዋል፤ እነርሱም መዋጀት (ማቴ 12÷1-8) እና መታደስ ናቸው (ማቴ 12÷9-

[111] M. Maher, "Take My Yoke Upon You," *NTS* 22 (1975): 97-103.

14)::[112] ኢየሱስ ስለሚያድነንና ስለሚያድሰን በእርሱ ቀንበር ማረፍ እንችላለን::

§ 59
ኢየሱስ በኀጢአተኛ ሴት ሽቱ ተቀባ
(ሉቃ 7÷36-50)

ይህ ታሪክ ማቴዎስ 26÷6-13፤ ማርቆስ 14÷3-9 እና ዮሐንስ 21÷1-8 ላይ[113] ከተጻፈው ጋር ተመሳሳይ ነው:: ከሁለቱም ታሪኮች እንደምንመለከተው ስምዖን በሚባል ሰው ቤት ግብዣ ላይ እያለ አንዲት ሴት ከአልባሳጥሮስ ብልቃጥ ኢየሱስን ሽቱ ቀባችው፤ በሁለቱ ታሪኮች መካከል ግን ጉልህ ልዩነቶች አሉ፤

1. ቦታዎቹ የተለያዩ ነበሩ፤ የፈሪሳዊ ቤት እና የለምጻሙ ሰው ቤት::
2. ከሉቃስ የምንመለከተው እግሮቹን በሽቱ መቀባቱን ነው፤ በተጓዳኝ ምንባቡ ግን እግሮቹንም ራሱንም መቀባቱን እናያለን::
3. ሉቃስ ሴትየዋ እያለቀሰች እንደ ነበር ቢናገርም፣ ሌሎች ግን ስለዚህ የሚሉት የለም::
4. ሉቃስ ላይ ካለው ታሪክ እንደምንመለከተው ታሪኩ የተፈጸመው ኢየሱስ የገሊላ አገልግሎቱን ባጋመሰበት ወቅት ላይ ነበር:: ከተጓዳኝ ምንባቡ የምንመለከተው ግን ታሪኩ የተፈጸመው ክርስቶስ መስቀል ላይ ከመሞቱ አንድ ሳምንት በፊት ነበር::
5. ሁለት የተለያዩ ትምህርቶች ቀርበዋል:: የዚህ ምንባብ ትኩረት ያቺ ኀጢአተኛ ሴት ንስሐ ማድረጓ ላይ ነበር:: ሌሎች ግን

[112] S. Bacchiocchi "Matthew 11:28-30: Jesus' Rest and the Sabbath," *AUSS* 22/3 (1984): 289-316.

[113] ብዙ ምሑራን የተቀባው አንዴ ብቻ ሲሆን ሌላው ግን ነገረ መለኮታዊ ምክንያት አርትዖት ተደርጉበታል ይላሉ:: ከ R. Holst "The One Anointing of Jesus: Another Application of the Form – Critical Method" *JBL* 95/3 (1976): 435 – 446 እና J.K Elliott, "The Anointing of Jesus," *ExpT* 85 (1973-74): 105-107 ጋር ያነ::



ለድኾች መዋል ሲገባው ኢየሱስ ላይ ስለ ባከነ ብዛት ያለው ገንዘብ ላይ ነበር ትኩረታቸው::

ስለሆነም ይህ ማቴዎስ፣ ማርቆስና ዮሐንስ ካቀረቡት መቀባት የተለየ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ እንደርሳለን::[114]

ሉቃ 7÷36-38

36 ከዚህ በኋላ ከፈሪሳውያን አንዱ ምግብ አብሮት እንዲበላ ኢየሱስን ጋበዘው፤ እርሱም ወደ ፈሪሳዊው ቤት ሄዶ በማእድ ተቀመጠ:: 37 በዚያ ከተማ የምትኖር አንዲት ኀጢአተኛ ሴት፣ ኢየሱስ በፈሪሳዊው ቤት በማእድ መቀመጡን በሰማች ጊዜ አንድ የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ሽቱ ይዛ መጣች፤ 38 ከበስተ ኋላው እግሩ አጠገብ ቆማ እያለቀሰች እግሩን በእንባዋ ታርስ፣ በራሷም ጠጉር ታብሰው ጀመር፤ እግሩንም እየሳመች ሽቱውን ቀባችው::

እንደ ታዋቂ መምህር ኢየሱስ በፈሪሳዊው ስምዖን ቤት ተጋብዞ ነበር:: ከፈሪሳዊው ጋር በተገናኘ ጊዜ ሁሉ ኢየሱስ አንድ ዓይነት አለመግባባት ይገጥመው እንደ ነበር ሉቃስ ያመለክታል (ሉቃ 5÷17-20፣30፤ 6÷2፣6-11):: እዚህም ላይ ቢሆን ንጹሕ ሰው መውቀስ ባንፈልግም ይህ የእራት ግብዣ ኢየሱስን ለማጥመድ የተዘጋጀ ሳይሆን እንዳልቀረ እንጠረጥራለን:: የስምዖን ጓደኞች ሁሉ በቦታው ተገኝተው ነበር (ቁ 49):: እኛም ብንሆን መረዳት እንደምንችለው ስምዖን አንድ ሰው ከወዳጁ የሚጠብቀውን ጨዋነት አላሳየም::

አይሁዳውያን የተለየ ምግብ የሚበሉት ጥቂት ጫማዎች ያህል ከመሬት ከፍ የሚል ገበታ ላይ ነበር:: በስተ ግራቸው በኩል በሚዘጋጀው ትራስ ላይ ይጋደሙ ነበር:: እያንዳንዱ ሰው ራሱን ገበታው

[114] ከዚህ አቋም ጋር A. Legault, "An Application of the Form – Critique Method to the Anointings in Galilee and Bethany," *CBQ* 16 (1954): 131-145 እና ከአርጌነስ ታይታንና ዮሐንስ አፈወርቀ ጀምሮ ብዙ የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች ይስማማሉ::